"በእኛ ፕሮግራም የኩላሊት ህክምናውን ማግኘት አይቻልም"

ዶ/ር ብርሃኔ ረዳኢ

የሃይማኖት አባቶች ሀገር የት ነው?

የሱፍ ጌታቸው

በወቅታዊ የሀገር ጉዳይ የቤተ ክርስቲያን ሚና

ዓባይነህ ካሤ(ዲ.ን)

አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር

በስሌት ወይስ በድንገት?

መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

ግዮን ቅጽ 1 ቁጥር 2 መጋቢት 2010 ዓ.ም

ዋጋ 14.99



## "ሕወሓቶች ለሀገራዊ ጥቅምና ጉዳይ ደንታ የላቸውም"

ብርጋዲየር ጄነራል ተፈራማሞ

# ግዮን


ቅጽ 1 ቁጥር 2 ቅዳሜ መጋቢት 15 2010 ዓ.ም

5 **ፖለቲካ**
ሁነኛ መሪ ጠፋ!

6 **ቅኝት**
**አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር**
በስሌት ወይስ በድንገት?

9 **ተጋባዥ ጸሐፊ**
ኢትዮጵያችን በመንታ መንገድና በገደል አፋፍ ላይ ትገኛለች፤ ዜጎች ምን እንወስን?
**ግርማ ሰይፉ ማሩ**

12 **ነጻ-ሃሳብ**
ኢትዮጵያን እናስቀድም
*ዶ/ር ትዕግሥት መንግሥቱ ኃይለማርያም*



24 **ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ጀግናችን ማን ነው?!**

ቀጣይ ዕትም ቅዳሜ መጋቢት 22 ይጠብቁን!




ቁጥር 1 ዕትም

13 **ጨዋታ**
«የምር ፖለቲካ አልወድም!»
*በኃይሉ ገ/እግዚአብሔር*

14 «ሕዝባችን አንድነቱን ማጠንከር አለበት»
*ደጃዝማች ዑመር ሰመተር*

15 **ዕይታ**
እውነት ሐቅ እና ቅንነት
*መስፍን ጌታቸው*

16 "ሕወሓቶች ለሀገራዊ ጥቅምና ጉዳይ ደንታ የላቸውም"
ብርጋዲየር ጄነራል ተፈራማሞ

21 በወቅታዊ የሀገር ጉዳይ የቤተ ክርስቲያን ሚና
ዓባይነህ ካሤ(ዲ/ን)



8 45 ዓመታት በመድረክ
ፍቃዱ ተ/ማርያም



10 **ፊት-ለፊት**
"በእኛ ፕሮግራም የኩላሊት ህክምናውን ማግኘት አይቻልም"
*ዶ/ር ብርሃኔ ረዳኢ*

26 **ኪነ ጥበብ**
"ዐፄ ምኒልክን ሳያከብሩ ለመርዓዊ ሽልማት ቢሰጡ ምን ዋጋ አለው?"
*አርቲስት መርዓዊ ስጦት*

28 የሃይማኖት አባቶች ሀገር የት ነው?
የሱፍ ጌታቸው

30 "በመለስ ዜናዊ ሞት ክፉኛ ተደብድቤ ሕይወቴ በተዐምር ተርፏል"
**አቶ ዘሪሁን ገብረእግዚአብሔር**

32 ከአሜሪካ ፕሬዝዳንት ቀጥሎ ከፍተኛው ደመወዝ ተከፋዩ ኢትዮጵያዊው ተመራማሪ

# ኦፌኮ መንግስትን ሊከስ ነው

የኦሮሞ ፌዴራላዊ ኮንግረስ (ኦፌኮ) በወቅታዊ ጉዳይ ላይ በሰጠው መግለጫ መንግስት አሁንም የሀገሪቱን ችግር በሠላማዊ መንገድ ከመፍታት ይልቅ ችግሩን በኃይል ለመቆጣጠር እየሰራ ነው ብሏል።

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሀገራችንን ቀውስ ይበልጥ እያባባሰው ይገኛል ያለው ኦፌኮ አዋጁ የፀደቀበት ወቅትና መንገድ ሕገ-ወጥ በመሆኑ በይፋ ከመቃወም በተጨማሪ መንግስትን በህግ ለመክሰስ ተአጋጅቻለሁ ብሏል። የህዝቡ ጥያቄ በአፋጣኝ መመለስ አለበት ብሎ የሚያምነው የኦሮሞ ፌደራላዊ ኮንግረስ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በግልፅ እንደታየው የሀገራችንን ችግር የሚያባብስ እንጂ መፍትሔ የሚያመጣ አዋጅ አይደለም ሲል ይሞግታል።

ለሁለተኛ ጊዜ የተደነገገው አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንዳይፀና የተለያዩ ወገኖች ይፋዊ ጥያቄ አቅርበዋል። አሜሪካ፣ እንግሊዝን ጨምሮ የአውሮፓ ኅብረት አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በዜጎች የመስራትና እንደልብ የመንቀሳቀስ መብት ላይ ገደብ እንደሚጥል በመግለፅ ኢህአዴግ የወሰደው እርምጃ ተገቢ እንዳልሆነ አስታውቀዋል።

የኦሮሞ ፌዴራላዊ ኮንግረስ ምክትል ፕሬዝዳንት አቶ ሙላቱ ገመቹ እንዳሉት " በዚህ ወቅት አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚያስደነግግ ምንም ዓይነት ምክንያት የለም። በታሪክ ከዚህ ቀደም ባልታየ መልኩ ከሰባት መቶ ሽህ በላይ የኦሮሞ ህዝብ በሀገሩ ኢትዮጵያ ውስጥ ተዘዋውሮ የመስራት መብቱ ተጥሷል ብለዋል። ከአዋጁ በኋላ በሞያሌ፣ በቀለም ወለጋ፣ በምዕራብ ሸዋ፣ በሱማሌ ክልል አካባቢ፣ በምስራቅና ምዕራብ ሐረርጌ፣ በጨለንቆ፣ በአወዳይና በሃመሬሳ አካባቢዎች በመንግስት ወታደሮች የዜጎች ሕይወት መጥፋትና አካል መጉደል፣ ንብረት መውደምና ስደት እየከፋ መምጣቱን በመግለጫቸው ጠቅሰዋል።

# የልዑል ራስ መንገሻ ስዩም መጽሐፍ ለገበያ ቀረበ

"የትውልድ አደራ" በሚል ስያሜ የተሰጠው የልዑል ራስ መንገሻ ስዩም መጽሐፍ ለገበያ ቀረበ።

ግለ ታሪክን የተንተራሰው ይህ መጽሐፍ በኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ ስር የተመሰረተውና ‹‹የኢትዮጵያ ፕሬስ አካዳሚ›› የተሰኘው ተቋም አሳትሞታል።

በንጉሱ ዘመን በአውራጃና ጠቅላይ ግዛት አገረ-ገዥነት፤ በከፍተኛ ሚኒስተርነት ለበርካታ ዓመታት ያገለገሉት የራስ መንገሻ ስዩም ግለ-ታሪክ መጽሐፍ በዘመኑ የነበሩ ታሪካዊ ኹነቶችን ወደኋላ መልሶ ያስቃኝ ለትውልድ የሚተላለፍ መልካም ሰነድ እንደሆነ ከጅምሩ ተመስክሮለታል።



# በእስር ላይ ያሉት የዋልድባ መነኮሳት ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጣቸው።

አባ ገብረየሱስ ኪዳነማርያምና አባ ገብረስላሴ ወልደሐይማኖት የተባሉ የዋልድባ አባቶች ጉዳይ በህዝበ ክርስቲያኑና በሌሎች ኢትዮጵያውያን ዘንድ ትኩረት እያገኘ ነው።

መነኮሳቱ በማዕከላዊ እስር ቤት በነበሩ ጊዜ በጨለማ ቤት ውስጥ ለቀናትና ሳምንታት እንዲቆዩ በማድረግ ቶርች በማድረግና የምንኩስና ልባሳችሁን አውልቁ በሚል ከፍተኛ ድብደባ የተፈፀመባቸው መሆኑን በተደጋጋሚ ሲገልፁ ቆይተዋል። ከዚህ በፊት በነበረው ችሎት ፍርድ ቤቱም ከዋልድባ ገዳም ተይዘው በእስር የሚገኙት ሁለቱ መነኮሳት ሀይማኖታዊ ልብሳቸውን ከመልበስ እንዳይከለከሉ ወስኖላቸዋል።

የዋልድባ መነኮሳት መጋቢት አስር በዋለው ችሎት ላይ በመቶዎች የሚቆጠሩ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ድጋፋቸውን አሳይተዋቸዋል። አንድ ሰዓት ዘግይተው የተሰየሙት ዳኞች የመነኮሳቱን ጉዳይ በሶስተኛ መዝገብ የተመለከቱ ሲሆን ቅያሪ የክህነት ልብስ እንዲገባላቸው፣ ተለያይተው መታሰራቸው ቀርቶ በአንድ ላይ እንዲሆኑ በቀደመው ችሎት ያስተላለፉት ውሳኔ ተፈጻሚ መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ ለመጋቢት 18 ተለዋጭ ቀጠሮ በመስጠት ችሎቱ ተጠናቋል።

የዋልድባ መነኮሳት እየደረሰባቸው ያለውን ግፍና ሰቆቃ በተመለከተ በሀገር ቤት የሚገኘው ቤተክህነት ዝምታ አነጋጋሪ ሆኗል።

# "ጤና ለጣና" ዘመቻ በዲያስፖራው መንደር

"ዓለም ዓቀፍ ጥምረት ለጣና ደህንነት" Global Coalition for Lake Tana Restoration የተሰኘው ግብረ ሰናይ ድርጅት በአሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ "ጤና ለጣና" በሚል ባሰናዳው የገቢ ማሰባሰቢያ ዝግጅት ከኢትዮጵያውያን ዲያስፖራዎች ከ140 ሺህ ዶላር በላይ ገቢ አስገኝቷል።

በዋሽንግተን የመድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን በበኩሏ አንድ የእንቦጭ ማስወገጃ ማሽን እሰጣለሁ ብላለች። ድምፃዊ ማህሙድ አህመድን ጨምሮ በርካታ የኪነጥበብ ባለሙያዎች ከተገኙበት የገቢ ማሰባሰቢያ ባሻገር ጥናታዊ ጽሑፎችና ምልከታዎች ቀርበዋል።

የድርጅቱ ሊቀመንበርና በካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ የሕብረተሰብ ጤናና የውሃ ሀብት ተመራማሪ የሆኑት ዶክተር ሰለሞን ክብረት ከዚህ በፊት በአሜሪካ አትላንታ እና በእስራኤል ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን 67,290 ዶላር በተሰበሰበ ገንዘብ Aquamarine H5-200 የተባለው ዘመናዊ የእንቦጭ ማስወገጃ ማሽን ከካናዳ ተገዝቶ በመርከብ እየተጓጓዘ ሲሆን እስከ ሚያዚያ ወር ኢትዮጵያ ይገባል ብለዋል።

"ዓለም ዓቀፍ ጥምረት ለጣና ደህንነት" በዓለም አቀፍ ደረጃ ጣና ሀይቅን እያጠቃ የሚገኘውን እንቦጭ አረም ለማጥፋት ተጨማሪ ማሽኖችን ከመግዛት ባሻገር የሰው ኃይል ስልጠና የመስጠት ብሎም ሐይቁን ወደ ነበረበት ይዞታ የመመለስ ዕቅድ ይዞ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል።

# ባህር ዳር ሁለት ታላላቅ ሰዎችን በሞት አጣች



ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲን ለአራት ዓመታት በፕሬዝዳንትነት የመሩት አንጋፋው መምህርና ተመራማሪ ዶክተር ፀሐይ ጀንበሩ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም በባህርዳር ፈለገ ህይወት ሪፈራል ሆስፒታል በህክምና ሲረዱ ቆይተው መጋቢት 9/2010 ዓ/ም በተወለዱ በ63 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ።

በአስተማሪነት ዘመናቸው በተማሪዎቻቸ ውና በዩንቨርሲቲው ማህበረሰብ ዘንድ እጅግ ተወዳጅና ተሰሚነት የነበራቸው ዶ/ር ፀሐይ ላለፉት 23 ዓመታት በባህር ዳር ዩኒቨርስቲ በመምህርነትና በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ያገለገሉ ሲሆን፣ በጎንደር መምህራን ኮሌጅና በደብረ ማርቆስ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመምህርነት አገልግለዋል። ከምርምር ሥራቸው በተጨማሪ መጽሃፍትን ለአንባብያን ማድረሳቸውንና በባህርዳር ዩኒቨርስቲ የተባባሪ ፕሮፌሰርነት ማዕረግም ማግኘታቸው ተጠቁሟል።

ባህርዳር ዩኒቨርስቲን ከ1997 እስከ 2001 ዓ.ም በፕሬዝዳንትነት በብቃት በመምራት የተቋሙ አህጉራዊና ዓለማቀፋዊ ተፅዕኖ ከፍ እንዲል አድርገዋል። በሀገር አቀፍ የከፍተኛ ትምህርት ፖሊሲ ማዕከል ዋና ዳይሬክተር በመሆን በስርዓተ ትምህርት ዝግጅቶች ከፍተኛ ሙያዊ አስተዋፅኦም አበርክተዋል።

የዶክተር ፀሐይ ጀንበሩ የቀብር ስነስርዓት ቤተሰቦቻቸው፣ ወዳጆቻቸው እና የዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ በተገኙበት መጋቢት10 በባህርዳር ከተማ ተክለሐይማኖት ቤተክርስቲያን ተፈፅሟል።

ከቀኝ አዝማች ጀምበሩ ተድላና ከእማሆይ ምንትዋብ ገደፋው በደብረ ማርቆስ ከተማ በ1947 ዓ.ም የተወለዱት ዶ/ር ፀሐይ ጀምበሩ ባለትዳር፤ የሁለት ሴት ልጆችና የአንድ ወንድ ልጅ አባት ነበሩ።

በተያያዘ ዜና የአኒሜሽን ባለሙያው አቶ ግርማ ዘለቀ በደረሰባቸው ድንገተኛ አደጋ ህይወታቸው ሊያልፍ ችሏል። በተለይም ‹‹ስንዝሮ›› የተሰኘውን የልጆች መዝናኛ ከዓመታት በፊት በሙዚቃ አጅበው በማቅረብ የሚታወቁት አቶ ግርማ ኑሮአቸውን ካደረጉበት አሜሪካ ለእረፍት በመጡበት አጋጣሚ በተፈጠረ ድንገተኛ አደጋ በስለት ተወግተው ሕይወታቸው ሊያልፍ ችሏል።   የአቶ ግርማ ስርአተ ቀብር መጋቢት 12-2010 ቀን በባህር ዳር ከተማ ተከናውኗል።

# የኢትዮጵያውያን ስደት በኬንያ

ከአስር ሺህ በላይ ስደተኛ ኢትዮጵያውያን ከሞያሌ በመሸሽ በኬንያ ከአራት በላይ የስደተኞች ጣቢያ ውስጥ ተጠልለው እንደሚገኙ የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን (ዩኤንኤችሲአር) ገልጿል። ወርልድ ቪዥን ደግሞ ሰማንያ በመቶ ሴቶች እና ህፃናት መሆናቸውን ጠቅሶ ከ3500 በላይ ኢትዮጵያውያን “ሶመሬ” ተብሎ በሚጠራው የስደተኞች ጣቢያ ውስጥ እንደሚገኙ ጠቅሷል። የወርልድ ቪዥን ተወካይ ደንክን ኦዳዎ ለቢቢሲ ሲገልፁ በየጣቢያዎቹ በርካታ ህፃናት እና ነፍሰጡር ሴቶች በተላላፊ በሽታ የመያዝ ዕድላቸው ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰው በኢትዮጵያ መረጋጋት ሰፍኖ የስደተኞች ቁጥር ካልቀነሰ በቀር ነገሮች ከቁጥጥር ውጭ ሊሆኑ እንደሚችል አስጠንቅቀዋል።

የኢትዮጵያ መንግስት በበኩሉ በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነሩ በጀነራል አሰፋ አብዩ እና በአምባሳደር ዲና ሙፍቲ በኩል ለቢቢሲ እንደ ገለፀው ዜጎችን ወደ ቀያቸው ለመመለስ ጥረት እየተደረገ ነው።

ባለፈው ወር መጨረሻ ላይ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በተሳሳተ መረጃ በሞያሌ ተኩስ ከፍቶ ንፁሃን ዜጎች ላይ ግድያ መፈፀሙን ተከትሎ የአካባቢው ቀውስ አሁንም ተባብሶ ቀጥሏል።

# የአዳም ረታ መጽሐፍ በብሔራዊ ቴአትር ተመረቀ




በሚያነሳቸው ርዕሰ ጉዳዮችና ለየት ባለ የአፃፃፍ ስልቱ ከፍተኛ እውቅናን ያተረፈው የደራሲ አዳም ረታ “አፍ” የተሰኘ አዲስ መጽሐፍ ማክሰኞ መጋቢት 11/2010 ዓ.ም በብሄራዊ ቴአትር ተመርቋል።

ኢጋ ሚዲያና ኮሚዩኒኬሽን ከሀሳብ አሳታሚ ጋር በመተባበር ያዘጋጁት የምረቃ ስነ ስርዓት ያማረ ነበር። ደራሲውን ጨምሮ፣ የተለያዩ ፀሐፊያን፣ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶችና የሚዲያ አካላት የተገኙበት ይህ ፕሮግራም በተለያዩ ዝግጅቶች የደመቀ ነበር።

ደራሲ እንዳለጌታ ከበደ ‹‹ኮርኳሪ ሀሳቦች በ”አፍ” ላይ›› በሚል ጽሑፍ የአዳም ረታን አዲስ መጽሐፍ በሚገባ ገልፆታል። የአዳም ረታ ፅሁፎች ይዘት የፎክሎር ይዘት አላቸው ያለው እንዳለጌታ ከበደ  አዳም የያዘውን የተለየ አገላለፅና አፃፃፍ ስልት ተከትለው ወደሙያው የገቡ በርካታ ደራሲያን መኖራቸውንና ይህም አዳም በስነ-ጽሑፉ ዘርፍ የራሱን ጉልህ ድርሻ ማበርከቱን ያመላክታል ብሏል።

ሰፈርን በተለይም የተመረጡ ቦታዎችን መሰረት አደርጎ ድርሰቶቹን ለአንባብያን በማድረስ የሚታወቀው አዳም ረታ በ”አፍ” መፅሐፍ ውስጥም ይህንኑ አካሄድ በግልፅ አስቀምጦታል።

በእለቱ የምረቃ ስነስርዓት ላይ ተወዳጆቹ ተዋንያን ኤልሳቤጥ መላኩና ዋሲሁን በላይ ከመጽሐፉ ውስጥ ቀልባቸውን የገዛውን ፅሁፍ መርጠው በትረካ መልክ ለታዳሚው አቅርበዋል። በቅርቡ ከአሜሪካ የተመለሰው በዕውቀቱ ስዩም የአሜሪካ ቆይታውን ተንተርሶ ያቀረበው አጠር ያለ ወግ ታዳሚውን በእጅጉ ያዝናና ነበር።

“አለንጋና ምስር” ከተሰኘ መጽሐፉ ውስጥ የተመረጠ ታሪክን ወደ ሙዚቃ በመቀየር ገነት ደምሴ በኮንቶፓራሪ ዳንስ ስልት ለዕይታ ያቀረበች ሲሆን ታሪኩን በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ሙዚቃ በመቀየር ጆርጋ መስፍን ትልቅ ሚና ተጫውቷል። በፕሮግራሙ መክፈቻ ላይ ብሌን እጅጉና ባልደረባዋ በትንፋሽ መሳሪያ (በዋሽንት) የታገዘ ጣፋጭ ሙዚቃ ለታዳሚው ሲያቀርቡ ምልዕተ ኪሮስ፣ ደምሰው መርሻና ሙልጌታ አለባቸው ደግሞ ግጥምና መጣጥፎቻቸውን ለታዳሚያኑ አድርሰዋል። ።

# ፌስቡክ እና ዙከንበርግ ላይ ጫናው በርትቷል



የእንግሊዝና ሌሎች የአውሮፓ ሀገራትን ጨምሮ አሜሪካም ሳትቀር በፌስቡክ ላይ ጣታቸውን መቀሰር ከጀመሩ ዋል አደር ብለዋል። የየሀገራቱ ፖርላማዎችም የፌስቡክ አለቃ ማርክ ዙከንበርግ ሁኔታውን እንዲያስረዳ ጥሪ እያቀረቡ ይገኛሉ። የነገሩ መነሻ የአሜሪካው ፌዴራል የንግድ ኮሚሽን ፌስቡክ የ50 ሚልየን ተጠቃሚዎችን ግላዊ መረጃ ለፖለቲካ አማካሪ ድርጅት አሳልፎ ሰጥቷል በሚል ምርመራ እየተካሄደበት ነው፡ ፡ የሰዎችን ግላዊ መረጃ ያለ ይሁንታቸው በመበርበር የተወነጀለው ፌስቡክ ከባለፈው ሰኞ ጀምሮ በገበያ ላይ ያለው ድርሻም እየወረደ መጥቷል።

በሰሜን አሜሪካ የቢቢሲ ቴክኖሎጂ ነክ ዜናዎች ዘጋቢ የሆነው ዴቭሊ እንደሚለው ኩባንያው በ2016ቱ የአሜሪካ ምርጫ ለትራምፕ ቅስቀሳ ቡድን ለተቀጠረው “ካምሪጅ አናሊቲካ” በተሰኘ ተቋም መታለሉን ነው የፌስቡክ ቃል አቀባይ ለመገናኛ ብዙሃን ያስታወቁት። መታለሉን ከታወቀበት ጊዜ በኋላ የፌስቡክ የገበያ ድርሻ በ60 ቢሊየን ዶላር አሽቆልቁሏል። ይባስ ብሎ የአሜሪካው የንግድ ኮሚሽን ፌስቡክ ከተፈበረከበት ጀምሮ ያሉ የሁለት አስርት አመታት መረጃዎች እንዲጣሩ አዟል።

# የሚመረጠው ብሩህ ቀን ዛሬ ነው!

በራሱ የለውጥ አርበኝነት ሰሞን ‹‹የሕዝብ ብሶት የወለደው›› ተብሎ የሚጠራው ኢሕአዴግ፤ ያለ ሕወሓት ደሙ አልዘዋወር እያለና ትንፋሽም የሌለው ሆኖ እስኪሰማው ድረስ፤ ያለፉትን 26 ዓመታት ከ10 ወራት ‹‹የኢትዮጵያና የሕዝቦቿ የዴሞክራሲና የፍትሕ በሎም የልማት ብቸኛ አልኝታ ነኝ›› እያለ አሁን ላይ ደርሷል፡፡ እዚህ የደረሰውም በቀጥተኛዎቹና ጥርት ብለው በሚታዩት፣ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ዘላቂ ጥቅምና ህልውና ዋስትና በሚሆኑት ሕጋዊና ዴሞክራሲያዊ ጎዳናዎች ላይ ብቻ በመረማመድ አይደለም፡፡

አይደለም ለማለታችንም በተደጋጋሚ ሲዳፈኑ የኖሩትንና አሁን በአብዛኛው የኢትዮጵያ ግዛቶች የሚስተዋሉትን አደባባይ የወጡ የዜጎችን ብሶቶች ዋቢ መጥቀሱ በቂ ይመስለናል፡፡ ከሀገሪቱ ፖለቲካዊ ችግር መፍትሔ ማጣትና መልሰው መላልሰው መደፈራረስ አንጻር፤ አያሌ ዜጎች ለእሥራት መዳረጋቸው፣ በይቅርታም ይሁን በምሕረት ወይም ‹‹ዴሞክራሲያዊ ምህዳሩን ለማስፋት›› እየተባለ ከወህኒ መውጣታቸው፣ የምሕረቱም ይሁን የይቅርታው መንፈስ ያልጎበኛቸው በርካቶች አሁንም በእሥር ላይ መሆናቸው፣ ደግሞም እየተያዙ መታሠራቸው፤ ጥቂት የማይባሉ መገደላቸው፣ ከኖሩበት ቀዬ ቤት ንብረታቸውን ጥለው መፈናቀላቸው፣ ‹‹ከእንግዲህስ ሀገር የለንም!›› እያሉ መሰደዳቸው፣ ሥርዐቱም ‹‹እታደሳለሁ›› እያለ በነበረበት መልክና ቅርፅ እስከ እርጅናው ዘመን ድረስ የመቀጠሉም ጉዳይ፤ በሕጋዊና በዴሞክሲያዊ ጎዳናዎች ላይ ብቻ ላለመጓዙ ዓይነተኛ ማስረጃ መሆኑ አያከራክርም፡፡

በአንፃሩም የሚታሠረው፣ የሚፈናቀለው፣ የሚሰደደው፣ ‹‹በስሕተት ነው›› የሚባለውን ጨምሮ የሚገደለው ሁሉ፤ ‹‹ሕጋዊና ኢ-ሕጋዊነትን›› በማቀላቀሉ፣ ‹‹የፀረ-ሰላምና የአሸባሪ ኃይሎች ተላላኪ›› ሆኖ በመገኘቱ፣ ‹‹የዴሞክራሲያዊ ልማት አቅጣጫን በምትከተለው ሀገሩ ላይ ሠርቶ መለወጥና መክበር›› ባለመፈለጉ፣‹‹በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች ላይ ጥቃት በመሰንዘሩ›› ወይም  በሌሎች ‹‹የአመፅና የሽብር›› የሚባሉ ተግባሮች በመሠማራቱ ነው ብሎ ከአንድ አጠቃላይ መደምደሚያ ላይ መድረስም አይቻልም፡፡

ያም ሆነ ይህ በትላንት የኢትዮጵያ ፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ተጠያቂነት እንደነበረው ሁሉ፤ በዛሬው ፖለቲካዊ ሂደትም ተጠያቂነቱ ይኖራል፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያ  ሥርዐትንና ገዢዎችን የተቃወሙ ዜጎቿን፤ የምታሳድድ፣ የምትገድል፣ የምድር ሲዖል እየሆነችባቸው የምትቀጥል መሆኗ የሚያከትምበት፤ አንድ ሕጋዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዐት በሕዝቧ ፈቃድ ላይ ተመሥርቶ እያበበ፣ እያፈራና እየጎመራ የሚዘልቅባት ትሆን ዘንድ፤ ዛሬ የትክክለኛው ሕጋዊና ዴሞክራሲያዊ መንግሥት መቋቋም መሠረቱ ሊጣልላት የተገባ ነው፡፡

ስለዚህም ያለፉትን ጊዜያት ስሕተቶች አርሞ ለነገ ካለፈው የተሻለ ሕጋዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዐት ለመፍጠር፤ ከመቼውም ይልቅ የተሻለውና የሚመረጠው ብሩህ ቀን ዛሬ ነው እንላለን፡፡ ከእንግዲህ ኢትዮጵያውያን በመወቃቀስና በመካሰስ ሊያባክኑት የሚችሉት ጊዜ አይኖርም፡፡ የሃይማኖት አባቶች የሚያመልኩትን አምላክ ከማክበርና ከመፍራት ባሻገር፤ ስለ ሀገራቸውና ስለወገናቸው ጉዳይ ከማንኛውም አፈ-ሊቅ ፖለቲከኛ ቀደም ብለው ሀገሪቱንና ሕዝቧን ከሁለንተናዊ ጥፋት ለመታደግ ከመጀመሪያው የሰላማዊ ትግል መስመር ላይ መሰለፍ አለባቸው፡፡ አስተዋይ አዛውንቶችና የሀገር ሽማግሌዎችም ከምንግዜውም በላይ አደገኛ ሆኖ የመጣውን ብሔራዊ ችግር ለመቅረፍ የየበኩላቸውን ሚና ሊወጡ የግድ ነው፡፡

በግዮን መጽሔት እምነት ያለፈው እንዳለፈ ሆኖ፤ ከእንግዲህ ጉልቻን በመቀያየርና ‹‹እምቢኝ የእኔ መስመር ብቻ ነው ትክክል›› በሚለው አቋም፤ ለዛሬውም ብቻ ሳይሆን ለመጪው ትውልድ መቅሰፍት ከመሆን የማይመለስ ሆኖ የሚያንዣብብ የሚመስለውን ብሔራዊ ቀውስ መመከት አይቻልም፡፡ የኢሕአዴግ ሰዎችን ጨምሮ ማንኛውም በዚህች ሀገር ላይ ሥልጣን የያዘና ወደ ሥልጣን የሚያልም ፍጡር፤ ኢትዮጵያ ሌሎች ሀገሮች ወደገቡበት የቀውስና የእርስ በርስ ግጭት አረንቋ እንድትገባ ከልብ የሚፈልጉ አይደሉም ብለንም እናስባለን፡፡ ከምንግዜውም በላይ ገዝፎ የሚታየውንና የከረረውን ፖለቲካዊ ውጥረት በኢሕአዴጋዊና በኢሕአዴጋዊ አማራጭ ሐሳብ ብቻ ማስተንፈስ እንደማይቻልም ለመጠቆም እንወዳለን፡፡

ለሁሉም ‹‹ከእኛ ወዲያ ሀገር አመራር ላሳር›› የሚለውና ብሔራዊውን ችግር ከመጥበሻው ወደ እሳቱ የሚመራው የግትረኝነት አባዜ፤ ለነገይቱ ኢትዮጵያ ብሩህ የሆነውን የሕዝባዊ ነፃነት ፋኖስ ሊያበራ አይቻለውም፡፡ የ‹‹አትንኩን›› ባይነት ስሜትም ቢሆን የብዙኃኑን ነፃነትና መብት እንዳሻቸው እየተጋፉ መቀጠልን ለሚሹ ወገኖች አይበጃቸውም! የሚለው መልእክታችን ሲሆን፤ ኢትዮጵያችን ሁሉንም ተቃዋሚ ወገኖች ባሳተፈ የዕርቅና የወንድማማችነት መንፈስ ወደ ሕጋዊና ዴሞክራሲያው ሥርዐት ዛሬ ነገ ሳትል እንድትሸጋገር መፈለጋችንም የመልእክታችን መነሻ ነጥብ ነው፡፡


**ጥቅምት 2010 ዓ.ም ተመሠረተ**
**ኢትዮ ሐበሻ ሕትመትና**
**ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር**
**በየ 15 ቀኑ ለሕትመት**
**የምትበቃ መጽሔት**

ማኔጂንግ ዳይሬክተር
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

ዋናአዘጋጅ
ፍቅር ሠይድ
አድራሻ፡- አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 7
የቤት ቁጥር 314

አዘጋጆች
ሠሎሞን ለማ
ሮቤል ምትኩ
ብሩክ መኮንን

አምደኞች
አበበው አያሌው
ቴዎድሮስ ተ/አረጋይ
ተረፈ ወርቁ
መስፍን ጌታቸው
ሁሴን ከድር
በሀይሉ ገ/እግዚአብሔር

ክርኤቲቭ ዲዛይን
መስፍን አድነው

የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09
የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 5ተኛ
ፎቅ ቢሮ ቁ. 501
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 951693
ኢ-ሜይል፡
Gihon2010meg@gmail.com
Facebook
Gihon meg

አታሚ
ለታሪክ ማተሚያ ቤት
ስልክ ቁጥር፡ 0911 51 55 68
በሌ ክ/ከተማ ወረዳ 04
የቤት ቁጥር 504/ሀ



አበባው አያሌው

# ሁነኛ መሪ ጠፋ!

እስካሁን ካለው የሰው ልጅ ታሪክ እንደምንረዳው ለአንድ አገር መልማትም ሆነ መጥፋት መሠረቱ ሕዝብ ነው። በየትም አገር መንግሥት ብቻውን ዳክሮ ያሳደገው ኢኮኖሚ፤ የገነባው አስተማማኝ ሥርዐት፤ ያሰፈነው ዲሞክራሲ ወዘተ… የለም። የሁሉ ነገር ቁልፍ ሕዝብ ነው። ነገር ግን ሕዝብ ደግሞ የለውጥ መሠረት ይሆን ዘንድ መሪ ያስፈልገዋል። መሪ ሲባል እንዲያው ሹመትና ስሙን የሚይዝ ሳይሆን፤ ሕዝብ "የእኔ ነው" ብሎ የሚቀበለው መሪ ሊሆን ይገባል። እንዲህ አይነት ሁነኛ መሪ ተቀባይነቱን፣ ዕውቀቱን፣ ብልሃቱን ተጠቅሞ ሕዝብን በማስተባበርና አቅጣጫ በማሳየት አገርን ወደ ተሻለ ደረጃ ሕዝብን ወደሚጠቅም የኑሮ ሁኔታ ይመራል። መሪና ሕዝብ ሲገናኙ አገር ይለወጣል። ዕውቀትና ጥበብ ይስፋፋል። ጠፍ የሆነ ነገር ሁሉ ይለማል፣ ይበለጽጋል። እንዲህ የሚያደርግ "መሪ" ይባላል። ነገር ግን ሹመትና ስሙን ብቻ ይዞ ለውጥ የማያመጣ "ገዛ" እንጅ "መራ" አይባልም።

ኢትዮጵያ በየዘመኑ በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች ጥሩም መጥፎም መሪዎች አጋጥመዋታል። ጥቂት በማይባሉ ጥሩ መሪዎች አገሪቱ ይብዛም ይነስም እድገት አሳይታለች። ይሁን እንጂ ከ1966ቱ አብዮት በኋላ አገሪቱም ሆነ ሕዝቧ ለቦታውና ለወቅቱ የሚመጥን መሪ አጥታለች። ሁነኛ መሪ በማጣቷ ምክንያት ከፍተኛ የፖለቲካ የኢኮኖሚና የማኀበራዊ ቀውስ ኪሳራ ገጥሟታል። አሁን ከምንገኝበት ውጥንቅጥ ላይ ሆነን ስንመለከት ለወደፊትም ተስፋ ያለን አይመስልም። ምክንያቱ ምንድን ነው? ምንስ ይሻላል? ይህችን አጭር ጽሑፍ ያዘጋጀሁበት ዋና ምክንያት በእነዚህ ሁለት ጥያቄዎች የበኩሌን ምልከታ ለአንባቢ ለማካፈል ነው።

የ1966 ዓ.ም አብዮትና ተከትሎት የመጣው የሶሻሊዝም ርእዮተ ዓለም በአገራችን አዲስና ባይተዋር የሆነ የፖለቲካ ባሕልና ሥርዐት ፈጥሯል። የሶሻሊዝም ርእዮተ ዓለም ከመነሻው የተጨቆነን መደብ ወይም የኅብረተሰብ ክፍል የሥልጣን ባለቤት ማድረግን ግቡ ያደረገ ርእዮተ-ዓለም ነው። ሕዝብን የሥልጣን ባለቤት ማድረግ ዓላማውም ግቡም አይደለም። የንድፈ ሐሳብ ፍልስፍናውን እንተወውና እ.ኤ.አ ከ1917 ጀምሮ የሶሻሊዝም ሥርዐት ወደ ተግባር ሲለወጥ ጥቂት ቡድኖች ተደራጅተው መሰሎቻቸውን ደግሞ በተዋረድ አደራጅተው ሥልጣን ይይዛሉ።

በዚህ የፖለቲካ ስልት ሕዝብ የሚወደው፣ የሚፈልገውና ለቦታውም ሆነ ለኃላፊነቱ የሚመጥን መሪ ወደ ሥፍራው አይመጣም። በሩሲያ የተጀመረው የሶሻሊዝም ርእዮተ ዓለምን መተግበር ለሌሎች የርእዮተ ዓለሙ ተከታይ አገሮች በተለያየ ጊዜ ያወረሰው የፖለቲካ ባሕል "ቦልሸቪዝም (Bolshevism)" ነው።

ቦልሸቪዝም ጥቂት "የተጨቋኝ ወይም የጭቁን ሕዝብ ወኪል ነን" የሚሉ ግለሰቦች ተመራርጠው ሥልጣን በመያዝ እልፍ አእላፍ የካድሬ ሠራዊት አሰልፈው ሕዝብ የሚመዘብሩበት ሥርዐት ነው እንጂ ሕዝባዊ የፖለቲካ ሥርዐት አይደለም። ለምን ቢሉ ሲጀመር ተቧድኖ ከፍተኛውን የመንግሥት ሥርዐት የያዘው አካል ሕዝብ ሳይመርጠው በአብዮት ስምም ይሁን በሌላ አጋጣሚ የሥልጣን ኮርቻውን ከያዘ በኃላ ለራሱ የሚመች ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ፣ ምርጫ ወዘተ… እያወጣና እያካሄደ እንዳይወድቅ እርካብና ልጓሙን ጠበቅ አድርጎ ይይዛል። በሥሩ ያለው የካድሬ ሠራዊት ሕዝብ የመረጠው ሳይሆን በታማኝነት፣ በአኅብዳጅነትና በአድርባይነት መስፈርቶች የተመለመለ ተውሳክ ነው። እስካሁን በታየው የሶሻሊዝም ተሞክሮ ካድሬ ተጠሪነቱና ታማኝነቱ ለመለመለውና ለአደራጀው ፓርቲ እንጂ ለሕዝብ አይደለም።

በአጭሩ በሶሻሊስታዊ ርእዮተ ዓለምና በቦልሸቪስት ትውፊት የተዋቀረ ሥርዐት ሕዝባዊ አይደለም። ሊሆንም አይችልም። ለሕዝብና ለአገር የሚበጅና የሚመጥን መሪም ወደ ሥልጣን ሊያመጣም አይቻለውም።

በአገራችንም ከአብዮቱ በኋላ የመጣው የፖለቲካ ሥርዐት ሕዝብና መንግሥትን ሊያገናኝ ያልቻለውና ሁነኛ መሪ መፍጠር (ማፍራት) ያልቻለው በቦልሸቪዝም የፖለቲካ ትውፊት የተቃኘ በመሆኑ ነው። በዘመነ ደርግ ከሠራዊቱ የተውጣጣ ዐሥር አለቃና ሃምሳ አለቃ ተመራርጦ ከፍተኛውን የመንግሥት ሥልጣን በእጁ አደረገ። ቀጥሎ ከወታደሩና ከምሁሩ ክፍል የሆነ ካድሬ አደራጅቶ ለሕዝብ ሳይሆን ለራሱ ህልውና የሚጠቅም ሥርዐት ፈጠረ። ካድሬውም የበላይ ባለሥልጣናቱም የልሂቃንና በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ግለሰቦች ዋነኛ ጠላት ሆኑ። በህዝብ መወደድ ለህዝብ መናገርና መቆም የልሂቅነት ሚናን መጫወት የሥርዐቱ ጠላት እንደመሆን ተቆጠረ። እንዲህ ባለ ሥርዐት ሕዝባዊ መሪ ሊፈጠር ይቅርና የነበረውም ጠፋ።

> **"የኢሕአዴግ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ሕዝብን ወይስ ድርጅትን ነው የሚያስቀድሙት?" ብለን ብንጠይቅም "ድርጅትን" እንደሆነ አያጠራጥርም። "ድርጅቱ ሕዝባዊ ነው ወይ?" ብለን ብንጠይቅ ደግሞ በአመዛኙ አይደለም...**

ከደርግ ውድቀትና ከኢሕአዴግ የሥልጣን ልደት በኋላም የተቀየረ ነገር የለም። መጀመሪያም ቢሆን የኢሕአዴግ ርእዮተ ዓለማዊ ጥንስስ ብቅልና ደረቆቱ ሶሻሊዝምና ቦልሸቪዝም ነው። ወደ ሥልጣን ሲቃረብ ወደ ነፃ ኢኮኖሚና መድብለ ፓርቲ ሥርዐት ለውጥ አድርጊያለሁ ቢልም በተግባር ግን ከቦልሸቪዝም ውርዴ አልተላቀቀም። ይህን ለማረጋገጥ ብዙ ሁነኛ አብነቶችን መጥቀስ ይቻላል። ጠቅለል ብለው ሲቀመጡ ግን ሁለት ናቸው።

አንደኛው የመድብለ ፓርቲ ሥርዐትን በሕገ-መንግሥቱ አውጆ ብሔራዊም ሆነ አገራዊ ፓርቲዎች ተመሥርተው እንቅስቃሴ ሲያደርጉና በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነትን ሲያገኙ በሆነ ባልሆነ ምክንያት እያሰናከለ የራሱን የሥልጣን ዋስትና ማስከበሩ ነው። ከፓርቲዎች በበረታ መልኩ የዚህ ድርጊት ዋነኛ ሰለባ የሆኑት ፓርቲዎችን የሚመሩ ሕዝባዊ ግለሰቦችና ልሂቃን ናቸው።

ሁለተኛው በኢሕአዴግ አባልና አጋር ድርጅቶች ውስጥ ከፍተኛ የመንግሥት ሥልጣን ያላቸው ግለሰቦች ሕዝባዊነትና ተቀባይነት እንዳይኖራቸው ማድረጉ ነው። አስቀድሞ እንደተጠቀሰው አንድ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ፓርቲ የመለመለው ሰው ታማኝነቱና ወገንተኝነቱ ለሕዝብ ይሆናል ብሎ ማመን አስቸጋሪ ነው። "የኢሕአዴግ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ሕዝብን ወይስ ድርጅትን ነው የሚያስቀድሙት?" ብለን ብንጠይቅም "ድርጅትን" እንደሆነ አያጠራጥርም። "ድርጅቱ ሕዝባዊ ነው ወይ?" ብለን ብንጠይቅ ደግሞ በአመዛኙ አይደለም። ነገሩ እንዲህ ከሆነ ከዚህ ድርጅት ሕዝባዊ መሪ ሊወጣ ወይም ሊፈጠር ይችላል ወይ? በእኔ አመለካከት ሊፈጠር አይችልም። ሊፈጠር የሚችለው የድርጅቱ መሪዎች ጥብቅና ብሎም ታማኝነት ከድርጅቱ በላቀ ሁኔታ ለአገርና ለሕዝብ ሲሆን ነው። የአገርና ሕዝብ ጥያቄና ቋንቋም የድርጅቱ ጥያቄና ቋንቋም ሊሆን የግድ ነው።

በኢሕአዴግ የፖለቲካ ባሕል በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያለው መሪ ሊፈጠር የማይችልበት ሌላው ምክንያት ድርጅቱ "ፖፑሊዝም (Populism)" እያለ የሚያቆላምጣት የግምገማ ወጥመድ መኖሯ ነው። የሕዝብን ጥያቄ አንሥተው የሚከራከሩ በሕዝባቸው ዘንድ ሰፊ ተቀባይነት ያገኙ ፖለቲካዊና ሰዋዊ ስብዕናቸው ከፍ ብሎ የሚታዩ ብሎም አገርና ሕዝብን በተገቢው መንገድ የመምራት ብቃት የሚታይባቸው ከፍተኛ የአመራር አባላትን ማሰናከያ ወጥመድ ኢሕአዴግ "ፖፑሊዝም" ብሏታል። የፖፑሊዝም ትክክለኛ የፖለቲካ ትርጉም የተራውን ሕዝብ ጥያቄ፣ መብት፣ ጥቅም ወዘተ… መሠረት ያደረገ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ነው።

አንድ የፖለቲካ ሰው "ፖፑሊስት ነው" ከተባለ ለሕዝብ ጥብቅና ቆሟል ማለት ነው። ፍቺው ይህ ከሆነ ዘንዳ አንድ ሰው እንደ መጥፎ ነገር ተቆጥሮበት እንዴት ይገመገምበታል? የኢሕአዴግ ሕዝባዊ ወገንተኝነት መለካትም ካለበት ከዚህ አንፃር መሆን ይገባዋል። ኢሕአዴግ ድርጅትንና የካድሬ አደረጃጀትን ሙጥኝ ብሎ እስከ ተጓዘ ድረስ ለሕዝብና ለአገር የሚመጥን መሪ የማፍራት አቅም ይኖረዋል ብዬ አልገምትም። በተግባር እያየን ያለውም ይህንኑ ነው። ይህን ባሰላሰልኩ ቁጥር በኀሊናየ የሚመጣው የስመጥሩ አዝማሪና ዘፋኝ የባሕሩ ቃኘ:-

"… ኧረ ደሴ ደሴ … ደሴ ደረቅ ወይራ ገራዶ ቢለን፣
የስንቱ መወከል ለከፈኝ እኔን።
እንኳን "ቀጭን ፈታይ" እንዝርቷን አራቂ፣
እንኳን መልካም ወላጅ ልጇን አስደላቂ፣
የማታጠራጥር ንግግር አዋቂ፣
"ሰው ያረበርባል" ለንፍሮ አንፈቅፋቂ።
እስኪ ባዳራሹ በእልፍኙ ዝለቂ፣
ምን አረንዛ ሆድ ነሽ ሰው የማትናፍቂ።…"

ትዝ ይለኛል።

ጥሎብን ለቀጭን ፈታይ ሳይሆን ለንፍሮ አንፈቅፋቂ ሸብረብ እያልን እናረበርባለን።

# አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር

## በስሌት ወይስ በድንገት?

ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ የሥልጣን መልቀቂያ ደብዳቤ ማስገባታቸውን በይፋ ለሕዝብ ከተናገሩ ማግስት ጀምሮ በሀገሪቱ ውስጥ ቀጣዩ ጠቅላይ ሚኒስትር ማን ይሆናል የሚለው ጥያቄ ሳምንታት የዘለቀ መወያያ ጉዳይ ሆኖ ሰንብቷል። በውስጥ ለውስጥ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ይህንን የሀገሪቱን ከፍተኛ የሥልጣን እርከን ለመቆናጠጥ ከፍተኛ ሽኩቻ ላይ ሰንብተው መክረማቸውን ነው ይፋዊ ያልሆኑ መረጃዎች የጠቆሙት።ፓርቲው ከዚህ ቀደም ኃይለማርያም ደሳለኝ ወደ ሥልጣን ሲመጡ ተጠቅሞበት እንደነበረው ዓይነት ከአባላቶቹ መካከል ብቁ ነው፣ ለዚህ ወንበር ይመጥናል የሚለውን ሰው የሚሾምበትን አሠራር አስቀርቶ አራቱም የግንባሩ አባል ድርጅቶች የየራሳቸውን እጩ አቅርበው በምስጢር ድምጽ አሰጣጥ በሚካሄድ ምርጫ ተረኛው ጠቅላይ ሚኒስትር ማን እንደሆነ የሚታወቅበትን አሠራር መዘርጋቱንም እንዲሁ ይፋ አድርጎ ነበር። ይህ የአሠራር ለውጥ ደግሞ በፓርቲዎቹ መካከል የሥልጣን ይገባኛል ሽኩቻ ተነሥቶ እንደነበርና ግንባሩንም ይህንን ለመፍታት የጠቅላይ ሚኒስትር ሹመት ሂደቱን በምርጫ ማከናወን ብቸኛ መፍትሄ አድርጎ እንዲይዝ ያደረገው መሆኑን የሚጠቁም ነው ይላሉ የፖለቲካ አዋቂዎች።

ኦህዴድ ከውስጥና ውጪ ከገጠመው ግፊትና ድርጅቱ በሚመራው ሕዝብ ብዛትና የቆዳ ስፋት ልክ የሥልጣን ውክልናውን ከፍ ለማድረግ በሚመስል መልኩ ቦታውን ለመያዝ የሚረዳውን ለጠቅላይ ሚኒስትርነት የሚያበቃ መመዘኛ ለማሟላት ሲል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የሆኑትን ዶክተር ዐብይ አህመድን የድርጅቱ ሊቀመንበር አድርጎ በመሾምና የምክርቤት አባል ያልሆኑትን አቶ ለማመገርሳን ምክትል አድርጎ በማስቀመጥ የሥልጣን ሽግሽግ አድርጎ እጩውን ለይቶ አሳውቋል። ይህም ለውጥ ለውጥ በሚሸት ንግግራቸው የብዙሃኑን ቀልብ የሳቡት ዶክተር ዐብይ አሕመድ በብዙዎች ዘንድ ለዚህ ቦታ የተጠበቁ ሰው ከመሆናቸው ጋር በተያያዘ ድርጅቱ ቦታው ለርሳቸው ይገባል የሚል አቋም ይዞ መነሣቱን የሚያመለክት ፍንጭ ነበር።

ኢህአዴግ በቆየ ታሪኩ የሚያስተላልፋቸው ውሳኔዎች ሁሌም ከተጠበቀው ይልቅ ባልተጠበቀው መንገድ ብቅ የሚሉ 'ሰርፕራይዞች' መሆናቸው የተመለደ ነገር ቢሆንም በአብዛኛው የፖለቲከኛ ተንታኞችም ይሁን እና ተራው ዜጋ ዘንድ ግን የኦህዴዱ ዶክተር ዐብይ አህመድ በዚህ የሥልጣን እርከን ላይ የሚቀመጡ ተረኛው ጠቅላይ ሚኒስትር ይሆናሉ የሚል ከፍተኛ ግምት የተሰጣቸው ሰው ነበሩ። ዶክተር ዐብይ ወደዚህ ወንበር እንዲመጡ የብዙሃኑ ፍላጎት የሆነበት ምክንያት ከኦሮሚያ ሕዝብ የሥልጣን ውክልና ጥያቄ ግፊት አንጻር ብቻ ሳይሆን፤ ከሰውየው ሰብዕና እና የተገራ አንደበት እንዲሁም በብዙሃኑ ዘንድ የማይፈለገውን ዘረኝነትና ጠባብ አስተሳሰብ በተግባር ሲዋጉ የቆዩ ሚዛናዊ ፖለቲከኛ ከመሆናቸው ጋር በተያያዘም ጭምር ነው።

በተለይም "በሕወሓት ጎራ አካባቢ ሰውየው ወደዚህ ወንበር እንዲመጡ አልተፈለገም" የሚል መረጃ መናፈሱና በተጨባጭም በማኅበራዊ ሚዲያዎች የዚሁ ድርጅት አባላት የሆኑ አክቲቪስቶች በሰውየው ላይ የሚያሰራጯቸው ጥላቻ የተሞሉ ጽሑፎች ጭምር ብዙሃኑ ሕዝብ የዶክተር ዐብይን ወደ ሥልጣን መምጣት አጥብቆ እንዲፈልገው ምክንያት ሆኗል የሚሉም አሉ። ዶክተሩ አሜሪካ በሄዱበት ወቅት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ በአሜሪካ በኩል ተሰሚነት ያለው አስተያየት በማቅረብ የሚታወቁትና ከ1989 እስከ 1993 ድረስ በአሜሪካን የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የአፍሪካ ጉዳዮች ኃላፊ በመሆን ያገለገሉት የ38 ዓመታት የዲፕሎማሲ ልምድ ያላቸው አምባሳደር ኸርማን ኮህን ድጋፍ የተቸራቸው፣ ከዚህም አልፎ አምባሳደሩ በአሜሪካ ድምፅ ራዲዮ ቀርበው "ዶክተር ዐብይ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር መሆን አለበት" አይነት ገለጻ መስጠታቸው በራሱ ዶክተሩ ተተኪ ጠቅላይ ሚኒስትር ሊሆኑ እንደሚችሉ አስቀድሞ ግምት እንዲሰጥ ያደረገ አንድ ምክንያት ነበር። (እዚህ ጋር በአቶ መለስ ሞት ማግስት አሜሪካ ለቦታው አቶ ኃይለ ማርያምን መሻቷን ፕሬዚዳንት ኦባማ ከሰውየው ጋር ባደረጉት የቀጥታ ስልክ ውይይት እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሯ ሱዛን ራይስ በተመሳሳይ ከርሳቸው ጋር በአካል ተገናኝተው ያደረጉት የዝግ ውይይት በጊዜው ጠቋሚ ምክንያት ሆኖ መገለጹን ልብ ይሏል)

በሌላ በኩል ብአዴን ለጠቅላይ ሚኒስትርነቱ ቦታ አቶ ደመቀ መኮንንን አጭቶ ማጨቱ ሰውየው ከ2005 ጀምሮ ካገለገሉበት የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርነት ቦታ አንጻር ተገቢና ቅቡልነት ያለው አሰራር ቢሆንም በአብዛኛው የክልሉ ተወላጆች ዘንድ ያላቸው ተቀባይነት አናሳ ከመሆኑ አንጻር፣ እንዲሁም ብዙዎች የግለሰቡን ተጽዕኖ ፈጣሪነት የሚጠራጠሩት ከመሆኑ አኳያ ፣ ለቦታው ቢመረጡ እንኳን አቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ አልፈውበታል ከሚባለው ቦታ አሟቂነት (place holder) የተለየ ሚና የማይጫወቱ ናቸው ተብሎ በብዙሃኑ ዘንድ ከመታመኑ ጋር ተያይዞ ለቦታው የተሰጣቸው ግምት ሚዛን የሚደፋ አልነበረም።

...“ለ27 ዓመታት የታፈኑ የለውጥ ጥያቄዎች መፈንዳት በጀመሩበት በዚህ ጊዜ ኢህአዴግ በአባል ግለሰብም ይሁን በፓርቲ ደረጃ ለውጥ ለውጥ መሽተት ካልቻለ ከሁሉም የከፋው አደጋ በራሱ ላይ የሚከሰተው የመሰነጣጠቅና የመበታተን አደጋ ነው”...

በአንጻሩ ደኢህዴን ያካሄደውን ስብሰባ ካጠናቀቀ በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትር ሃይለማርያም ደሳለኝን ከድርጅቱ ሊቀመንበርነት ማሰናበቱን ገልጾሲራጅ ፌጌሳን አዲስ ሊቀመንበሩ አድርጎ መምረጡን በፌስቡክ ገጹ ባሳወቀበት ቅጽበት ወዲያውኑ "የፌስቡክ ገጼ ሃክ ተደርጎ ነው" ብሎ በሰጠው ይፋዊ መግለጫው ያልተጠበቁትን አቶ ሽፈራው ሽጉጤን ሊቀመንበሩ አድርጎ መሾሙን አስታውቋል። በዚህ ስሌት አቶ ሽፈራውም በስሌት ወደ ውድድሩ እንዲመጡ የተደረጉ ደቡብን ወክለው ለጠቅላይ ሚኒስትርነት የሚወዳደሩ እጩ በመሆን ውድድሩን እንዲቀላቀሉ ተደርጓል። ብዙዎች ይህንን አካሄድ "ህወሃት በእጁ ያለውን አርባ ካርድ ለማን ሊሰጥ እንደፈለገ ከወዲሁ የገለጸ አመላካች ነው" በማለት ወደርግጠኝነት ያደላ ቅድመ ግምታቸውን ሰንዝረውን ነበር።

በሌላ በኩል ይህ መጽሄት ህትመት እስከገባበት ጊዜ ድረስ ከግንባሩ አባላቶች መካከል ህወሃት ለጠቅላይ ሚኒስትርነት የሚወዳደር እጩ አለማቅረቡ ሲነገር የነበረ ሲሆን አልፎ አልፎ የሚወጡ መረጃዎችን ተንተርሰው ግምታቸውን የሰጡ ታዛቢዎች ደግሞ ህወሃት ዶክተር ደብረጽዮንን የድርጅቱ ሊቀመንበር አድርጎ ከመሾሙ ጋር አያይዘው ዶክተሩ ፓርቲውን ወክለው ለዚህ ወንበር የሚወዳደሩ እጩ ሆነዋል ብለው ነበር ። በጊዜው ጉዳዩን በቅርበት በሚከታተሉ የፖለቲካ እና መገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች ዘንድ ግን ይህ መረጃ ከግምት እንጂ ከነባራዊ እውነት ጋር ተዛምዶ የለውም በሚል ተቀባይነት አላገኘም። ምክንያቱ ደግሞ ደብረጽዮን ለጠቅላይ ሚኒስትርነቱ ቦታ ቢወዳደሩ አሸነፉም አላሸነፉ በተቃዋሚዎቹ ዘንድ "ህወሃት ይህንን ቦታ ላለመልቀቅ የሚሟሟት ድርጅት ነው" የሚል መደምደሚያ ስለሚያሰጠውና" ተጠናውቶታል የሚባለውን የስልጣን ጠቅላይነት ፍላጎት ስለሚያጎላበት "ድርጅቱ ይህንን እሰጥአገባ ላለመጋፈጥ ራሱን ከምርጫ ማግለል አማራጭ አደርጓል የሚል ነው። በርግጥም ህወሃት በብዙዎች እንደተተነበየው በእጁ ያለውን 40 ድምጽ (አምስቱን አባላቱን በተለያየ ምክንያት በማሰናበቱ ) ብሄራዊ ድርጅቶቹ ከሚያቀርቧቸው ሶስት እጩዎች ለፈለገው አንድ እጩ ሰጥቶ በተዘዋዋሪ የርሱ ምርጫ የሆነውን ሰው ወደ ስልጣን ለማምጣት ተዘጋጅቷል ተብሎ ተጠብቆም ነበር።

በዚህ መልክ የስልጣን ፉክክሩ ጦዞ የተጀመረው የፓርቲው የስራ አስፈጻሚ ምክር ቤት ስብሰባ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ምርጫ ቀዳሚ አጀንዳው እንዳልሆነ በመግለጽ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ አተገባበር፣ በሃገሪቱ ፖለቲካ ሁኔታ እና በኮማንድ ፖስቱ ሃላፊነት አፈጻጸም ላይ ግምገማ ሲያደርግ ሰንብቷል። ይህ ስብሰባ ቀነ-ገደብ ያልተበጀለት ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ከተጠበቀው ጊዜ በላይ ወስዷል። ይህም ኢህአዴግ ለ 17 ቀናት ሲያደርግ ከቆየው ጉባኤ ባልተናነሰ በዚህ የስራ አስፈጻሚ ስብሰባም ዘንድ ከባድ ንትርክ አስተናግዶና በብሄራዊ ድርጅቶቹ መካከል ያለውን አለመግባባት ለማጥበብ ፈታኝ ጊዜ አሳልፎ እንደነበር ያመለክታል ይላሉ ታዛቢዎች።

ለማንኛውም በጉጉት ሲጠበቅ የነበረው ኢህአዴግ ሊቀመንበርነትና የጠቅላይ ሚኒስትርነት "ማን መሆን " ጉዳይ በኢትዮጵያውያን ዜጎችና በአለም አቀፍና ሃገር አቀፍ ድርጅቶች ዘንድ የተለያየ ቅድመ ትንበያና አስተያየት ያስተናግድ እንጂ ውሎ አድሮ አንድ ሰው ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ መምጣቱ አልቀረም። ይህንን ተከትሎም በሚቀጥሉት ጊዜያት የድጋፍና የተቃውሞ ድምጾች ከዚህም ከዚያም መሰማታቸው አይቀሬ ነው። የተቃውሞም ይሁን የድጋፍ ቀዳሚ ምክንያቱሃገራዊ ሳይሆን ድርጅታዊ አለያም ብሄራዊ ፍላጎት እንደሚሆን መገመት አዳጋች አይሆንም። ምክንያቱም ሁሉም ወደዚህ ስፍራ እንዲመጣለት የሚፈልገው በቅድሚያ የያዘውን ፖለቲካ የሚያስቀጥልለትና ዘላቂ ጥቅሙን የሚያስከብርለት ሰው መሆኑ ነው።

ለመሆኑ ኢህአዴግ ሃይለማርያምን ለምንና

በምን መልክ ነበር ወደ ስልጣን ያመጣቸው? አሁን አዲስ የሾመውን ጠቅላይ ሚኒስትር ከዚያ በተለየ መልክ ወንበር እንዲይዝ ፍላጎት አለው ይሆን? ይህንን ለመመዘን በቅድሚያ ከአቶ መለስ ሞት በኋላ የተካሄደውን የጠቅላይ ሚኒስትር ምርጫ ማየት ተገቢ ይሆናል።

ኢህአዴግ በ2004 ዓ.ም ነሀሴ ወር ላይ የቀድሞ ሊቀመንበሩንና የሃገሪቱን ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ዜና ህልፈት ይፋ ካደረገበት ቀን ጀምሮ ያልተጠበቀ ነው ከተባለው የጠቅላይ ሚኒስትሩ አሟሟት ባላነሰ በሃገር አቀፍ ደረጃ አነጋጋሪ የነበረው ጉዳይ ልክ እንደዛሬው "በርሳቸው እግር የሚተካ ጠቅላይ ሚኒስትር ማን ይሆናል? "የሚለው ጥያቄ እንደነበር አይዘነጋም።

መለስ ዜናዊ 21 ዓመታት ወንበራቸውን ሳይለቁ የሃገሪቱን ስልጣን ጠቅልለው ይዘው የኖሩ ወሳኝና ባለከባድ ሚዛን ፖለቲከኛ መሆናቸው በራሱ በብዙሃኑ ዘንድ "ከድርጅቱ ውስጥበርሳቸው እግር ተተክቶ ሃገር ለመምራት ብቃት ያለው ሌላ ሰው ማነው?" የሚል ጥያቄ እንዲነሳ አድርጎታል።ይህንን ጥያቄ ለመመለስ እንኳን ውጭ ያለው ታዛቢ ቀርቶ ራሱ ኢህአዴግም አንድ ወር ያህል አምጧል።

ኢህአዴግ አቶ መለስ ዜናዊ እንደሞቱ በመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ሚኒስትሩ አቶ በረከት ስምዖን አማካኝነት በሂልተን ሆቴል ለተገኙ ጋዜጠኞች መግለጫ ሲሰጥ "ተተኪው ጠቅላይ ሚኒስትር ማን ይሆናል?" የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር።አቶ በረከት በወቅቱ የሰጡት መልስ ሰሞኑን የኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚ ስብሰባ ሲጀመር በሚዲያ ቀርበው ከሰጡት መግለጫ ጋር በይዘትም በሃሳብም ተመሳሳይ ነበር። "የመሪያችንን አስከሬን አስቀምጠን ስለምርጫ አናወራም።አንድ ሰው መምረጥ ከጓዶች መሃል ለላቀ መስዋዕትነት አንድ ሰው ከመሰየም በዘለለ ፓርቲውን የሚያስጨንቀው ጉዳይ አይደለም" ነበር ያሉት።

ኢህአዴግ አንድ ወር ፈጅቶ የስራ አስፈጻሚ ምክርቤቱን እስኪሰበስብና በመለስ እግር ተክቼዋለሁያለውን ሰው መርጦ እስኪያሳውቅ ድረስ ሃይለማርያም ደሳለኝ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነታቸው ጋር ደርበው የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ቦታ በተጠባባቂነት እንዲመሩት ቢያደርግም በቋሚነት ወንበሩ ላይ ማን ይቀመጣል በሚለው ጉዳይ ላይ ያልተሰጠ ትንታኔ አልነበረም ማለት ይቻላል።

ሃይለማርያም ደሳለኝ በመለስ ዜናዊ ትዕዛዝ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት የማህበራዊ ጉዳዮች አደረጃጀት አማካሪ ሆነው ወደ ፌዴራል ከመዛወራቸው በፊት የደኢህዴን ሊቀመንበርና የደቡብ ክልል ርዕሰ መስተዳድር የነበሩ ሲሆን መለስ ወደርሳቸው የሳቧቸውም ለጊዜው ግልጽ ባልሆነ ምክንያት ከክልል ፕሬዚዳንትነት ስልጣናቸው መልቀቂያ ጥያቄ ማቅረባቸውን ተከትሎ ነው።

የፖለቲካ ተንታኞች እንደሚናገሩት ኢህአዴግ በ2003 ዓ.ም አዳማ ላይ ባደረገው የግንባሩ ጉባዔ ላይ ባሳለፈው ውሳኔ መሰረት ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጀምሮ በትጥቅ ትግሉ ተሳትፎ የነበራቸውን ጎምቱ ባለስልጣናቱን ሙሉ በሙሉ በአዲሱ ሃይል የመተካት እቅድ ይዞ ነበር።መለስ ዜናዊም ራሳቸው በ2007 ሊካሄድ የታቀደውን ሃገራዊ ምርጫ ተከትሎ ራሳቸውን "ጡረታ የማውጣት" ዕቅድ ነበራቸው።በዚህ መሰረትም ተተኪና ብቁ ልምድ ያላቸውን አመራሮች ወደፊት ለማምጣት ያስችላል ያሉትን እድቅ በማውጣት ይህንኑ መተግበር ጀምረው ነበር።የትጥቅ ትግሉ ዘመን ሰው ያልነበሩት ነገር ግን ከአዲሱ የኢህአዴግ ትውልድ የሚመደቡት የውሃና ሳኒቴሽን መሃንዲሱ አቶ ሃይለማርያም ደሳለኝ ከክልል ወደ ፌዴራል የመምጣታቸው ምክንያትም ይኸው ነበር።አቶ መለስ ህወሃት በሞኖፖሊይዞት የቆየውን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ቦታ ለሃይለማርያም ሲሰጡና ሰውየውን "ለኢህአዴግ አላማዎች መፈጸም ቁርጠኛ አቋም ያለው" ብለው በአደባባይ ሲያደንቋቸው በፓርቲው ዘንድ ቀድሞም ለጠቅላይ ሚኒስትርነት የታጩ ሰው እንደነበሩ፣ በተቃዋሚዎች ዘንድም "ህወሃት ከኋላ ሆኖ የሚዘውራቸው አሻንጉሊት ባለስልጣን" ማግኘቱን ያረጋገጠ ፍንጭ ሆኖ ነበር።

በመጨረሻም ከአንድ ወር በኋላ 170 አባላቱን ይዞ ስብሰባ የተቀመጠው የኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚ ምክር ቤት የአዲሱ ትውልድ አባላት ናቸው የተባሉትን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩንና የደኢህዴን ሊቀመንበሩን ሃይለማርያም ደሳለኝን፣የትምህርት ሚኒስትሩንና የብአዴን ሊቀመንበሩን ደመቀ መኮንንን እንዲሁም በወቅቱ ማንነታቸው ያልተገለጸ (ውስጥ አዋቂዎች እንደሚናገሩት የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩን ሶፊያን አህመድን ) እጩ በማድረግ ምርጫ አካሂዷል። በዚያ ምርጫም ለሃይለማርያም ከ170 ድምጽ 151 በመስጠት ጠቅላይ ሚኒስትር ሲያደርግ ደመቀ መኮንንና ያልታወቁት እጩ 19 ነጥብ በጋራ ተጋርተው አቶ ደመቀ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ተሹመዋል።

ኢህአዴግ በሚከተለው የብሄር ፖለቲካ መሰረት ስልጣን ሁሌም ከጠቅላዩ ህወሃት እጅ ከወጣ ቅድሚያ የሚሰጠው ለችሎታና ብቃት ሳይሆን ለብሄር ውክልና ነው። የመለስን ሞት ተከትሎ "ተተኪው ጠቅላይ ሚኒስትር ማን ይሆን ?" የሚሉ ጥያቄዎች ሲነሱ በብሄራዊ ድርጅቶቹ መካከል ለወንበር የተካሄደ ፍትጊያ መኖሩን ብዙዎች ይስማሙበታል።ይህም ፓርቲው በመደበኛ ደረጃ ስብሰባ አካሂዶ የሃገሪቱን ጠቅላይ ሚኒስትር በይፋ ለመሾም ሶስት ወራት እንዲፈጅ አድርጎታል።በዋናና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ መካከል ያለው የድምጽ ብልጫ የፈጠረው ሰፊ ልዩነት "ምርጫው ለይስሙላ የተካሄደ ነው" ለሚል ድምዳሜ በር የከፈተ ነበር።

በአካሄዱ መሰረት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩን አቅርቦ ሹመት የሚያስጸድቀው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሆንም በዚያን ወቅት ፓርቲው ለህግና ደንብ ቦታ አልነበረውምና ሁለቱንም እንደ የደረጃቸው መሾሙን በመግለጽ በምክርቤት አስጸድቋል።ይህ ብቻ ሳይሆን ሃይለማርያም ህግ በሚሰጣቸው ስልጣን መሰረት ነባሩን የመለስ ካቢኔ ሳይበትኑና የራሳቸውን አዲስ ካቢኔ ሳያዋቅሩ ወራትን መሻገራቸው ብቻ ሳይሆን በሹመታቸው ዕለት በፓርቲው ስራ አስፈጻሚ ምክር ቤት ስብሰባ ላይ "መርጣችሁናልና ከናንተ ጋር ተጋግዘን ሃላፊነታችንን እንወጣለን "የሚል ንግግር ማድረጋቸው የሰውየው ሹመት ለይስሙላ የተካሄደና አለቃቸው የነበራቸውን አይነት ሙሉ የጠቅላይ ሚኒስትርነት ስልጣን የሚሰጥ አለመሆኑን በግልጽ ያመላክታል ብለዋል የወቅቱ ፖለቲካ ተንታኞች።

ያም ሆነ ይህ ብዙም የሃይለማርያም ሹመት ብዙም ሳይዘልቅ ክፍት በሆነው የጠቅላይ ሚኒስትርነት ቦታ ላይ የአራቱም የግንባሩ አባል ድርጅቶች አይን አረፈ።የህወሃቱ ሊቀመንበር መለስ ዜናዊ ያለተቀናቃኝ ብቻቸውን እጁን ይዘው ሲመሩት ቆይተው ድንገት በሞት ሲለቁት መራመድ ተስኖት የተውገረገረው ኢህአዴግ አቶ ሃይለማርያምን ከሾመ ከሶስት ወራት በኋላ ህዳር 20 ቀን 2005 ዓ.ም ባካሄደው የስራ አስፈጻሚ ምክር ቤቱ ስብሰባ ያልተጠበቀ ውሳኔ በማሳለፍ ብዙዎችን አስገርሟል።ፓርቲው በዚህ ስብሰባ ላይ አባል ድርጅቶቹ ለስልጣን የሚያደርጉትን ሽሚያ በግልጽ ያሳየበትን ውሳኔ አሳልፏል ይላሉ አስተያየት ሰጪዎች።ኢህአዴግ አንድ የህውሃት ከባድ ሚዛን ተሰላፊ ባለስልጣኑን (መለስ ዜናዊን) ቦታ አዲስ ለሾማቸው የደኢህዴንና የብአዴን አመራሮች ብቻ ከማስረከብ ይልቅ ለአራቱም አባል ድርጅቶች ለማካፈል የወሰነ በሚመስል መልኩ በክላስተር ሃላፊነት ከኦህዴድ እና ከህወሃት ሁለት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮችን በሹመት በመጨመር ሃይለማርያም በአጠቃላይ በሶስት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮች እንዲታጀቡ አድርጓቸዋል።

ከህገመንግስታዊ የአሿሿም ስርዓቱ ውጪ የተካሄደው ያልተለመደ የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮች ሹመት ከሁለት አመታት ላልበለጠ ጊዜ ጸንቶ ቢቆይም በብዙሃን ዘንድ ያስነሳውን የውስጠ ፓርቲ የስልጣን ሽኩቻ ጥርጣሬን ለመቀልበስ ተብሎ በድጋሚ የተካሄደው የአደረጃጀት ለውጥ የተጨመሩትን ሁለት የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮች ቦታ ሰርዞት ወደ ነበረበት መልሶታል።ያም ሆኖ ብዙሃኑ ለሃይለማርያም ተሰጥቷል የተባለው ስልጣን የይምሰል እንደነበር ሲተች እንደነበረው ሁሉ በርግጥም የርሳቸው የስልጣን ዘመን አንድ ጠንካራ ውሳኔ እንኳን ያልተላለፈበትና በፓርቲው ውስጥ የአመራር ዝቅጠት የታየበት ጊዜ ሆኖ አልፏል።

## ትናንትና ዛሬ

ብዙሃኑ አስቀድሞ የተዘራ በሚሉት ፓርቲውግን "ይሆናል ብዬ አልጠበቅኩም ነበር" በሚለው ቀውስ የሃገሪቱ የፖለቲካ አቅጣጫ ከአንድነት መንፈስ ይልቅ ወደ ዘርና ጎሳ ፖለቲካ ሲቀየርና ኢህአዴግ ሃገር የሚዘውርበትን የፖለቲካ መሪ ሊያስጥለው ሲቃረብ 17 ቀናት የፈጀ ስብሰባ በማካሄድ "ውስጤን ለማጥራትና ችግሩን ከስሩ ለመመርመር ሞክሬ ተሳክቶልኛል" ብሎ ብቅ አለ። ለዘመናት ታፍነው የቆዩ የህዝብ ድምጾች መሰማት ሲጀምሩ፣የመብት ጥያቄዎች እዚህም እዚያም ሲነሱ፣ከዚያም አልፎ በኦሮሚያ እና አማራ ክልል ታላላቅ ህዝባዊ ተቃውሞዎች ሲቀጣጠሉና የአንድ ፓርቲ የበላይነት ያብቃ የሚሉ ድምጾች ገንነው ሲደመጡ፣ኢህአዴግም በቀደመ አካሄዱ በሃይል ለመፍታት ሞክሮ የማይሆን ሲሆንበት የማይቋቋመው ፈተና እንደገጠመው ተረድቶ ጥገናዊ ለውጦችን ለማካሄድ ሞክሯል። በዚህ አደገኛ እና ምስቅልቅል ኹነት ውስጥ ያለው ኢህአዴግ "ህዝብን ባለማዳመጡ የተነሳ ችግር መፈጠሩን አምኗል" ብለው የተናገሩትና "እመኑን ሁሉንም እናስተካክላለን" ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ሃይለማርያም ባልተጠበቀ ሁኔታ "ለተፈጠረው ችግር የመፍትሄው አካል ለመሆን" የሚል ምክንያት በመስጠት በስልጣን ዘመናቸው ሁለተኛቸው የሆነውን የስልጣን መልቀቂያ ጥያቄ ሲያቀርቡም ለሁለተኛ ጊዜ "ኢህአዴግን ማን ሊመራው ነው?" የሚለው ጥያቄ መራገብ ጀምሯል። ይህንን ተከትሎም ነው የአባል ድርጅቶቹ የስልጣን ፍላጎት ፈጥጦ የወጣውና እስከዛሬ ለዘለቀ ሃሜትና ሽኩቻ የዳረገው።

## የ44 መርፌ ጉዳይ

"44 መርፌዎች ተጨፍልቀው አንድ ማረሻ አይወጣቸውም "እንደሚባለው ኢህአዴግ አብይን ቢያመጣ ደመቀን ቢያወጣ ኢህአዴግነቱን አይለውጠውም፣ የህዝቡ ጥያቄ የጠቅላይ ሚኒስትር ሳይሆን የስርዓት ለውጥ ጥያቄ ነው" ይላሉ ስማቸው እንዲገለጽ ያልፈለጉ አስተያየት ሰጪ። በሌላ በኩል ኢህአዴግ በመጪው ነሃሴ ተግባራዊ ያደርገዋል ተብሎ የሚጠበቀውን ከግንባርነት ወደ ሃገራዊ ፓርቲነት የሚያሸጋግረውን ሰነድ ማርቀቁን ተከትሎ እንደዶክተር አብይ ያሉ አዲስ አስተሳሰብ ይዘው ወደመድረኩ ብቅ ያሉ ፖለቲከኞች ሲጨመሩበት "ፓርቲው ለገዛ ራሱ እድሜ ሲል ያለፉ ስህተቶቹን ይዞ ይጓዛል ብሎ ለመደምደም ያስቸግራል" የሚል አስተያየት የሰጡ ፖለቲከኞች ምናልባትም ለውጥ መምጣት ካለበት ኢህአዴግ የሚፈራውን ለውጥ መተግባር ያለበት ጊዜ አሁን ነው ይላሉ። ምክንያታቸው ደግሞ "ለ27 ዓመታት የታፈኑ የለውጥ ጥያቄዎች መፈንዳት በጀመሩበት በዚህ ጊዜ ኢህአዴግ በአባል ግለሰብም ይሁን በፓርቲ ደረጃ ለውጥ ለውጥ መሸተት ካልቻለ ከሁሉም የከፋው አደጋ በራሱ ላይ የሚከሰተው የመሰነጣጠቅና የመበታተን አደጋ ነው" የሚል ነው። በአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ዘመን ህዘብ የናፈቀውን ለውጥ ማጣጣም ይችላል አይችልም የሚለውን ለማየት ከፊት ያሉት ጥቂት ወራት በቂ ናቸው።

# 45 ዓመታት በመድረክ

"ፍቅር እወዳለሁ። ሰው ሲዋደድ ማየት ደስ ይለኛል። ሰው ሲናናቅ ማየት ያስጠላኛል። እብሪት አልወድም።"

ፍቃዱ ተ/ማርያም



ፍቄን የብሔራዊ ቴአትር ቤተኛ ከመሆኔ 1989 በፊት ነው የማውቀው። በሩቁ። በአድናቆት። በፍቅር። በጣም በፍቅር የምወደው እሱን ለመተካት የምመኘው ሰው ነበር። ያኔ።

ድምፁ ፣ እርጋታው ፣ የመድረክ አጠቃቀም ብቃቱ ፣በሬዲዮ የቅዳሜ መዝናኛ ድራማ ከነጀማነሽ ሰሎሞን ጋ ሲሠራ የነበረው የአተዋወን ብቃት ፤ እሑድ ምሽትና በድጋሚ ሰኞ ጠዋት ከመጽሐፍት ዓለም ፕሮግራም ላይ ይተርካቸው የነበሩ መጽሐፍት የገጸ-ባሕሪያቱ ድምፁጽግርማ ሞገሱ ለፍቄ ልዩ ቦታ እንድሰጠው አድርጎኛል።

በሚተውንባቸው ቴአትሮች አብዛኛውን ጊዜ የንጉሥ ገጸ-ባሕሪ አልያም መሪ ተዋናይ ሆኖ መጫወቱ ብዙዎች እንዲያውቁት ሆኗል፡ ፡ ከአንድም አራት ዐሥርት ዓመታት ተሻግሮ ዕውቅናው ያልደበዘዘ ክብሩ ያልቀዘቀዘ ፤ ሁሌም ደረጃውን እንደጠበቀ ያለ ተዋናይ ነው።

ዛሬ ፍቄ ሁለቱም ኩላሊቶቹ ታመው ወገኖቼ ድረሱልኝ እያለን ነው። ጉዳዩን ከሰማንበት ቅጽበት ጀምሮ ሐሳባችን በሙሉ ወደ ፍቃዱ ተ/ማርያም ጤና አመራ። ፈርጥ መጽሔት ሰኔ 1994 ላይ የወቅቱ ተሸላሚዎችን ታሪክና ብቃት በመጥቀስ ለአንባቢያን አቅርቧቸው ነበር። እኛም ፍቃዱ ተ/ማርያምን ከምንጫችን በጥቂቱ እነሆ።

የ1994 የኢትዮጵያ ሥነ ጥበባትና መገናኛ ብዙኃን ሽልማት በተዋንያን ዘርፍ ተሸላሚው ፍቃዱ ተ/ማርያም የተወለደው ጥቅምት 1 ቀን 1948 ነበር ። ይህ ዓመት ብሔራዊ ቴአትር የተከፈተበት ዓመት መሆኑን ልብ ይሏል። ዛሬ የ62 ዓመት (ላስረጀው ከበደኝ) አንጋፋ ተዋናይ አዲስ አበባ፣ አራት ኪሎ ፣ባሻ ወልዴ ችሎት ፣ጅሩ ሰፈር ነው የተወለደው። ዛሬ ሰፈሩ ለልማት ፈርሶ ወይ አልለማ ወይ አልኖሩበት በቆርቆሮ ታጥሮ የውሻ መፈንጪያ ሆኗል።

የተማረው ፦ ኢዮቤልዮ ቤተመንግሥት ፣ዑራኤል ት/ቤት ፣ ኮከበ ጽባህ ፣ ዳግማዊ ምኒልክ ነው። በ1976 በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በቴአትር ጥበባት ክፍል ይሰጥ የነበረውን ልዩ የቴአትር ትምህርት ለሁለት ዓመት ተኩል ተከታትሏል። ከ10 ዓመታት በፊትም በማኔጅመንት የመጀመርያ ዲግሪውን አግኝቷል።

በልጅነቱ ለፊልም ልዩ ፍቅር ነበረው። አራት ኪሎ ወወክማም ይሳተፍ ነበር። አንድ ቀን ትሩፋት ወ/የስን ያገኛትና አድናቆቱን ገልጾ ቴአትር መሥራት እንደሚወድ ይነገራታል። እሷም ሀገር ፍቅር የቴአትር ዕድገት ክበብ መሥራች ከሆኑት ከአቶ ተስፋዬ አበበ ጋ አገናኘችው። (ይሄ ማለት 1965 ነው) እዚያ ዝነኞቹን እነ ወጋየሁ ንጋቱ ፣ደበበ እሸቱን ፣ተክሌ ደስታን ሲራክ ታደሰን ፣ዓለሙ ገ/አብ ፣ዓለም ፀሐይ ወዳጆን ያገኛቸዋል። እነዚህን የዘመኑን ዝነኞች ማግኘት ምን ዓይነት የደስታ ስሜት እንደሚሰማ አማተር የጥበብ ሰው በደንብ ያውቀዋል።

ከሁለት ዓመት በኋላ ፍቄ ማዘጋጃ ቴአትርና ባሕል አዳራሽ ተቀጠረ። መቼ እንደሆነ ባላውቅም (1980ዎቹ ውስጥ ይመስለኛል) ወደ ብሔራዊ ቴአትር ተዘዋወረ።

በፕሮፌሽናል መድረክ የመጀመሪያ ሥራው ባለካባና ባለዳባ የመንግሥቱ ለማ ድርሰትን ነበር። ይህንን ድርሰት ከረጅም ዓመታት በኋላም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር መድረክ በብቃት ሲጫወተው ተመልክቻለሁ።

በ1968 በአያልነህ ሙላት ተደርሶ በአባተ መኩሪያ የተዘጋጀውን "እሳት ሲነድ" ቴአትርን ገና በ20 ዓመቱ በመሪ ተዋናይነት ለመጫወት በቃ። ፍቃዱ ባለፉት ድፍን 44 የቴአትር ዓመቱ በበርካታ ቴአትሮች ፣የቴሌቪዥን ድራማዎች ፣ የመጽሐፍት ትረካዎች ፣ ፊልሞች የሬዲዮ ድራማዎች ላይ ተሳትፏል። ከተሳተፈባቸው ቴአትሮች ጥቂቱ ፦

ግደይ ግደይ አለኝ ፦ መንግሥቱ ለማ
መቃብር ቆፋሪውና ሬሳ ሣጥን ሻጩ ፦ ዶ/ር ፍቅሬ ቶሎሳ
ቤቱ ፦ ሥዩም ተፈራ
ሠርግና ዋዜማ ፦ ሥዩም ወልዴ

የጋሽ ጸጋዬ ገ/መድኅን
መልእክተ ወዛደር
መቅድም
ኦቴሎ
ቴዎድሮስ
የከርሞ ሰው
ታርቲዩፍ (ሞልየር)
ማክቤዝ
ሐምሌት
የሊስትሮ ኦፔራ ፦ አባተ መኩሪያ
ኤዲፐስ ንጉሥ ፦ዶ/ር ኃይሉ አርአያ
ዋዜማ (በጣም የወደድኩለት) ቴዎድሮስ ተሰማና ጫንያለው ወ/ጊዮርጊስ
ንጉሥ አርማህ ፦ መልካሙ ዘሪሁን
ይጠቀሳሉ።

ከሠራቸው ቴአትሮች ከግማሽ በላዩን አይቼለታለሁ። በወቅቱ ፍቃዱ ቴአትር ሠርቶ ለማየት ያስተዛዝብ ነበር (1980-1999) ፍቄ የሠራቸውን ቴአትሮች እንደሚያስታውስም ሲናገር፦

"ጠለቅ ብሎ የገባሕን ነገር አትረሳውም። የጸጋዬ ገ/መድኅን የከርሞ ሰውን ፣ የመንግሥቱ ለማ "ባለካባና ባለዳባን" አልረሳቸውም። እንደገና ይሠሩ ቢባል ትንሽ ንባብ ይበቃኛል። ቃለ ተውኔቶች የማልረሳበት ምክንያት ፍቅር ነው። ፍቅሩ ስላለኝ ሁልጊዜ ውስጤ ይኖራሉ። "የከርሞ ሰው" የራሳችን ታሪክ ነው። ሰፈሩ ቁጭራ ነው። አሜሪካን ድረስ ሠርተነዋል። በቀለ ተፈራ አዘጋጅቶት እኔ ፣ሱራፌልና ሥዩም ሆነን እዚህ ሠርተነዋል። ተውኔቱ አልቆ ሰዓት ስንመለከት እስከ አራት ሰዓት እንጫወተው ነበር። በኋላ ሲታይ ለካ ሦስታችንም እንወደዋለን። በቃ ስንታመምበት ፣ስንታሽበት እንውላለን። የምር የምር ነበር የምንጫወተው"

ፍቃዱ በ45 የቴአትር ዓመቱ (ከ1965 እስከዛሬ) ስለጻፈው ተውኔት ወይም ስላዘጋጀው ቴአትር የሰማሁት ነገር የለም። እንደ ባልደረቦቹ ገለጻ ፍቃዱ ቴአትር የማያዘጋጀው እጅግ ትሁት በመሆኑ ፤ በቴአትር ዝግጅት ወቅት ደግሞ መጎሻሸም ስለማይታጣ ያንን በመሸሽ ነው።

ፍቄ ለሚዲያም እንደ ሌሎቹ አክተሮች ቅርብ አይደለም። በተደጋጋሚ ለቃለ መጠይቅ ፈልገውት ያልተቀበላቸው ጋዜጠኞች በአንድ ወቅት የተሳሳተ ነገር በመጻፋቸው መቆጣቱንና ቁጣውንም "አንበሳው አገሳ" በሚል በሳምንቱ መጻፋቸውን አስታውሳለሁ።

ሽልማት ፦ የፍቄ ትልቁ ሽልማት ሥራዎቹን ያዩ ሁሉ ያለ ልዩነት እሱን መውደዳቸው ነው፣ሌላው የሥነጥበባትና መገናኛ ብዙኃን የወቅቱ ተሸላሚ መሆኑ ፣ በአንድ ወቅት በሠራው ፊልም የመኪና ተሸላሚ መሆኑ.....

"የፍቃዱ ትልቅ ሀብቱ ድምፁ ነው። የማይሰለች ድምፅ አለው ። ይህን ጣፋጭ ድምፁን አዳራሽ ውስጥ ፊት እና ኋላ የተቀመጠ ሰው እኩል ይሰማዋል ።አይጮህም።....እያንዳንዱ የሚናገረው ቃል ይሰማል። በዚህ ላይ በጣም ዲሲፒሊንድ ነው። ችግር አጋጥሞት ልምምድ ላይ የሚያረፍድ ከሆነ ደውሎ ይናገራል። ሥራው ላይ በጣም ሲሪየስ ነው።"

ማንያዘዋል እንደሻው።

"ለሕዝቡ ሊሰጥ የሚገባውን ነገር በሙሉ ይሰጣል። ቴዎድሮስ ቴአትር በጣም ብዙ ለሆኑ ተመልካቾች ሜዳ ላይ ተሠርቷል። በእንዲህ ያለ አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ በአግባቡ ይሠራ ነበር።"

አበበ ባልቻ

ስለ ጋሽ ፍቃዱ ብዙ ማለት ይቻላል። አሁን በቅድሚያ በጤናው ላይ እንዲድን እንረባረብ። ሁለቱም ኩላሊቶቹ እንደታመሙበትና በአስቸኳይ ወደ ውጭ ወጥቶ ሊታከም እንደሚገባው ኮሚቴዎቹ ገልጸዋል። ለዚህ ደግሞ ገንዘብ ያስፈልጋል። ከኪሱ አውጥቶ የሚታከምበት ቀላል ገንዘብ አይደለም። ገንዘብ እንዲሰበሰብ በሀገር ውስጥ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 1000239345488 የአካውንት ቁጥር በውጭ የምትገኙ ደግሞ በጎ ፈንድ ሚ አድራሻ ገቢ ብታደርጉለት የፍቄን ውለታ እንመልስ ይሆናል። የጣለብን ኃላፊነት ከባድ ነው። በቴአትር ፣በፊልም ፣በሬዲዮ ድራማ ትወና ከ45 ዓመት በላይ ስላገለገለው ፍቄ ነው የምናወራው።

ይህ ዜና ለሕዝብ ከተሠራጨበት ቅጽበት አንሥቶ በርካታ በጎ ፈቃደኞች ኩላሊታቸውን ለመስጠት መነሣሣታቸውን አስተባባሪዎቹ ተናግረዋል። ይህም መልካም ዜና ነው፤ ሆኖም ኩላሊት ልገሳ በደም መመሳሰል ብቻ የሚሰጥ ሳይሆን በርካታ "ማቺንግ" በመኖራቸው ምራመራዎች ይደረጋሉ ይህም የሚታወቅ በመሆኑ የሕክምና ባለሙያዎች በተለይ የኩላሊት ስፔሻሊስቶች የነገሮች ማፋጠን ትኩረት ቢሰጡበት እንጠቁማለን።

የፍቃዱ ተክለ ማሪያም ጤና ያሳስበናል፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተሽሎት ወደሚወደው ማኅበረሰብ እንዲመለስ የ"ግዮን" መጽሔት ዝግጅት ክፍል ይመኛል።



ግርማ ሰይፉ ማሩ

# ኢትዮጵያችን በመንታ መንገድና በገደል አፋፍ ላይ ትገኛለች፤ ዜገች ምን እንውሰን?

የአገራችን ፖለቲካ መበላሸቱ ብቻ ሳይሆን፣ የአገር ህልውናን አደጋ ላይ የሚጥል ሊሆን እንደሚችል ስጋት ያላቸው ብዙ ናቸው፡፡ እኔም የፈለገ ተሰፈኛ ብሆን ከዚህ ስጋት ነፃ ነኝ ልል አልችልም፡፡ አፍቃሪ ህወሓት/ኢህአዴግ የሆኑ የማህበራዊ ሚዲያም ይሁኑ ሌሎች መገናኛ ብዙሀን ይህን ስጋት አጉልተው ለማሳየት የማያደርጉት ጥረት የለም፤ ከጥረታቸው ሚዛን የሚደፋው በቅርቡ በመታመስ ላይ ያሉትን ሊቢያ፣ ሶሪያና የመንን እንደ ምሣሌ በማቅረብ ነው፡፡ ይህ በምሥልና ድምፅ እየተደገፈ የሚቀርበው ዘግናኝ ትዕይንት ለመማር ለሚፈልግ ጥሩ ማሣያ ቢሆንም ነገሩ ግን ሌላ ነው፡፡ ‹‹እንደ እነዚህ አገሮች እንዳንሆን አርፋችሁ ተቀመጡ›› የሚል መልዕክት ያዘለ፣ ሠላም፤ ሠላም፤ ሠላም በሚል መዝሙር አጅበው ማቅረባቸው ነው፤ ሊቢያ፣ ሶሪያ እና የመን ለዚህ ደረጃ ያበቋቸው አንባገነን መሪዎች ናቸው፤ ከዚህ መማር ያለባቸው አንባገነን መሪዎች እንጂ ህዝቡ ሊሆን አይችልም፡፡

..መቼም ለእነዚህ አገሮች ውድመት ህዝቡ ነው ተጠያቂ የሚል ሰምቼም አንብቤም አላውቅም፡፡ .. የእኛም አገር መሪዎች እባካችሁ አገራችን እንደነዚህ አገሮች እንዳትሆን ከግል ሥልጣን መሻት እና ሌላ ማንኛውም ግላዊ ፍላጎት እራሳችሁን አፅድታችሁ ታሪክ ስሩ እያልናችሁ ነው፤ ኢትዮጵያ ከላይ ከተጠቀሱት አገሮች እንደ አንዳቸው እንዳትሆን ኃላፊነቱ ያለው በፖለቲካ መሪዎች ይልቁንም በህወሓት/ኢህአዴግ እጅ ውስጥ ነው፡፡

አገራችን በመስቀለኛ መንገድ ላይ እንደምትገኝ፤ ከመገዶቹ ዳር እና ዳር ደግሞ ትልቅ ገደል መኖሩን እንገነዘባለን፤ ትክክለኛውን መንገድ መምረጥ እና ከገደሉ መራቅ የግድ ይላል፤ ይህ የአስተዋይ ምርጫ ነው፤ የሰሞኑን ሁኔታ ለሚያስተውል ግን የብልህ አያያዝ አይመስልም፤ እስረኞችን መፍታት መጀመሩ በጎ ጎኑ ሲሆን ሌሎችን ያለመፍታቱና በተመሳሳይ ሁኔታ ሌላ እስርን መጀመሩ አሳዛኙ ክስተት ነው፤ እስረኞች የተፈቱበት ምክንያት ለጋራ አገር በጋራ መፍትሔ ለመፈለግ የመሰለን ሰዎች ተሳስተናል ማለት ነው፡፡

የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች የፖለቲካ ምህዳሩን ለማስፋት በቁርጠኝነት የተሻሉ እርምጃዎች ይወስዳሉ የሚለው ቀርቶ ለቀጣይ ስድስት ወር በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ስር እንድንሆን ያለ ፍላጎታችን ሲፈረድብን ደግሞ የበለጠ ግምታችን የተሳሳተ፣ ተስፋችንም የህልም እንጀራ እየሆነብን ይገኛል፤ ሌላው ተስፋ የጣልንበት ወፌ ቆመች እያልነው የነበረው ፓርላማ መዋረዱ ተስፋችንን ያጨልምብናል፤ ፓርላማውን የሚያዋርዱት ደግሞ “የተከበሩ” ተብለው በምክር ቤት ውስጥ ያሉት ጭምር መሆናቸው ነው፡፡

እንዲህ እንድንል ያስገደደን ደግሞ ግንባሩ ከዚህ በፊት በሚስጥር ሲያደርግ የነበረውን ሁሉ አሁን በይፋ እያደረገው መሆኑ ነው፡፡ ግንባሩ በሸፍጥ የተሞላ ድርጅት እንደሆነ በግልፅ አውቀናል፤ በቅርቡ ኢህአዴግ እንደ ግንባር የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያስፈልገኛል ብሎ ቆርጦ ተነስቷል፤ በግልፅ ቋንቋ ወታደራዊ አገዛዝ ያስፈልገኛል እያለ ነው፡፡... ይህን ደግሞ በኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ በተለመደው አካሄድ ካፀደቀ በኋላ ወደ ካቢኔ በመሄድ ለወጉ እንዲፀድቅ ተደርጓል፡፡

ፓርቲው ያፀደቀውን የመንግስት አካል ተብዬው “ካቢኔ” የሚባለው የሚቃወምበት አቅም የለውም፤ ለዚህ ነበር ቴክኖክራት ካቢኔ ዋጋ የለውም ስንል የነበረው፡፡... ይህ ጉዳይ ወደ ፓርላማ መቅረብ ስለነበረበት በተመሳሳይ የፓርላማ አባላትም ቀድመው ውይይት እንዲያደርጉ በየድርጅቶቻቸው የስራ አሰፈፃሚዎች ውሳኔው ተነገራቸው፤ ውይይቱ ውሣኔ ለመቀየር ሳይሆን እንደ ተለመደው የስራ አሰፈፃሚውን |ውሳኔ እንዲቀበሉ ነበር፤ ድርጅታዊ ማዕከላዊነት በሚባል አሰራር፡፡ ይህ በተመሳሳይ ‹‹አጋር›› ለሚባሉት ድርጅቶችንም ይመለከታል፡፡ ሁለት ሶሰተኛ ድምፅ የሚያስፈልግ በመሆኑ 46 ድምፅ ያላቸውን አጋሮችንም ችላ ማለት ሳያስፈልግ፣ አፈ ጉባዔው ፈልገውት እንደ ነበረው በተባበረ ድምፅ በማፀደቅ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ቲያትር ተሰራ፡፡

**ጠቅላይ ሚኒስትር ታሪክ እንዳይሰራ እንቅፋት የሚሆን አፈና በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ስም ለምን እንዳሰፈለገ አልገባንም፤ ለለውጥ የተነሳን ህዝብ ማንኛውም የአፈና አካሄድ አያቆመውም፡፡**


አፈ ጉባዔ አባዱላ ገመዳ ‹‹በተባበረ ድምፅ እንዲፀድቅ›› የሚል ደፋር ጥያቄ ለምክር ቤት ተብዬው ያቀረቡት ይህንን አካሄድ በመተማመን ነበር፡፡ ለማንኛውም ይህ እንዲሆን ለጊዜውም ቢሆን ያልፈቀዱት እጅግ ብዙ አባላት በታሪክ ፊት በኩራት የሚያቀርባቸውን ውሳኔ ወስነዋል፡፡

ከህዝብ ጀርባ፤ ከህዝብ ፍላጎት ውጭ ይህ ሁሉ ሲደረግ በእኔ አስተያየት አቶ ሀይለማሪያም ደሣላኝ ከስልጣን የመልቀቅ ጥያቄ አቀረብኩ ከሚሉን፤ በእውነትም የለውጡ አካልና መሪ ሊሆኑ የሚችሉበትን እድል በሚያሳዝን ሁኔታ አሳልፈው ሰጥተዋል፡፡ ይህንን ምክር ቤት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 60 መሠረት በትነው በስድስት ወር ውስጥ ምርጫ በማድረግ ለአሸናፊው ስልጣን ማስረከብ ነበረባቸው፤ ይህ ታሪክ በወርቅ ሳህን ያቀረበላቸውን እድል ሳይጠቀሙበት አልፈዋል፤ እናዝናለን፡፡ ... አሁን ደግሞ ማንም ይሁን ማን የሚመጣው ጠቅላይ ሚኒስትር ታሪክ እንዳይሰራ እንቅፋት የሚሆን አፈና በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ስም ለምን እንዳሰፈለገ አልገባንም፤ ለለውጥ የተነሳን ህዝብ ማንኛውም የአፈና አካሄድ አያቆመውም፡፡ በውስጥ ለውስጥ ስምምነት ተደርጎ በመጣ ውሳኔ በምክር ቤት ስም ለማላገጥ የመጣን ቡድን አምላክ በኪነ ጥበቡ አጋለጠልን፡፡ አሁን የተፈጠረው የቁጥር ስህተት ለአንደኛ ደረጃ ተማሪም ቢሆን ከባድ አልነበረም፤... እንኳን ስማርት ፎን/ስልክ/ ይዞ ሂሣብ ለሚሰራ የምክር ቤት አፈ ጉባዔ፡፡ ፈጣሪ ግን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጀርባ የተሰራን ሴራ በአደባባይ አጋልጦልናል፤ ይህን ሸፍጥ ለማጋለጥ ብርታት ላገኙት የምክር ቤት አባላት ምስጋና እና ክብር ይገባቸዋል፡፡

በዚህ አጋጣሚ አቶ ሀይለማሪያም ደሣለኝ እድላቸውን ባይጠቀሙበትም ሌሎች ታሪክ እንዲሰሩ እድል ፈጥረዋል ለማለት ይቻላል፤ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ማን ይሆናል? የሚል ጥያቄ እንዲነሳ በማድረግ፡፡ ነገር ግን ይህ አዲስ ጠቅላይ ሚኒስትር የመሰየም ጣጣ አሁንም በድርጅት ሴራና አሻጥር ውስጥ መውደቁ አሳዛኙ የህወሓት/ኢህአዴግ ቲያትር ሌላኛው ክፍል ነው፡፡... ሰሞኑን ይህ ጉዳይ እያስነሳ ያለው ጭቅጭቅ የኢትዮጵያ ህዝብ በግልፅ መሪውን የመምረጥ ፍላጎት ብቻ ሳይሆን አቅም አንዳለውም የሚያመላክት ነው፡፡ ከዚህ ቀደም ህወሓት በተለይ አቶ መለስ ዜናዊ ለህዝብ ያላቸውን ዝቅተኛ ተቀባይነት ከግምት በማስገባት “ፓርላሜንታዊ ሥርዓት” በሚል ሽፋን ዜጎች መሪያቸውን በቀጥታ እንዳይመርጡ ፤ይልቁንም ድርጅቶች ከህዝብ ጀርባ ሆነው መሪ ተብዬ የሚመርጡበትን ሴራ ሰርተውብን አልፈዋል፡፡ ይህ አካሄድ ግን ማብቂያው ጊዜ ደርሷል፡፡ ራዕይ አለኝ፣ የኢትዮጵያን ህዝብ ለመምራት እችላለሁ የሚል ዜጋ በይፋ ወጥቶ ለህዝብ ቀርቦ ዳኝነቱን ከህዝብ መጠበቅ አለበት፡፡

ኢትዮጵያዊያን በመንታ መንገድ በገደል አፋፉ ላይ ብንገኝም መውጫውን መንገድ እናውቀዋለን፡፡ ደንቃራ የሆነብን አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚባለው መንፈስ እና የመንፈሱ ተሸካሚ የሆኑት የህወሓት/ኢህአዴግ ዋነኛ ችግሮቻችን ናቸው፡፡ ለዚህች አገር ትንሣዔ ሲባል አገራችን የጋራ መሆኗን ከግንዛቤ በማስገባት በጋራ መፍትሄ እንፈልግ፡፡ ቀጣዩ ጠቅላይ ሚኒሰትር ከዚህ የሚበልጥ ታሪካዊ አጋጣሚ አያገኝም፡፡ ይህን እድል በመጠቀም ይህችን ትልቅና ታሪካዊ አገር ወደ ከፍታው ማማ ለማውጣት በጋራ አብረን እንቁም!!!!!





ቴዎድሮስ ተ/አረጋይ

# “በእኛ ፕሮግራም የኩላሊት ህክምናውን ማግኘት አይቻልም”

## ዶ/ር ብርሃኔ ረዳኢ

(በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ የህክምና አገልግሎት ዘርፍ ም/ፕሮቮስት)

- ለምን አይቻልም?
- ሁለቱም ኩላሊቶች አገልገሎት መስጠት አቁመዋል ለምን ተደጋግሞ ይሰማል?
- የሃገራችን ኩላሊት ንቅለ ተከላ በአለም በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?
- ህክምናው ነፃ ነው ወይስ በከፍተኛ ወጪ?
- ምን ያህሎች ለችግሩ ተጋልጠዋል ስንቶቹ ታክመ ዳኑ በህይወት ያልተረፉትስ?

በእነዚህና ሌሎች ጥያቄዎች ላይ ዶ/ር ብርሃኔ ረዳኢ ምላሽ ይሰጡባቸዋል፡፡

**ግዮን፡- በከተማችንም ሆነ በአገራችን ሁለቱም ኩላሊቶቹ/ቿ አገልግሉት መስጠታቸውን አቁመዋል የሚለው ዜና በስፋት እየተሰማና የብዙዎችን የድንጋጤ ትኩረትም እያገኘ ነው፡፡ በሙያው አጠራር ‹‹ኩላሊት›› አገልሎት መስጠቱን አቆመ ማለት ምን ማለት ነው?**

ዶ/ር ብርሃኔ፡- በቅድሚያ እነዚህን መልሶች የምሰጥህ እንደ ኩላሊት ባለሙያ ሳይሆን እንደ አንድ በአገራችን በኩላሊት ዙሪያ የተሟላ አገልግሉት የሚሰጥ ተቋም ሃላፊ በመሆኔ ለስራው ባለኝ ቅርበት ነው፡፡ ይህ ግንዛቤ ውስጥ እንደዲገባልኝ እፈልጋለሁ፡፡ የኩላሊት ዋና አገልግሉት በሰውነታችን ውስጥ ያሉ አገልግሎቶቻችንን በማሳላጥ ደም የማጣራት ስራ ነው የሚሰራው፡፡ ከመላው ሰውነታችን ወደ ደማችን የገቡና መወገድ ያለባቸውን ለማስወገድ፣ ወደ ሰውነታችን መመለስ ያለባቸውን ለመመለስ የማድረግ ስራ ነው የሚሰራው፤ ስለዚህ ኩላሊት ስራ መስራት አቆመ ስንል ደምን የማጣራትና ቆሻሻውን የማስወገድ ስራ አይሰራም ማለት ነው፡፡

ሰውነታችን የራሱ ተረፈ ምርቶች ወዲያው መወገድ ሲኖርባቸው ደማችን ውስጥ በመዘዋወር ሰውነትን የመመረዝ ስራ ይጀምራል ማለት ነው፡፡

**ግዮን፡- ለምን አንድ ብቻ እንደታመመ ታክሞ መዳን አልተቻለም፤ ሁለቱም መባል ለምን ተደጋገመ?**

ዶ/ር ብርሃኔ፡- እንደ ምክንያቱና እንደየግለሰቡ የጤና ሁኔታ አንዱ ወይም ሁለቱ ሊጠቁ ወይም አገልሎት መስጠት ሊያቆሙ ይችላሉ፡፡ ሁለቱም ኩላሊቶች ለስንፈት የሚዳረጉት በአብዛኛው በማወቅም ባለማወቅም ይህ ነው የሚባል የበሽታ ምልክቶች ሳያሳዩ ወደኋላ መመለስ በማይቻልበት ደረጃ ለይ ሲደርስ ነው ወደ ህክምናው ተቋም የሚመጣው፡፡ በየጊዜው የጤና ምርመራ ስለማናደርግ የግንዛቤ ችግርም አለ ፤እያወቅንና ህመም እየተሰማንም ወደ ህክምና ተቋም አንሄድም፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች ህክምናውን እየገፋን አንዱን አክሞ ማዳን እየተቻለ ሁለቱንም ማዳን በማንችልበት ሁኔታ ውስጥ ስንደርስ ነው ወደ ህክምና ተቋማት የምንሄደው፡፡

**ግዮን፡- ምን ምን ሁኔታዎች ኩላሊታችን አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል አስብሎ ወደ ምርመራ ሊወስደን ይችላል?**

ዶ/ር ብርሃኔ፡- እድሜህ ከ50 አመት በላይ ከሆነ፤ የሰውነት ክብደት ካለብህ፤ ሲጋራ የምታጨስ ከሆነ በቤተሰብ ታሪክ ውስጥ የኩላሊት በሽታ የነበረባቸው ካሉ፣ የስኳር በሽታ ወይም የኩላሊት በሽታ ወይም የደም ግፊት በሽታ ካለብህ፣ ከእነዚህ ውጭም የተለያዩ በሽታዎችም ባልጠረጠርክበት ሁኔታ ለምሳሌ የኩላሊት ጠጠር ለዚህ ችግር ልንጋለጥ ሰለምንችል የመዳን እድላችንን አጥተን ወደ ሆስፒታል ስንሄድ ችግሩ ይከሰታል፡፡ በከተማ ባለው የአኗኗር ዘዴ በስኳር ወይም ደም ግፊት የሚጠቁ ዜጎች ቁጥር ከፍተኛ ነው፡፡የእነሱ ቁጥር ጨመረ ማለት ደግሞ ለኩላሊት ስንፈት የሚደረጉ ዜጎች ቁጥር ይጨምራል ማለት ነው፤ በ1960ዎቹ ለህክምና ተማሪዎች የኩላሊት ህመምተኛን ማሳየት በጣም ችግር ነበር አሁን እዚህ ደረጃ ደርሰናል፡፡

**ግዮን፡- የጤና ምርመራ ማድረግ ብንችልና የኩላሊት ስንፈትን በጊዜ ብንደርስበት ታክሞና ድኖ ወደ መደበኛው የጤና ሁኔታ መመለስ ይችላል?**

ዶ/ር ብርሃኔ፡- አዎን መመለስ ይችላል፡፡ የኩላሊትን እንተወውና ዋነኛ አጋላጮች ናቸው የምንላቸው ስኳርና ደም ግፊትን መከላከል ይችላል ወይስ አይቻልም ነው ጥያቄው፡፡ ይቻላል፤ በቀጥታ ኩላሊትህን ሊያስተካክል አይደለም ነገር ግን ሁለቱን በመከላከል ብቻ በኩላሊት ስንፈት የመያዝ እድልህን ታጠባለህ፡፡ በዋነኝነት ሁለቱን ህመሞች ተከታተለህ መቆጣጠር ባለመቻል የሚመጣ ችግር ነው፤ በቀጥታ መታከምም ሌላው አማራጭ ነው፡፡

**ግዮን፡- ለምንድነው የኩላሊት ስንፈት ችግር ይበልጥ የተጋነነ እና ትረኩረት ያገኘው፤ የበሽታው ቁጥር መብዛት ወይስ ሌላ ሰበብ ይኖረዋል?**

ዶ/ር ብርሃኔ፡- በአገራችን ደረጃም ብትሰማቸው እንቅልፍ ወስዶ የማያሳድሩ የበሽታ አይነቶች አሉ፤ ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች ኩላሊት የተለየ ትኩረት አግኝታለች፡፡ ፊልሙ፣ ኤፍ ኤም ራዲዮው፣ ሚዲያው በተለያዩ ምክንያቶች ስለ ኩላሊት ስንፈት ርዕስ አድርገው አንስተው ህብረተሰቡን እንዲወያዩበት አድርገዋል፡፡ ታሪኳ ጆሮ ገብ ሆኖ መቅረቡ በራሱ ትኩረት አሰጥቷታል፡፡ ቁጥሩን ጨምሮታል፤ በተጨማሪም የህክምናው መሻሻልም ሰዎች ወደ ሃኪም ቤት እንዲሄዱ አድርጓቸዋል፡፡

**ግዮን፡- የኩላሊት ህክምና፣ እጥበትና ንቅለ ተከላ የሚካሄድባቸው ሆስፒታሎች የትኞቹ ናቸው?**

ዶ/ር ብርሃኔ፡- በአዲስ አበባ ውስጥ ዘውዲቱ፣ ምኒልክ፣ ጥቁር አንበሳ፣ የኩላሊት ህክምና እስከ እጥበት ይሰጣሉ፤ መቀሌ ጎንደር ባህር ዳር፣ ድሬደዋ፣ ወላይታ ሶዶ ህክምናው በአጭር ጊዜ መስጠት ተጀምሯል፡፡ ህክምናው እስከ እጥበቱ ማለት ነው ሐዋሳ በሂደት ላይ ነው፡፡

**ግዮን፡- ቀደም ሲል የኩላሊት ስንፈት በተለያዩ ምክንያቶች የኪነ ጥበብ የብዙሃን መገናኛ ትኩረትም አግኝቷል ሲባል ህብረተሰቡን ወደ ህክምናው ጣቢያዎች እንዲሄድና ምርመራ እንዲያደርግ በቅድመ መከላከል ስርአት ውስጥ እንዲገባ አድርጎታል ማለት ይቻላል?**

ዶ/ር ብርሃኔ፡- አንተ ተናገርክ ማለት ሰው አዳምጠህ ማለት አይደለም፡፡ ሰው አዳመጠህ ማለትም ይተገብረዋል ማለት አይደለም፡፡ በዚህ ሶሰት አመት ውስጥ በተፈጠረው እንቅስቃሴ መሰረታዊ ለውጥ ይመጣል ብለን አናምንም፡፡

የኩላሊት ህመሙ በአብዛኛዎቹ የሊሎች በሽታዎች ነፀብራቅ ነው፤ ሌሎችን በሽታዎች ስትከላከል ደግም ለኩላሊት ብቻ ሳይሆን ለአጠቃላይ ጤናህ አስፈላጊ እርምጃ ነው። ከስኳርና ደም ግፊት ራስህን መከላከል ብቻ እንኳን የኩላሊት ስንፈትን ችግር በ2/3ኛ መቀነስ ማለት ነው።

**ግዮን፡- የኩላሊት ስራውን ማቆም በነገራችን ላይ የበሽታው ተገቢ ስሙ ምንድነው ‹‹ኩላሊት አገልግሉት መስጠት አቆመ›› እያልን በረጅም መንገድ እየገለፅን ነው፤ ይህ ደግሞ ተግባሩ እንጂ ስሙ አይሆንም፤ ምን ብለን እየጠራነው እንግባባ?**

ዶ/ር ብርሃኔ፡- ስንረዳው ኩላሊቷ አለች በተወሰነ ደረጃም ስራውን ልትሰራ ትችላለች። ነገር ግን በዋነኘነት እሷ የሚጠበቀውን ደምን የማጣራት ስራዋን አትሰራም፤ ሰንፋለች ስለዚህ አዲስ በመጣው አገላለፅ የኩላሊት ስንፈት የሚለው ስያሜ ይበልጥ ሊያግባባን ይችላል።

በነገራችን ላይ በሌሉች ህክምናውን በራሳቸው ቋንቋ በሚሰጡ አገሮች ለእያንዳንዱ የህክምና ቋንቋ፣ አቻ ትርጉም ይሰጡታል። እኛ አገር ግን ሁሉም የመሰለውን ትርጉም ነው የሚሰጠው። የሙያ ማህበራትና የቋንቋ ተቋማት እንደስራ ወስደውት ትርጉም ቢያዘጋጁለትየተሻለ ይሆናል። እኔ የኩላሊት ስንፈት እልሃለሁ። ሌላው ደግሞ ሌላ ይላል፤ የኩላሊት ህመም አይነቱ ብዙ ነው፤ አንዱን ከሌላው በመለየት ስያሜ የሚሰጠው ሌላ ክፍል እንጂ እያንዳንዱ ዶክተር የራሱን ስያሜ መስጠቱ አጠቃላይ መግባባትን አያመጣም። እንዲህ ያለ ሳይንሳዊ ስያሜዎች አቻ የአማርኛ ትርጓሜ ሊሰጣቸው ይገባል፤ ወይም ደግሞ ተማምነህበት የእንግሊዘኛውን በቀጥታ እንውሰደው ማለትም ትችላለህ፤ ታካሚውም አይቸገርም። አንድ ታካሚ መጥቶ የኩላሊት በሽታ ነው የያዘኝ ሲል ብዙ አይነት የኩላሊት ህመሞች አሉ፤ የኩላሊት ስንፈት ቢል ግን ይገባኛል። አንድና የጋራ ስያሜ መኖር አለበት።

**ግዮን፡- በአገራችን ምን ያህል ሰዎች ለኩላሊት ስንፈት ህመም ይጋለጣሉ? ተጋልጠዋል ተብሎ ይገመታል?**

ዶ/ር ብርሃኔ፡- በትክክል ቁጥሩን ማወቅ ይቸግራል። አንተም የጠየከኝ ትክክለኛ ቁጥሩን ሳይሆን ግምቱን ስለሆነ ከዚህ በፊት በውይይት ላይ እንደሰማሁት ከሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ ወደ 60.000 የሚሆኑ በተለያየ ደረጃ የኩላሊት ስንፈት ያለባቸው ሰዎች አሉ ተብሎ ይገመታል። ከዚህ ቁጥር ውስጥ ምን ያህሉ ወደ ህክምናው ጣቢያ መጥተው ክትትል እያደረጉ ነው የሚለውን ማወቅ ይቸገራል። የኩላሊት ታካሚዎች ማህበር የያዘውን ሌሎችንም ደምረህ እስከ 400 ሰው የኩላሊት እጥበት ላይ ይኖራሉ ተብሎ ይታመናል። ግልፅ ባልሆነ መልኩ ባለፈው አመት እስከ 60 የሚሆኑ በከላሊት ንቅለ ተከላ ስርአት ውስጥ የገቡ ሰዎች አሉ። እነዚህ ግን በአንድ አመት የመጡ ወይም ንቅለ ተከላው የተካሄደላቸው አይደሉም፤ ንቅለ ተከላውን ለማካሄድ በተለያየ ደረጃ ላይ ያሉ ናቸው። አዲስ አበባ ውስጥ በተለያዩ የግል ጤና ተቋማት የኩላሊት እጥበት የሚያካሄዱ አሉ፤ መረጃው ወደ አንድ ማዕከል የሚመጣበትና የሚሰበሰብበት አሰራር መኖር አለበት፡

**ግዮን፡- በሃገራችን የመጀመሪያው የኩላሊት ንቅለ ተከላ የተካሄደው መቼ ነው?**

ዶ/ር ብርሃኔ፡- የመጀመሪያው ንቅለ ተከላ ከተካሄደ ያለፈው መስከረም ሁለት አመት አለፈው። አሁን ወደ 2 አመት ከ6 ወራት ማለት ነው።

**ግዮን፡- በእነዚህ 2 አመት ከ6 ወራት ለምን ያህል ዜጎች የኩላሊት ንቅለ ተከላዎች አገልግሎት ተሰጥቷል?**

ዶ/ር ብርሃኔ፡- እስካለፈው ሳምንት ለ75 ሰዋች የኩላሊት ንቀለ ተከላ ተካሂዷል።

**ግዮን፡- ከ75ቱ የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ምን ያህል ሰዎች በህይወት የመትረፍ እድል ሳያገጥማቸው ቀሩ?**

ዶ/ር ብርሃኔ፡- በንቅለ ተከላው ስራ 75 የሚሆኑትም የተሳካ ነው፤ አንድ ታካሚ ግን ንቀለ ተከላው ከተደረገለት በኂላ ሰውነቱ ኩላሊቱን ሳይቀበለው ቀርቶ በህይወት አልፏል። ንቀለ ተከላው በተጀመረ በመጀመሪያዎቹ 6 ወራት የሆነ ነው ይሄ። ከዚያ በፊትም ሆነ በሐኂላ ሌላ እክል የገጠመው ማንም የለም። ስለዚህም በህክምናው ቋንቋ ሙሉ ለሙሉ የተሳካ ነው ማለት ይቻላል።

**ግዮን፡- ለንቅለ ተከላ ስንት ሐኪሞች ከውጪ ይመጣሉ?**

ዶ/ር ብርሃኔ፡- በዋነኘነት አንድ ሐኪም ነው የሚመጣው። ሌላውን ሙያ በሙሉ የሚሸፍኑት የእኛ ሃኪሞች ናቸው። በዚህ ሙያ የሰለጠኑ 4 ባለሙያዎች አሉ፤ ከጥቂት ጊዜያት በኂላ የእኛ ባለሙያዎች ስራውን ሸፍነው የሚሰሩበት ሁኔታ ይፈጠራል።

**ግዮን፡- ከውጭ የሚመጡት ሐኪም የሙያ ብቃታቸዉ ምን ያህል ነው?**

ዶ/ር ብርሃኔ፡- እንግዲህ ከአሜሪካው ሚችጋን ዩኒቨርሲቲ ነው የሚመጡት። ውጤታቸው ደግሞ ብቃታቸውን ይመሰክራል። የአገራችን የኩላሊት ንቅለ ተከላውን በማንኛውም አለም ካለው ተመሳሳይ ተቋም ጋር መወዳደር የሚችል ውጤት ነው ያለው።

**ግዮን፡- በቴክኖሎጂ ረገድ የሀገራችን የኩላሊት ንቅለ ተከላ ቴክኖሎጂ በአለም በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?**

ዶ/ር ብርሃኔ፡- ቴክኖሎጂው በእጅጉ አቅምን የሚጠይቅ ቢሆንም አሁን ሀገራችን ከሌሉች አገራት አንፃርም ተመጣጣኝ እና የተሻለ በሚባል ደረጃ ላይ ትገኛለች። ወደኂላ ልመልስህና አፍሪካ ሀገራት ላይ በንቅለ ተከላው የተለያዩ ፕሮግራሞች አሉ፤ ኬንያ፣ ናይጄሪያ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ግብፅ፣ ከሰሃራ በላይ ያሉ ሀገራት የተለያዩ ፕሮግራሞች አሏቸው። ብዙዎችን ሄደን ስላየን የቴክኖሎጂው ጥራት ደረጃ የመጀመሪያውን ንቅለ ተከላ ካካሄዱ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ነው የጀመርነው። እነሱ ያስቀመጡት ደረጃ ከፍተኛ ነው። የሌሎቹን ደረጃ ለማሳነስ ሳይሆን በአነስተኛ ውጪ አነስተኛ አገልሎት መስጠት ይቻላል፡ እኛ ያመጣነው ቴክኖሎጂና አገልግሎታችን በጣም ከብዙዎች የተሻለና የተሻሉ ከሚባሉት ጋር የሚመጣጠን ነው። የንቅለ ተከላው ዝግጅት ብቻ ወደ 40 ወራት ፈጅቷል። ይህ የሆነው እያንዳንዱ ስራ በጥንቃቄ ለ40 ወራት በመስራቱ ነው ውጤታማ የሆነው። ሮጠን የገባንበት አይደለም ገና ሲጀመርም በአለም ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንዲገኝ ተደርጎ የተሰራ ነው።

> **...በአገራችን ደረጃም ብትሰማቸው እንቅልፍ ወስዶ የማያሳድሩ የበሽታ አይነቶች አሉ፤ ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች ኩላሊት የተለየ ትኩረት አግኝታለች...**

**ግዮን፡- በወጪ ረገድስ የኩላሊት ንቅለ ተከላ ለማድረግ ምን ያህል ይጠይቃል?**

ዶ/ር ብርሃኔ፡- ለንቅለ ተከላው ምንም አይከፈልም፤ ለህክምናው ቀዶ ጥገናውን ጨምሮ አብዛኛው ህክምና ነፃ ነው። ለኩላሊት እጥበት የሚከፍሉት ለግላቸው የሚጠቀሙበትን መሳሪያ መግዣ ነው፤ የባለሙያና ህክምና አይከፍሉም። ለሁለት ወር የሚያስፈልገው መድሃኒት በነፃ የሚሰጥ ሲሆን፤ ከዚያ በኂላ የሚያስፈልገውን መድሃኒት ደግሞ ሃገር ውስጥ በገባበት ዋጋ ይገዛሉ ይሁንናም በሳምንት 3 ጊዜ የኩላሊት እጥበቱን ላማካሄድ በሳምንት እስከ ብር 1,500 (በወር ብር 6,000) ይሆናል። አገልግሎቱ በነጻም ቢሆን ይህ ወጪ ለታማሚው ቀላል እንደማይሆን ይታመናል።

**ግዮን፡- የኩላሊት ንቀለ ተከላን ለማካሄድ ኩላሊት የሚሰጠው ሰው ለታካሚው የቅርብ ዘመድ እንዲሆን የሚፈለገው ለምንድነው?**

ዶ/ር ብርሃኔ፡- በቅርብ ጊዜ ይህ ህግ ይሻሻላል ብለን እናስባለን።

**ግዮን፡- የቅርብ ቤተሰብ የሚለው ሊቀር ማለት ነው?**

ዶ/ር ብርሃኔ፡- አይቀርም፤ አሰራሩን ለማላላት ሳይሆን ይበልጥ ለማጥበቅ ነው የሚሻሸለው። ቤተሰቡ መባሉ አይለወጥም፤ የጤና ጥበቃና ውል ማስረጃ ሰዎች ባሉበት በህግ ፊት ተቀባይነት ያለው ዝምድና በሰነድ ተደግፎ ሲቀርብ እኛም እንቀበለዋለን።

**ግዮን፡- ለምንድነው ዝምድናውን የፈለጋችሁት?**

ዶ/ር ብርሃኔ፡- በዋነኛነት ህገ ወጥ የአካል ሽያጭ ለመከላከል ነው ፤መንግስት የዜጎችን ሰብአዊ ሞራላዊ መብት የመጠበቅ ግዴታ አለበት።

ግዮን፡- በቅርብ ቤተሰቡ ተፈልጎ ኩላሊቱን ለመስጠት ፈቃደኛ የሚሆን ቢያጣ ወይም የሚሰጠው አግኝቶ ከደም አይነቱ ጋር ተስማሚ ባይሆንስ?

ዶ/ር ብርሃኔ፡- በእኛ ፕሮግራም መሰረት የኩላሊት ህክምናውን ማግኘት አይችልም።

**ግዮን፡- የኩላሊት ስንፈት ህመምን ውስብስብ የሚያደርገው ከፍተኛ ወጪ መጠየቁ ብቻ ሳይሆን ለንቅለ ተከላው የሚሰጠው ኩላሊት ከቅርብ ዘመድ እንዲገኝ ግዴታ መደረጉና ከዘመድ ካልተገኘ ታማሚው ተራ ጠባቂ ብቻ መሆኑ ነው። ኩላሊት ሊገኝ የሚችልበት እድል እየተሻሻለ በሚገኘው ህግ በተለየ መልኩ አይታይም?**

ዶ/ር ብርሃኔ፡- ከዘመድ ውጪ ኩላሊት እንዲገኝና ንቀለ ተከላው እንዲካሄድ መፍቀድ በጭራሽ የለበትም፤ ህጉ ይህን ወደ መፍቀድ በፍፁም አይሄድም። ከዚያ ውጪ የኩላሊት አጠባና በተለያዩ ምክንያቶች ኩላሊታቸውን ለግለሰቦች ሳይሆን ለተቋም የሚለግሱ ሰዎች መፍጠር ያስፈልጋል። ጥያቄህን በሰውነት ሳስበው ይገባኛል። ግን አንድን በር ስትከፍት ሌላውን ትከፍታለህ። አሁንም ራሱ ህጉ ሳይፈቅድ አካልን ለሽያጭ የማዋል ሙከራዎች አሉ። በቀድም በሩሲያኛ አንድ ዶክመንተሪ እያየሁ ነበር። ሰውዬው ኔፓል ሄዶ ጋራ ላይ የሚኖሩ ማህበረሰቦችን ያገኛል። ማህበረሰቡ በጋራ መንግስትን አልጠበቀንም ብሎ ከሰሰ።

**ግዮን፡- ለምን?**

ዶ/ር ብርሃኔ፡- የማህበረሰቡ ወንዶች ጠቅላላ አንድ ኩላሊታቸውን ሸጠዋል። ከደቡብ ህንድ እየመጡ 10.000 ሩፒ ወደ መቶ ምናምን ዶላር እየሰጡ ነው ኩላሊታቸውን የገዟቸው፤ መንደሩ በሙሉ ኩላሊቱን ሸጧል፤ ማንም ሰው ለፈለገው ሰው ኩላሊቱን ይርዳ/ይስጥ ስትል ይህ ሽያጭ በግልፅ ይመጣል። ምንም መከላከያ መንገድ አይኖርህም። ህጉንም አጥብቀህ እንኳ ሽያጩን ማስቀረት ቀላል ላይሆን ይችላል። ግን የተሻለ አማራጭ ነው ማለት ነው የሚቻለው።

**ግዮን፡- እስቲ ዶክተር በመጨረሻም በኩላሊት ስንፈት እንዳልጎዳ ምከረኝና ውይይታችንን እናጠናቅ?**

ዶ/ር ብርሃኔ፡- የኩላሊት ጤንነት እጅህ ላይ ነው፤ ማድረግ ያለብህ ነገሮች በጣም ትንሽ ናቸው። የምታጨስ ከሆነ አቁም፤ ክብደትህንም አስተካከል፤ የቤተሰብ የታማሚነት ታሪክ ካለህ አስፈላጊውን ክትትል አድርግ። እድሜህ ከ50 አመት በላይ ከሆነ ለዚህ ህመም ልትጋለጥ እንደምትችል አውቀህ አስፈላጊውን ክትትል አድርግ፤ በቂ ውሃ ጠጣ፤ በስኳርና ደም ግፊት በሽታዎች ላለመጠቃት የምትችለውን ሁሉ አድርግ። ከታመምክ ደግሞ ህመሞች የሞት ፍርድ አይደሉም። ልታስታምማቸውና ልትቆጣጠራቸው የምትችላቸዉ ህመሞች ናቸው። ከሃኪምህ ከተለያዩ መረጃዎች የምታገኛቸውን ምክሮች ከተገበርክ የኩላሊት ስንፈትም ሆነ ሌላውን ጤንነትህን ትጠብቃለህ።

# ኢትዮጵያን እናስቀድም

ዶ/ር ትዕግሥት መንግሥቱ ኃይለማርያም

የኮ/ል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ልጅ ትዕግሥት መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በሀገራዊ ጉዳይ ላይ ለሕዝብ ያስተላለፈችውን መልእክት እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡

‹‹ውድ የኢትዮጵያ ዜጎች ያለፉት ዓመታት የቀኝ ገዥዎቻችን እውነተኛ ዓላማ እየተረዳን የመጣንባቸው ጊዜያት ናቸው፡፡ በዚህ አጋጣሚ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነትና አንድነት መሥዋዕትነት የከፈሉ ወገኖችን በሙሉ ቆም ብለን እንድናስባቸው እጠይቃለሁ፡፡

ሕዝብ ብዙ በደል ደርሶበታል፤ ትግሉም መራርና ከባድ ነው፡፡ ባለንበት በ21ኛው ክፍለ ዘመን ለኢትዮጵያ አብዮት ተሳታፊ ለሆናችሁ ጀግኖች በመሉ ታላቅ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ በቅርቡ አሻንጉሊቱ ጠቅላይ ሚኒስቴር ሥልጣናቸውን ለቀዋል፡፡ ምክንያታቸዉ ‹‹የችግሩ ሳይሆን የመፍትሔው አካል መሆን እፈልጋለሁ›› የሚል ነበር፡፡ አነጋገራቸውም አቀራረባቸውም ጥሩ ነው፤ ነገር ግን የእሳቸው ስልጣን መልቀቅ አሁን ኢትዮጵያ አሁን ኢትዮጵያ ለገባችበት ችግር ምንም ፋይዳ አይኖረውም፡፡

መጀመሪያውኑ ምንም ዓይነት ሥልጣን የሌላቸው ጠቅላይ ሚኒስቴር ሥልጣን ላይ ኖሩ አልኖሩ ልዩነት አያመጣም፡፡ ቀኝ ገዥዎቻችን አምጥተው የሚጭኑብን አሻንጉሊት ጠቅላይ ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ሕዝብ ላነሳው ጥያቄ መልስ አይሆንም፡፡ መልኩ ቢቀያየርም አሻንጉሊት አሻንጉሊት ነው፡፡ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ችግር መፍትሔ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ነው፡፡ የእኛን ሕመም ከእኛ የበለጠ የሚያውቀው የለም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነቱን የሚቀዳጀው በተአምር ሳይሆን አሁን በተጀመረው ከባድና መራር ግትል ነው፡፡ ሁላችንም እንደየአቅማችን እንደየችሎታችን ለእዚህ ትግል መሰለፍ ይኖርብናል፡፡ በጸሎት፣ በጾም፣ በዕውቀት፣ በማኅበራዊ ድረ ገፆች ላይ ዜናዎችን በማሰራጨት፤ በገንዘብ በሞራልና በማቴሪያል ትግሉን ማገዝ ይጠበቅብናል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይውረዱልን ሲል ሕዝቡ አልጠየቀም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ እየጠበቀ ያለው ሥር ነቀል መሠረታዊ ለውጥ ነው፤ በመሆኑም እኔ እንደገባኝ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1ኛ-ከሕዝቡ የተውጣጣ፣ በሕዝብ የተመረጠ ሕዝቡን በሚያገለግል መንግሥት መተዳደር


2ኛ- የመናገር፣ የማሰብ፣ የመኖር፣ የመሥራት፣ የመንቀሳቀስና የመደራጀት መብቱ እንዲጠበቅለት

3ኛ-በገዛ ሀገራቸው ባይተዋርና ሁለተኛ ዜጋ ሳይሆኑ የመኖር መብት በእኩል ደረጃ መከበር፡፡

4ኛ-ሰው በሰውነቱ የሚከበርበት ሀገር ውስጥ መኖር እንጂ ብሔሩና ነገዱ እየተቆጠረ የሚጠቃበትና የሚገደልበት ሀገር ውስጥ ያለመኖር

5ኛ-ኢትዮጵያኖች የሚፈልጉት የሚያምኑት፤ የሚጠብቃቸውና የሚያስከብራቸውን መንግሥት እንጂ አገራቸውን እየሸነሸነ የሚሸጥባቸውና ልጆቻቸውን በየጎዳናው የሚገልባቸውን አይደለም፡፡

በአጠቃላይ ኢትዮጵያውያኖች የሚጠይቁት በሠለጠነው ዓለም መሠረታዊ የሰው መብት የሚባሉትን ጥያቄዎች ነው፤ እነዚህ ጥያቄዎች ደግሞ ትክክልና አግባብ ያላቸው ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ነገር ግን ይህ ቀኝ ገዥ መንግሥት ‹‹የኢትዮጵያ ዕድገት ደረጃ ገና ለዴሞክራሲ አላበቃትም፤ አዲስ ለተወለደ ልጅ ሥጋ



የመስጠት ያህል ነው›› እያለ ይሳለቃል፡፡ ሕዝቡን ንቀውታል፡፡

ዛሬ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያኖች የታሪክ መሰቀለኛ መንገድ ላይ ቆመናል፡፡ ዛሬ የምንወስዳቸው እርምጃዎች የነገ ማንነታችን የሚወስኑ ይሆናሉ፡፡ ዛሬ የሰነቅነውን ነው ነገ ለልጆቻችንን የምናወርሰው፤ ማውረስ ያለብን ሰላምን፣ ብልጽግናንና ደስታን ከሆነ አንድነትን መፍጠር አለብን፡፡

ቀኝ ገዥዎቻችን ለበርካታ ዓመታት ከፋፍለው ገዝተውናል፡፡ መከፋፈላችን ደግም የድክመታችን ምንጭ ሆኗል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ያልተጎዳ ኢትዮጵያዊ የለም፡፡ ሐዘኑ በሩን ያላንኳኳበት ኢትዮጵያዊ የለም፤ “ለምንድ ነው አሁንም እየተገዛን ያለነው?” ብለን ብንጠይቅ መተባበር ስላቃተን ብቻ ነው፡፡ በተለያዩ ሰዎች ለበርካታ ጊዜ ‹‹አንድነት አንድነት›› ተብሏል ይሄንን ሐሳብ በተግባር የምናውልበት ጊዜ ደርሷል፡፡ ይመሩናል ያስተምሩናል ብለን የምንመካባቸው ሰዎች የሚቀጥለውን ጠቅላይ ሚኒስቴር ማነው? በሚለው ጥያቄ ላይ ጊዜ ሲያባክኑ አይተናል፡፡ ቀኝ ገዥ መንግሥት (ኢሕአዴግ) ማንን አምጥቶ በቦታው ላይ እንደሚጭን መነጋገር ወርቃማ ጊዜን ማቃጠል ብቻ ሳይሆን፤ ለእኔ ይሄ ሁኔታ ውኃ እንደ መውቀጥ ሆኖ ነው የሚታየኝ፡፡

ሲ..ኤን.ኤንና ቢቢሲን የመሰሉ ዓለም አቀፍ ጣቢያዎች የሚያደርጉትን የፖለቲካ ትንቢት ጨዋታ አሁን ጊዜውም ቦታውም አይደለም፡፡ ሕዝብ እየሞተና እየተሰደደ ያመጣውን የመንግሥት ሥልጣን መንገጫገጭ እንደ እዚህ አሳንሶ ማየት የሕዝቡን መሥዋዕትነት እንደ ማቃለል ይቆጠራል ብዬ ነው የማምነው፡፡ ሲ ኤን ኤ ን እና ቢቢሲ ያሉበት አገር ህዝቡ መብቱን ስለጠየቀ ብቻ ጠዋትና ማታ በጥይት አይደበደብም፡፡ የእኛ ሕዝብ ዛሬ እሳት ውስጥ ነው ያለው፡፡

ቀጣዩ ጠቅላይ ማኒስቴር የኢትዮጵያ ዴክላርክ ይሆናል ሲባል ሰምቻለሁ፡፡ የአፓርታይድ



ሥርዐትን ይበጣጥስልናል የሚል፡፡ ይሄ ህልም እንደውም ቅዥት ነው ለማለት እደፍራለሁ፡፡ የዛሬው ዋናው መልእክቴ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለተቃዋሚ ፖርቲዎች እንዲሁም አመራሮች ነው፡፡ መልእክቱም እንደሚከተለው ነው፡፡

ቀኝ ገዥዎቻችን እየደከሙና እየተፈረካከሱ ነው፡፡ ይሄንን እውነታ የሚደግፉ ብዙ ድርጊቶችን አይተናል፡፡ በተለይም ባለፉት የተወሰኑ ሳምንታት፡፡ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሥልጣን መውረድ ከእነዚህ ምልክቶች አንዱ ነው፡፡ ይሄ የሚያሳየው ወደ መጨረሻው መጠጋታችንን እንጂ አከተመ፣አለቀለት፣ ማለት አይደለም፡፡ እንደውም በበለጠ አስቸጋሪና መራራ የትግል ጊዜ እንደሚጠብቀን ማሰብ አለብን፡፡ ባለፉት 27 ዓመታት የተማርነውን ትምህርት ሳንረሳ የሚመጣውን ትግል ለማሳጠር መሞከር አለብን፡፡ አንድ እንሁን እንደጋገፍ፤ ቀኝ ገዥዎቻችንን (ኢህአዴግ) የሚታገሉትን ሁሉ እንደግፋቸው፤ እናክብራቸው፤ እርስ በርሳችን አንዘላለፍ፡፡ አንጠላለፍ፡፡ በቅርቡ ብዙ የሚያበረታቱ የአንድነት ተሞክሮዎች እያየን ነው፤ ይሄ እንዳለ ሆኖ የበለጠ አንድ የምንሆንበትን መንገድ እንፈልግ፤ አብረን እንቁም፡፡ በአንድ ድምፅ እንነጋገር ኢትዮጵያችንን እናስቀድም፡፡ እናት አገራችን ቀኝ ግዛት ላይ ናት፡፡ የእኛ ቀኝ ገዥዎች ነጮች አይደሉም፡፡ ይህንን እውነት መካድ አይቻልም፡፡ ቀኝ ገዥዎቻችን ከላይ እንደገለፅኩት ነጮች ሳይሆኑ እኛን ነው የሚመስሉት፡፡ አልገዛም ያለን እምቢተኛን ሕዝብ መግዛት አይቻልም፡፡ ታሪክ የሚያስተምረን በትግል በአንድነትና በሕዝባዊ እምቢተኝነት ብቻ ነው ቀኝ ገዥዎቻችን መጣል የሚቻለው፡፡

የራሳችን ባለቤት እንሁን፣ ታሪካችንን እናድስ፣ ሀገራችንን እናስመልስ፤ ዛሬ ጨልሞ ቢታይም አንዳንድ ጊዜ ተስፋ ቢያስቆጥርም ነገር ግን በመጨረሻ ድል ሁሌም የሕዝቡ ነው፤ እናሸንፋለን፡፡ ኢትዮጵያ ትቅደም፡፡

ምንጭ፡- ጤናዳማ ዩቲዩብ (tenaadam) ቻናል



በኃይሉ ገ/እግዚአብሔር

# «የምር ፖለቲካ አልወድም!»

ነገረኛው ነገረኛ ጥያቄ አምጥቶ አስደነገጠኝ፡፡

‹‹ወንድሜ!››

‹‹አቤት!››

‹‹ይህቺ አገር ወዴት እየሔደች ነው?››

ሞኝህን ፈልግ፤ ዝም ጭጭ:: ከኤፍቢ ግሮሰሪ መውጣቴ ነው፡፡ እዚህ ግሮሰሪ መቼም የሚመጣው፣ ለሙሉ ጤናው ሩብ ጉዳይ የሆነ ሰው ብቻ ነው፡፡ ታዲያ ከነዚህ ሰዎች ጋር እንዴት ማውራት ይቻላል!? …እንዴትም!

ተናድጃለሁ፡፡ ብቻዬን፣ ጥጌን ይዤ ከቢሜ ጋር እየተጫወትኩ፣ ከቴፑ የሚመጣውን የቴዲ አፍሮ፣ ‹‹ማታ ማታ ማልቀስ ነው ሥራዬ››ን እየሰማሁ፣ ደህና እየጠጣሁ ሳለ አንድ ቀዥቃዣ መጥቶ አጠገቤ ተቀመጠ፡፡ (ዲጄው ከአንዱ ጠጪ እጅ መንሻ ተቀብሏል መሰል ‹‹ማታ ማታ ማልቀስ ነው ሥራዬ››ን ደጋግሞ እየከፈተ ያሰቃየናል፡፡)

ሰውየው አጨብጭቦ የሚጠጣውን አዘዘ፡ ፡ ያዘዛትን ጥቂት እንዳጎደለ፣ ‹‹እሺ! …እንዴት ነው አየሩ?›› አላለኝም!? …በጥያቄው ግራ ተጋብቼ፣ ‹‹የትኛው አየር?›› አልኩት፡፡

‹‹የሀገሪቱ!››

‹‹ቀኑ ደመናማ ሆኖ ነበር የዋለው፤ አሁን ግን እንጃ!›› አልኩት፡፡

‹‹ኧረ እኔስ የጠየቅኩህ ሌላ ነበር!›› አለ መለኪያውን ወደ አፉ እየሰደደ፡፡

‹‹ምን ነበር የጠየቅከኝ!?››

‹‹የሀገሪቱን ወቅታዊ ጉዳይ ማለቴ ነበር!››

ደነገጥኩ፡፡ ‹የሚሰማን ሰው ይኖር ይሆን?› በሚል ግራ ቀኜን ገላመጥኩ፡፡ ከዚህ ሰውዬ ቶሎ መለያየት አለብኝ፡፡ ዘንድሮ ከማያውቁት ሰው ጋር፣ ፖለቲካ አይደለም የእግዚአብሄር ሰላምታም ከባድ ነው፡፡

የጠጣሁትን ከፍዬ ልወጣ አስተናጋጅ ስጠራ፣ ‹‹እውነት ግን ወንድሜ ይህቺ ሀገር ወዴት እየሔደች ነው?›› ብሎ ዋናውን ነገረኛ ጥያቄ ተንፍሶት ቁጭ፡፡ ፋራ ነኝ እንዴ እኔ ታዲያ፤ ባልሰማ ጭጭ፤

‹‹ማነህ ሒሳብ!›› አልኩ እየተጠንጠራራሁ፡፡

‹‹ወንድሜ!›› አጠገቤ የተቀመጠው ሰውዬ እየጠራኝ ነው፡፡

‹‹አቤት!››

‹‹ይህቺ ሀገር ወዴት እየሔደች ነው?››

ዝም፤ ጥርቅም፡፡ ጅል! ከፈለገ ሀገሪቱን ይዘዋት የሚዞሩትን ‹ሾፌሮች› አይጠይቅም!? ምን አገባኝ እኔ!? ‹‹ዝም ባለ አፍ ዝንብ አይገባም›› አሉ! …ሆ!

‹‹ኧረ እባካችሁ ሒሳብ ተቀበሉኝና ልውጣበት!›› ቤቱ ውስጥ ከወዲያ ወዲህ የሚራወጡ አስተናጋጆች ላይ እየጮኽኩ ነው፡፡

‹‹ወንድሜ እየሰማኸኝ ነው!?›› ይኼ ሰውዬ ዛሬ አልተወኝም፡፡

ዝም፡፡

‹‹ይህቺ አገር ወዴት እየሔደች ነው?››

አሁን አልቻልኩም፡፡ ‹‹ጌታዬ እምልልሃለሁ፣ ወዴት እንደ ሔደችም፣ እንደምትሔድም አላውቅም!›› አልኩ ቁጣ በተቀላቀለበት ድምፅ፡፡

አስተናጋጁ መጣ፡፡ ሒሳቤን ከፍዬ ነገረኛውን ሰውዬ ቻው ሳልለው ውልቅ፡፡

ከመጠጥ ጋር እንዲህ አንጉል ተነካክቼ ወደ ቤቴ መሔድ አልፈቀድኩም፤ ከኤፍቢ ወጥቼ ግድግዳ ወደሚጋራው ወተቴ ግሮሰሪ አመራሁ፡፡

…ገብቼ ገና ሁለተኛ ጃንቦዬን ከማጉደሌ ታዲያ፣ ‹‹የበላይ ልጅ ነኝና!›› የሚለው ሙዚቃ ተከፈተ፡፡ አልቻልኩም፤ ደሜ በጣም ሞቀ፡፡ ተነስቼ ወዘወዝ ማለት አማረኝና ተነሳሁ፡፡

‹‹የበላይ ልጅ ነኝ የዚያ ሳተና…›› …ተው ተው እስክስ! ስል፣ ባለጌ ወንበር ላይ የተቀመጠ አንድ ባለጌ ቁልቁል እያየኝ፣ ‹‹የገ/እግዚአብሔር ልጅ!›› በማለት ጠራኝ፡፡ እኔ ሆዬ እስክስታዬን አቁሜ ‹‹አቤት!›› አልኩ፡፡ እንዲህ በቅርበት የሚያውቀኝ መሆኑ ደንቆኛል፡፡

‹‹የገብረ እግዚአብሔር ልጅ!››

‹‹አቤት!››

‹‹የበላይነቱንማ ይዛችሁታል፤ ባይሆን ዘፈኑን እንኳ ለእኛ ተዉልን እንጂ!›› አላለኝም!? …ተበሳጨሁ፤ በጣም ተበሳጨሁ፡፡

‹‹አራት ስጠጣ አራት እሆናለሁ፤ አምስት ስጠጣ አምስት እሆናለሁ!›› አልኩ በጣም ተናድጄ፡፡

‹‹ምን አልክ?›› አለኝ ያው ባለጌ፡፡

ዓላማዬ የእሱ ቢጤን ማስፈራራት ነውና ጮኽ ብዬ ደገምኩለት፤ ‹‹ልትፈሩኝ ይገባል! አራት ስጠጣ አራት እሆናለሁ፤ አምስት ስጠጣ አምስት እሆናለሁ!›› አልኩ ድምፄን ወፈር አድርጌ፡፡

‹‹ሰዎች! ሰዎች!›› ሲል ጮኸ ሰውየው፡፡

‹‹ምንድን ነው?›› አሉት ሌሎች ጠጪዎች፡፡

ነገረኛው ሰውዬ ወደኔ እየጠቆመ፣ ‹‹ሰማችሁት? ‹አምስት ስጠጣ አምስት እሆናለሁ› እያለ ነው፤ ይሄን የወንበዴ ቡድን በረሃ ሳይገባ አሁኑኑ በቁጥር ስር እናውለው፤ አሁኑኑ!›› ቤቱ በሳቅ አውካካ፡፡ ምንድን ነው ነገሩ? ምን ሆኗል ሰዉ? ፖለቲካን የምፈራው እኔ ብቻ ነኝ እንዴ!?

‹‹እውነትም መጠጥ ቤት ውስጥ መንግሥት ወርዷል!›› አልኩና የጠጣሁበትን ሒሳብ ከፍዬ ወጣሁ፡፡

ከመንደሬ ራቅ ብዬ ለመጠጣት ወስኜ በብዙ ረዣዥም የታክሲ ሰልፎች መሃል ግራ ተጋብቼ ቆሜያለሁ፡፡ የእኔ ሰልፍ የትኛው እንደሆነ በማሰብ ላይ ሳለሁ፣ ‹‹የት ነህ?›› የሚል ጥያቄ ከወደ ኋላዬ መጣ፡፡ የታክሲ ተራ አስከባሪ ነው፡፡ ‹‹ወንጀልን በጋራ እንከላከል!›› የሚል ቢጢሌ ሰማያዊ ሻማ ልብስ የለበሰ ጭርምትምት ያለ ወጣት፡፡

‹‹ይኼ የምን ሰልፍ ነው?›› ራሴ ጠየቅኩት፡፡

‹‹የመገናኛ!›› መለሰ ልጁ፡፡

‹‹ይኼኛውስ?››

‹‹የካዛንቺስ!››

‹‹ይኼስ?››

‹‹የፒያሳ!”

“ያኛው ሰልፍስ?”

“የሃያ ሁለት!”

“እዚያ ጋ ያለው ረዥሙስ?”

ተራ አስከባሪው ተበሳጨ፤ ‹‹ሰውዬ የፈለግከው ሰላማዊ ሰልፍ ነው እንዴ!?

‹‹ኣ! ምን!?›› ደንግጫለሁ፡፡ የልጁ ንግግር ጆሮው የደረሰ ምድረ ሰልፈኛ ሁሉ እየሳቀ ነው፡፡

‹‹በሕግ አምላክ! እኔ ፖለቲካ አልፈልግም!›› ልጁ አልሰማኝም፡፡ የሚፈልገውን ተናግሮ ጀርባውን ሰጥቶኝ ሔዷል፡፡

‹‹ሰውዬ የፈለግከው ሰላማዊ ሰልፍ ነው እንዴ!?›› አለ፤ እውነትም ይህቺ ሀገር ወዴት እየሔደች ነው!?

ጥቂት በእግሬ እንደ ተጓዝኩ ታክሲ አግኝቼ ገባሁ፡፡ ከሹፌሩ አጠገብ ቁጭ ብያለሁ፤ ከተከፈተው ቴፕ የበገና መዝሙር ይደመጣል፡፡

‹‹አንተ ጎዳና አንተ መንገድ
ሰው እንዳይሔድ የለም፤
ሰው እንዳይሔድ!››

ተበሳጨሁ፡፡ ‹‹በመዝሙር ስም የምን አድማ መጥራት ነው!?›› እያልኩ ሳጉረመርም የሚከተለው ግጥም ተከትሎ መጣ፡፡

‹‹እኔ ምንዝሩ ችግረኛ
ጦም መፍቻዬን የት አገኛ?
ሁሉ ያላችሁ መኳንንት፤
እንደያዛችሁ ፍቱት!››

የማዳምጠው መዝሙር ሳይሆን ቅስቀሳ መሰለኝ፡፡ እግዚሃር ይስጠውና ሾፌሩ መዝሙሩን ዘግቶ ሬዲዮ ላይ አደረገው፡፡ አእምሮዬ፣ ‹‹ሁሉ ያላችሁ መኳንንት፤ እንደያዛችሁ ፍቱት!›› የሚለው ሐረግ ላይ ቀርቷል፡፡

በዚህ መሃል ድንገት ሾፌሩ በብስጭት የመኪናውን መሪ በኃይል ደበደበው፡፡ ደነገጥኩ፡፡

‹‹ምን ሆንክ!?›› አልኩት፡፡

‹‹ይኼ ሰውዬ እያቃጠለን ነው!›› አለ በብስጭት፡፡

‹‹ማን ነው?››

‹‹አርሰን ቬንገር!››

‹‹ምን አድርጎ?›› ስለው፣ የተከፈተውን ሬዲዮ እንድሰማ በምልክት ጠቆመኝ፡፡


‹‹የአርሰናሉ አሰልጣኝ አርሰን ቬንገር ኮንትራታቸውን በሁለት ዓመት ማራዘማቸው ብዙ የስፖርት ሰዎችን አስገርሟል!›› አለ ሬዲዮኑ፡፡

‹‹ይውጡ! ይልቀቁ! ይብቃዎ!” የሚል ተቃውሞ በአየር እና በምድር እየቀረበበበት እሱ ግን ስልጣኑን ይዞ ሙጭጭ!›› ሹፌሩ አሁንም መሪውን ደበደበ፡፡

በዚህ ጊዜ የታክሲው ረዳታ አንገቱን ወደኛ አስግጎ፣ “እሱ ሰውዬ ግን የሔደው ከደደቢት በረሃ ነው እንዴ!?” አለ፡፡ ረዳቱና ሹፌሩ ተሳሳቁ፡፡ እኔ ግን ተኮሳተርኩ፡፡ ቆይ ፖለቲካ የማልሰማበት የት ልሒድ!? ኧረ የት ልሒድ!?

‹‹ወራጅ አለ! እዚህ ጋ ወራጅ!›› እንደ መብረቅ ጮኽኩ፡፡ ታክሲው ቆመልኝ፡፡ ወረድኩ፡፡ …እውነት ይህቺ አገር ወዴት እየሔደች ነው!? አ! ይቅርታ ይኼ ሕዝብ ወዴት እየሔደ ነው!?

# የማይሆን የማይሆን ሆነና ሥራችሁ
# እነማን ነበሩ ታሰኙናላችሁ



**ሁሴን ከድር**

ዛሬ ጥቂትም ቢሆን ስለ አርበኛው ዑመር ሰመተር ታሪክ እናወጋለን፡፡ ደጃዝማች ዑመር ሰመተርን ማስታወስ ያሰኘኝ ጀግንነትን የመተረክ ኩራት ተሰምቶኝ አይደለም፡፡ ዑመር ሰመተርን ማስታወስ ያሰኘኝ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቴን በስማቸው በተሰየመ ትምህርት ቤት ውስጥ በመማሬ ትዝታ ተቀስቅሶብኝ ትዝታዬን ላጋባባችሁ ፈልጌም አይደለም፡፡ የአድዋ 122ኛ ዓመት በዓል ማግስት ላይ ነንና ደጃዝማች ዑመር ሰመተርን እናነሳሳ ለማለት አስቤም አይደለም፤ ቀድሞ ነገር ዑመር ሰመተር በዐድዋ ድል ወቅት የ17 ዓመት ጎረምሳ ነበሩ፡፡ ጀግንነታቸውም በአምስት አመቱ የጣልያን ወረራ ወቅት እንደነበር ይታወቃልና፡፡

‹እህሳ ሆድህ ምን አንካካ ቢኖር ነው?› ያላችሁ እንደሆን በስተመጨረሻ የማወጋችሁ ተከር(ጉዳይ) ገጥሞኝ ነው፡፡

አንድ አፍታ ወደ አርበኛው ዑመር ሰመተር ታሪክ ልለፍ፡፡ የተወለዱት በኦጋዴን ‹ከልካዩ›› የተሰኘ ስፍራ በ1871 ነበር፤ በአካባቢያቸው ልማድና ወግ መሠረት በልጅነታቸው መድረሳ በመግባት ቁርአንና ኪታብን በመቅራት አሳለፉ፡፡ እድሜያቸው ለብስለት ደረጃ ሲደርስም በሱማሌ ክልል ኤልቡር ወረዳ የሱልጣን ዓሊ ዩሱፍ እንደራሴ በመሆን በቃዲነት እና በአስተዳደርነት ለ23 ዓመታት አገልግለዋል፡፡

እብሪተኛው የጣሊያን ጦር በአድዋ የተቀበለው ሽንፈት 40 ዓመት ሙሉ ሲተናነቀው ኖሮ ዳግም ኢትዮጵያን ለመውረር በቃጣበት ወቅት ዑመር ሰመተር በአድዋ ጦርነት ያጡትን እድል ዳግም እንዳያጡት በመስጋት ‹ሥልጣን ከሀገር ሰላም በኋላ› በማለት ካባቸውን አውልቀው፤ የጦር ዝናራቸውን አጥልቀው ወደ ዱር ገቡ፡፡ በወልወል ጣሊያን የለኮሰው እሳት መላው ኢትዮጵያን እንዳያከስል በመስጋት በዱር ገደሉ ከተሰለፉ አርበኞች ጋር በመሆን የሀገር ግዳጃቸውን መወጣት ጀመሩ፡፡ ወትሮም ወራሪ በመጣ ቁጥር ቀድሞ የሚያጠቃው በጠረፍ ያሉ ኢትዮጵያውያንን በመሆኑ የዳር ሀገር ሰው የጦርነት ልምዱን አዳብሯል፡፡

የደጃዝማች አፈወርቅ ወልደሰማያት ረዳት ሆነው ጠላትን በገባበት እንዲወጣ ያደፈጡት ዑመር ሰመተር ጉርለጉቤ በተባለ ቦታ መሽጎ የነበረው የጠላት ጦር የእሳቸውን ጦር መቋቋም እስኪያቅተው ድረስ አፍነው ትንፋሽ አሳጡት፤ ድል በድል እየተቀዳጁም ሄዱ፡፡ የዑመር ሰመተርን ኃያልነት የተረዳው የጣሊያን ጦር አልቡር ላይ ስድስት ባታሊዮን ጦር በመያዝ የዑመር ሰመተርን ጦር ከበበው፡፡ ዑመር የጠላት መጠናከርና ብዛት የሚያመጠው አደጋ ታይቷቸው ጦራቸውን ይዘው ፈትለክ በማለት ከአደጋው አመለጡ፡፡

ከየአካባቢው አርበኞችን በማሰባሰብ ጦራቸውን ለከፍተኛ ተጋድሎ ማደራጀት ጀመሩ፡፡ ለአምስት ወራት እቅድ በመንደፍና ጦር በመመልመል ከቆዩ በኋላ በ1930 በአንዱ ቀን ሌሊት ጠላት በተዘናጋበት ሰአት ድንገተኛ አደጋ በማድረስ የጣሊያንን ጦር ፈቱት፤ ስድስቱንም ባታሊዮን ዶግ አመድ አደረጉት፡፡ ከላይ ታች መውጫ ቀዳዳ በማሳጣት አርበተበቱት፤ ግማሹን ለጥይት ግማሹን ለምርኮ ዳርገው በጀግንነትና በድል አጠናቀቁ፡፡ ዮሐንስ አድማሱ በ‹‹እስኪ ተጠየቁ›› የግጥም መጽሐፉ ውስጥ የሚያወሳው ጀግና ዓይነት ሆኑ፡፡

የወለደች እናት አምጣ፣
ለሙያ ሚውል ሰበዝ ግራምጣ፣
የሚያደባልቅ ዲቡን ከዲብ፣
ፈጥኖ የሚያረካ የቆንጆ ልብ፡፡
ክንዱ ያንበሳ መቸ የሌላ
ለጠላቱ እግር ክፉ አሜኬላ
አንደበቱ ጦር ቃሉ ምሳር
የሚቆራርጥ ሲሰነዝር፡፡
ወኔው ኃይለኛ ሰደድ እሳት፣
የሚለበልብ በሄደበት፡፡
ክንዱ ያንበሳ ቁጣው ግስላ፣
መካች የሌለው ደሙ ሲፈላ፡፡….

ዑመር ሰመተር ከጠላት የማረኩትን መሣርያ በመሰብሰብ ድጋሚ ሺላቦ የተባለ ቦታ መሸጉ፡፡ የጠላት ጦር ሺላቦ ድረስ በመምጣት ቂሙን ለመበቀል ከአንድም ሁለቴ ሞከረ፤ ሆኖም ክንደ ብርቱው ጀግና ጠላትን አሳፍረው መለሱ፡፡ ከሺላቦ ወደ ቆራሄ በማምራት ከአርበኞች በሚላክላቸው ጦር በመታገዝ ሌላ ድል ተቀዳጁ፡፡ ደገሃቡር ላይ ከጦር ጓዶቻቸው ጋር ተገናኝተው ለሌላ ግዳጅ የፊታውራሪነት ማእረግን ጭነው ተንቀሳቀሱ፡፡ ደጃዝማች ገብረማርያም ከኦጋዴን ወታደር መልምለው እንዲቀጥሩ አድርገዋቸው እንደነበርም የታሪክ ዘጋቢዎች ያወሳሉ፡፡

ፊታውራሪ ዑመር ሰመተር በጉርላጉቤ፣ በቆራሄ፣ በሃነሌ እንዲሁም በተሳተፉባቸው የጦር ሜዳዎች በሙሉ ጀግንነትና ወኔ እንዲሁም በታላቅ የሀገር ፍቅር ስሜት ተዋግተው የሃገራቸውን ክብር ከፍ ያደረጉ ጀግና ናቸው፡፡ አቶ ዋለልኝ እምሩ የተባሉ ጸሐፊ በጻፉት መጽሐፍ ገጽ314 ላይ ዑመር ሰመተር እንዲህ ማለታቸውን ጠቅሰዋል፡-

‹‹የሐገሬን ሕዝብ የፈጀው ጠላት በጀግኖች ክንድ ተረግጦ ሲወጣ በዐይኔ ተመልክቼዋለሁ፡፡ የመገዛት የመዋረድና የመረገጥ እድል ምን እንደሆነም አይቻለሁ፡፡ እንደጠራራ ንብ ከየምሽጉ እየገቡ የሚነድፉ ኢትዮጵያውያን ዘር በመሆኔ ኮርቻለሁ፡፡ በታሪክ የሰማሁትን የአድዋ ጀግኖች ጀብዱ ለማስመስከር ልጆቻቸው በኦጋዴን የጣሊያንን አንገት ስንቆርጥ አይቻለሁ፡፡ የዚህ ሕዝብ ልጅ በመሆኔ አሁንም እኮራለሁ፡፡…..››

ፊታውራሪ ዑመር ሰመተር ከደጃዝማች አፈወርቅ ወልደሰማያት ጋር አብረው ጣሊያንን ባስጨነቁበት ሜዳ አፈወርቅ ሕይወታቸው ሲያልፍ ዑመር ሰመተር የአርበኛውን ወኔ በመጠበቅ እያበረታቱ በሚያዋጉበት ወቅት በጠላት ዒላማ ውሥጥ ገቡ፤በተከታታይ በዘነበባቸው ጥይት ሕይወታቸው ብትተርፍም ጥቃቱ ለከፍተኛ ጉዳት ዳረጋቸው፡፡ በሸክም ወደ ጅጅጋ ለከፍተኛ ሕክምና እንዲሄዱ ተደረገ፤ በሰውነታቸው የተሰገሰጉት ጥይቶች በሀገር ውስጥ ሕክምና ተለቅመው የሚወጡ አልሆኑም፡፡ ዑመር ሰመተር ሕመማቸው በጦር ሜዳ የማያውላቸው ቢሆንም እሳቸው ግን አርበኛውን ደጀን ሆነው ከመርዳት አልተቆጠቡም ነበር፡፡ የጦር መሣርያ የሚገኝበትን ዘዴ በማመላከት፣ ህዝባቸው ንብረቱን ሽጦ ጥይት እንዲገዛ በመቀስቀስ ለአርበኞች የመሳርያ አቅርቦት እንዳይጓደል አድርገዋል፡፡

ቁስላቸው እየጠና ሕመማቸው እየጨመረ በመሄዱ መጀመርያ ወደ ሐርጌሳ ቀጥሎ ወደ ኬንያ ከዚያም ወደ ለንደን ለከፍተኛ ሕክምና ተሻገሩ፡፡ በሰውነታቸው ውስጥ የገቡትን ጥይቶች ከሰውነታቸው ማውጣት ለለንደንም ሊሳካላት የቻለ አልነበረም፤ በለንደን እስከ1933 ከቆዩ በኋላ ጠላት ሀገራችንን ለቆ ሲወጣ ወደ እናት ሀገራቸው ተመለሱ፡፡

በነጻነት ማግስት ንጉሱ ለፊታውራሪ ዑመር ሰመተር የደጃዝማችነት ማእረግ በመስጠት የኦጋዴንና የጅጅጋ አውራጃዎች ገዥ እንዲሆኑ ሾሟቸው፡፡ ሆኖም ሕመማቸው የተረጋጋ ሕይወትን እንዲኖሩ አላደረጋቸውም፡፡ በሀገር ውስጥ በተለያዩ ሐኪሞች በሕክምና ቢታገዙም መዳን ባለመቻላቸው በተወለዱ በ61 ዓመታቸው መጋቢት 10 ቀን 1936 ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ፡፡ ዑመር ሰመተር ከሞቱ ዘንድሮ 74ኛ ዓመታቸውን ይይዛሉ፡፡ ደጃዝማች በአንድ ወቅት እንዲህ ማለታቸውን አዲስ ዘመን ጋዜጣ በ1977 እትሙ ዘግቦ ነበር፡-

‹‹…ኦጋዴን በጦር ሜዳ ፣ሐረር ጠቅላይ ግዛት በአስተዳዳሪነት ሳለሁ እንዳሁኑ የአልጋ ቁራኛ ከመሆኔ በፊት ከምእራብ፣ከሰሜን፣ከደቡብ እንዲሁም ከመሃል ኢትዮጵያ የመጡ የሃገሪቱን ተወላጆች ተመልክቻለሁ፡፡ ከነደጃች ነሲቡና ከነደጃች አፈወርቅ ጋር ሆኜ ተዋግቻለሁ፡፡ ሌላውን ኢትዮጵያዊ ከኦጋዴን ሱማሌ የሚለየው አንዳችም ነገር አይቼ አላውቅም፡፡ ባሕል፣ቋንቋና ሃይማኖት ሌላ ጉዳይ ነው፤ ስለዚህ ምኞቴ በምስራቅ ክፍላችን ያሉ የተበታተኑ ሶማሌዎች አንድ ሆነው ኢትዮጵያዊነታቸውን ሲያስከብሩ ይታየኛል፡፡…››

ለእኚህ ታላቅ አርበኛ ሀገር ወዳድ ዜጋ ለስማቸው መጠሪያ ይሆን ዘንድ አንዋር መስጅድ አጠገብ የመስጅዱ ንብረት በሆነ መሬት ላይ የመጀመሪያና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተሠርቶ ታሪካቸው እንዳይረሳ ሀገር ስትጥር ቆይታለች፡፡ ይህ ትምህርት ቤት እስከ ቅርብ ዓመታት ድረስ ተገቢውን ግልጋሎት ሰጥቷል፡፡

በአሁኑ ሰአት የአባቶቻችንን ለሀገር የተከፈለ ትክክለኛ ታሪክ ትውልዱ የሚያውቅበት አጋጣሚ እየመነመነ መጥቷል፡፡ የደጃዝማች ዑመር ሰመተር ት/ቤት ዛሬ የተማሪዎች ዕውቀት መቅሰሚያ ሳይሆን የፖሊሶች መዋያ ሆኗል፤ የዚህ ምክንያትም በግልጽ አይታወቅም፡፡

ከ1970ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ ትምህርት ቤቱ ከቦታው እንደሚነሳ፤ ቦታው የመስጅዱ በመሆኑ መስጅዱ የማስፋፍያ ሥራውን እንደሚሰራ በወቅቱ ተማሪዎች ለነበርን ሕፃናት ሲነገረን ቆይቶ በቅርቡ ተግባራዊ ተደርጎ አይተናል፡፡

ጀግናው ዑመር ሰመተር ለሀገራቸው ለከፈሉት መስዋእትነት መታወሻቸው ምን ታስቦ ነው ት/ቤቱ የተነሳው? የሀገር ባለ ውለታዎች ዘመን በተለወጠና ሕዝቦች አዳዲስ ፍላጎቶችን ባመጡ ቁጥር አሮጌ ተብለው ሊጣሉ ነው ማለት ነው?... በዑመር ሰመተር የሚጠራ ጎዳናም ሆነ ሆስፒታል፣ መንገድም ሆነ ሃውልት በሌለበት ት/ቤቱን አፍርሶ ምትክ አለመስጠት ለጀግናው ክብር መንፈግና ውለታ መብላትን አያሳይምን? ይህ በአስቸኳይ ሊታረም የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ የአርበኞች ማኀበር፣ትምህርት ሚኒስቴር፣የቅርስ ጥበቃም ሆነ የባህል ቢሮዎች በእንዲህ ዓይነት ጉዳዮች ላይ ድምጻቸውን ሊያሰሙ ይገባል፡፡

በሌላ ጊዜ በቂ ሃሳብ ካገኘን እንመለስበታለን፡፡ ውድ አንባብያን በጉዳዩ ዙርያ የተሰማችሁን ለዝግጅት ክፍሉ ብትሰዱ ይደርሰናል፡፡ ቸር እንሰብት፡፡



መስፍን ጌታቸው

# እውነት ሐቅ እና ቅንነት

እነዚህ እሴቶች ለአምላክ ካለን ቀናኢነት የተነሣ ከፈጣሪ የወረስናቸው ብቻ ሳይሆኑ፤ ከእናታችን ሆድ ስንወጣ አብረውን የሚወለዱ መልካም እሴቶች ናቸው።

ለዚህ ነው በአካል የምንበልጣቸውና በመንፈሳዊ ንጽሕና በጣም የምናንሳቸው ሕፃን ልጆቻችን እኛ ውሸት እስክናስተምራቸው ድረስ ፍፁም ቅን እውነተኛና ሐቀኛ የሚሆኑት። አንድ ሕፃን ልጅ አባቱ ወይም እናቱ ውሸት እንደሚናገሩ ባወቀባት የመጀመሪያ ቀን የሚሰማውን መሳቀቅና ባዶነት ባሰብኩ ቁጥር በጣም ይዘገንነኛል።

ልጆቻችን ውሸት እንደምንናገር ያወቁና የሰሙ ዕለት ያኔ ከፈጣሪ ጋ ያላቸው መንፈሳዊ ቁርኝት መላላት ይጀምራል። እያደር ቅጥፈታችን እየሰፋና እያደገ ሄዶ የነሱ ጨቅላ አእምሮ "እዚህ ዓለም ላይ በስኬት የመኖሪያውና የማሸነፊያው ጥበብ ውሸት ነው" ብሎ ያመነ ዕለት ከፈጣሪያቸው ጋ እስከመጨረሻው ተቆራርጠው ይቀራሉ።

ከዚያ በኋላ ቤተክርስቲያን ብንወስዳቸው ቁራን ብናስቀራቸው የሥነ-ምግባር ትምህርት ብናስተምራቸው ዋጋ አይኖረውም። ከውሸት እየተላቀቁ ከመሄድ ባለፈ መቼም ቢሆን ከሐቅ ከእውነትና ከቅንነት ጋ ሊታረቁ አይችሉም።

ጓዳ ውስጥ የተጀመረ ውሸት ቀስ በቀስ ከቤት ይወጣና ሰፈር ውስጥ ከሌሎች ቤቶች ከወጡ ውሸቶች ጋ በመቀላቀል ይፈረጥማል። ከየሰፈሩ የተውጣጡ ፈርጣማ ውሸቶች በከተማ ደረጃ ሲሰባሰቡ ማንም ችሎ የማይጥለው ትልቅ አውሬ ይፈጥራሉ። እያንዳንዱን ከተማ የሚወክሉ የውሸት አውሬዎች በአገር ደረጃ ተሰባስበው ሲገጥሙ ደግሞ የትኛውም የተላቀቀ ሐኪም በምንም ዓይነት መድኃኒት ሊፈውሰው ወደ ማይችለው አስከፊ ወረርሽኝነትና ገዳይ በሽታነት ይቀየራሉ።

እናም ከመላው ቤተሰብ ጋ በመተባበር ጓዳ ውስጥ ቀፍቅፈን ያሳደግነው፣ ከጎረቤቶቻችን ጋ ተረዳድተን ያፈረጠምነው ከቢሮክቶች ጋ በመተባበር አውሬ ያደረግነው በአገርና በሃይማኖት መሪዎች ቡራኬ ወደ ገዳይ ወረርሽኝነት የቀየርነው ውሸት ወደየ ጓዳችን በመመለስ በየቀኑ እያሳቀቀና እየደቆሰ እኛንም መልሶ ሲገለን ይኖራል።

እውነቱን ለመናገር ዛሬ ኤች አይ ቪን ጨምሮ አገር ውስጥ ያሉ በሽታዎች በጠቅላላ የትራፊክና የተፈጥሮ አደጋዎች እኛን ብቻ ሳይሆን አካባቢያችንና አገራችንን ጨምር በየቀኑ እየገደለን ነው የሚገኘው። ነገር ግን እነዚህ ሁሉ ችግሮች ካደረሱብን ውድመትና የሞት አደጋ ይልቅ የቅንነት መጥፋት፣ የሐቅና የእውነት ከህገራችን ተጠራርጎ መጥፋት ያደረሰብን ሰብአዊና አገራዊ ግድያ በጣም እጅግ በጣም ይበልጣል።

የፍትሕ መዛባት ምንጩ ሌላ ምንም ሳይሆን ጓዳችን ቀፍቅፈን ያሳደግነው ውሸት ነው። ግፍ የበረከተው፣ ሙስና የተስፋፋው፣ በሥልጣን መባለግ ለከት ያጣው፣ የጦርነት ነጋሪት በየአቅጣጫው ሲጎሰም የሚሰማው፣ ስግብግብነት የበዛው፣ ፍቅርና ርኅራኄ የጠፋው፣ መተማመን ብርቅ የሆነው፣ ጥርጣሬ ያለ ልክ የገነነው፣ ክህደት የበረከተው፣ ብዙ ገዳይ በሽታዎች በየጊዜው የሚጨርሱን፣ ሰው ሠራሽና የመኪና አደጋ ያለ ልክ የሚፈጀን፣ ድርቅ ያለ አንዳች ከልካይ በየዓመቱ እየተመላለሰ መጫወቻ ያደረገን ሌላ በምንም ምክንያት ሳይሆን፤ እውነትን አርቀን በመቅበራችን ሐቅና ቅንነትን ተረባርበን ድራሻቸውን በማጥፋታችን ነው።

መገናኛ ብዙኃን እውነተኛ ዜናና መረጃ ማስተላለፊያ መሆናቸው ቀርቶ ትልቅ የጥፋት መሣሪያ የሆኑት ለዚህ ነው። አንድ ማሕፀን ያፈራን፣ አንድ አይነት ጡት ጠብተን፣ በጦጣ ፍራንክ ተገበያይተን፣ ጢባ ጢቤ ተጫውተን፣ በበረኪና ላስቲክ ለተሠራች ዋንጫ ነጭ ላብ እስኪወጣን ድረስ ጭቃ ላይ እየተንከባለልን ተጋጥመን ያደግንበት ወንድማማችነታችን አፈር በልቶ እርስ በርስ መወነጃጀልና መካሰስ፤ አንዳችን ሌላችንን ለመቅበር ጉድጓድ መማስ የዕለት ተዕለት ተግባራችን የሆነው ለዚህ ነው። ግርማ ሞገሱ የሚያስፈራና ቃሉ ፈውስ የሆነ የሃይማኖት መሪ ያጣነው ለዚህ ነው። ወርቅ ላይ ተኝተን በድህነት የምንማቀቀው፣ ቤተ መቅደሳችን የረከሰው፣ የመስጊዶቻችን አዛን የምእመኑን ልብ ቀጥ በማድረግ ለሰላት ወደ መስጊድ የማይጠራው፣ በተመሳሳይ ሰዓት፣ በተመሳሳይ ቦታ የተሰጠ አንድ ጋዜጣዊ መግለጫ ሁለት የተራራቁ ተቃራኒ መልእክቶች የተላለፈበት መሆኑ የሚሰማው፣ የአንዳችን ስቃይ የሌላችን ደስታ፣ የአንዳችን ዐይኖች

**...መፈክራችን ሁሉ እንዴት እናቸንፋለን ብቻ ሊሆን ቻለ፤ የጋራ ጠላታችንን ሳይሆን የገዛ ወንድማችንን ገለን መቃብሩ ላይ መፎከርና ስለኛ ድል አድራጊነት ብቻ ሳይሆን፤ ስለሱ ሽንፈት ጠዋት ማታ በትዕቢት መደስኮር እንዴት ለሁላችንም ቀለለ...**

የሚያፈሱት የመከራ ዕንባ ሌላችን ልብ ውስጥ የተተከለችን የክፋት ቅጠል አጥግቦ የሚያሳድግ ውኃ የሆነው ለዚህ ነው።

እኛ ልጆቻችንን ባሕር ማዶ በመላክ ውድ ዋጋ ከፍለን እያስተማርን፣ ወንድም እኅቶቻችን እናቶቻቸው የሚያቦኳትና የተቀረውን ለቤተሰብ አባል የሚያቀምሷትን እፍኝ ዱቄት ፍለጋ ስደት ወጥተው ባሕር ሲበላቸውና የአሸዋ ማዕበል ውጦ ሲያስቀራቸው ምንም የማይመስለን ለዚህ ነው። ሰውን ያህል ክቡር ፍጡር በግፍ እንደ ውሻ ገለን በስሕተት ነው የሚል የንቀት መግለጫ ስንሰጥ ማልቀሱ ቀርቶ ትንሽ እንኳን የሐዘን ስሜት ፊታችን ላይ የማይታየው ለዚህ ነው።

ለዚህ ነው ፈጣሪ ፊቱን ያዞረብን፣ ለዚህ ነው ፍቅር፣ ሰላም ብርቅ የሆኑብን፣ ለዚህ ነው በረከት እርቆን የመከራ ሸክም የተጫነብን፣ ለዚህ ነው ሕልማችን ሁሉ በአስፈሪ ቅዠት የተሞላ የሆነብን። ለዚህ ነው የምናምነው ግለሰብ ቀርቶ ተቋም እንኳን የጠፋብን ለዚህ ነው....ለዚህ ነው...

ግን ለምን?...ለምን ራሳችንን ከፍቅር አሳንሰን አጎደልን፤ ሥራ ፍቅር አብዝተው የሚያቀነቅኑ ወገኖችን፣ የፍቅር መንገድ የሚጠርጉ መሲሆችን፣ እድገታችንን በፍቅር መሠረት ላይ እንገንባ፣ እራሳችንን በእውነት በሐቅና በቅንነት አጥምቀን ለሁላችንም እኩል የሆነች የጋራ ቤታችንን በፍቅር አጥነን ምድሪቱን በተስፋና በደስታ እናድምቅ የሚሉ መቀመጫ ማሳጣቱን ለምን መረጥን።

ሥልጣን ወይም ሞት የሚል መፈክር ስለምን የጠዋት ማታ ቋንቋችን ሆነ፣ ከኔ ሐሳብ ውጪ የሆነ ሌላ ሐሳብ፤ እኔ ሞቼ ተቀብሬ ካልሆነ በስተቀር በተአምር በሁለት እግሩ አይቆምም፤ በሚል ሐሳቡን ብቻ ሳይሆን የሐሳቡን ባለቤቶችም ከምድረ ገፅ ማጥፋት፣ ለታፈኑ ድምፆች ድምፅ መሆኑ ቀርቶ አስገድዶ ይበልጥ ማፈኑ፤ የፍቅርና የአንድነት ሐውልቶችን አፍርሶ ብዙ የጥላቻ ሐውልቶችን ማቆሙ ስለምን መለያ መታወቂያችን ይሆን ዘንድ ፈቀድን።

መፈክራችን ሁሉ እንዴት እናቸንፋለን ብቻ ሊሆን ቻለ፤ የጋራ ጠላታችንን ሳይሆን የገዛ ወንድማችንን ገለን መቃብሩ ላይ መፎከርና ስለኛ ድል አድራጊነት ብቻ ሳይሆን፤ ስለሱ ሽንፈት ጠዋት ማታ በትዕቢት መደስኮር እንዴት ለሁላችንም ቀለለ...እምነታችን ሁሉ ሁሌም ድል አድራጊነት ገሎ /ገኖ ካልሆነ/ በቀር ሊገኝ አይችልም የሚል ብቻ እንዴት ሆነ፣ አንሶና ዝቅ ብሎ ገሎ ሳይሆን ሞቶ ትልቅ ድል አድራጊ መሆን ይቻላል የሚለው ቃል እንደምን ከልቦናችን ተሰወረ?...

መቼ ነው ከፍቅራችን ጋ የተጣላነው፣ ማን ነው እምነታችንን ያረከሰው፣ ማን ነው ፈጣሪ የሰጠንን ንጽሕናችንን ያቆሸሸው...

እስኪ ከራሳችን ጋ የምንታረቅበት መልካም የተስፋ ቀን እንዲነጋ ሁላችንም በያለንበት ነፍሳችንን በንስሐ እናንፃ ፤እራሳችንን ቤታችንንና አገራችንንም በሐቅ፣ በቅንነት፣ በእውነትና በፍቅር አጥምቀን ሰላማችንን እናብዛ። ያ ካልሆነ ግን ሁላችንም የቀመምናትን የክፋት መርዝ ተግተን እራሳችን በቆፈርነው ጉድጓድ እራሳችን የምንቀበርበት ግዜ እሩቅ አይሆንም።



ብ/ጄነራል ተፈራ ማሞ ከኢህአዴግ ነባር ታጋዮች አንዱ ናቸው። ኢህዴንን ከተቀላቀሉበት የልጅነት ጊዜያቸው አንስቶ አብዛኛውን የእድሜ ዘመናቸውን በጦርነትና በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ ነው ያሳለፉት።

የዛሬ አስር አመት ገደማ "ከግንቦት ሰባት ጋር ግንኙነት ፈጥረዋል። መፈንቅለ መንግስት ለማድረግ ተንቀሳቅሰዋል" በሚሉና ሌሎች ተዛማጅ ክሶች ተጠርጥረው በህግ ቁጥጥር ስር ውለው የእድሜ ልክ እስር ተፈርዶባቸዋል።

በቅርቡ መንግስት ለፖለቲካ እስረኞች ምህረት ሲያደርግና በክስ ሂደት ላይ የነበሩትን ግለሰቦች ክስ ሲያቋርጥ በምህረት የተለቀቁት ብ/ጄነራል ተፈራ ማሞን የግዮን መፅሔቱ **ፍቃዱ ማ/ወርቅ** በተለያዩ ወቅታዊና አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ አነጋግሯቸዋል።

# "ሕወሓቶች ለሀገራዊ ጥቅምና ጉዳይ ደንታ የላቸውም"

## ብርጋዲየር ጄነራል ተፈራማሞ

**ግዮን፡- ትውልድና ዕድገትዎ የት እንደነበር በመግለፅ ብንጀምርስ?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡- የተወለድኩት በቀድሞው አጠራር ወሎ ክፍለ ሀገር በላስታ አውራጃ ጉማ ወረዳ በጭርጭራ ደብር ነው። እስከ 14 ዓመቴ ድረስ እንደ ማንኛውም የገጠር ልጅ ከብቶችና አዝመራ ስጠብቅ፣ አልፎ አልፎ አደን እያደንኩ ነው ያደግኩት። ከ14 ዓመቴ በኋላ በሕመም ምክንያት የተወለድኩበትን አካባቢ በመቀየር፣ የእናቴ ሀገር በሆነው አይና ሚካኤል ደብር ለአምስት ዓመት ኖሬአለሁ። እንግዲህ ወደ ትግሉ የገባሁት ከዚያ በኋላ ነው።

**ግዮን፡- ለእሥር የተዳረጉበት ምክንያት ምንድነው? መቼና የት ነው የተያዙት?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡- መነሻው በማንነታችን ላይ የተመሠረተ ጥቃት ነው። ሚያዚያ 16 ቀን 2001 ዓ.ም ዓርብ ዕለት ለእኔ ብቻ አንድ ሻምበል ኃይል ላኩብኝ። በዚያን ወቅት ጦር ኃይሎች ጎልፍ ሜዳ አካባቢ የመጀመሪያ ዲግሪዬን ሊደርሸፐ እየተማርኩ ነበር። ከደህንነት፣ ከፖሊሲ፣ ከመከላከያም ከበው የፍርድ ቤት ወረቀት አሳዩኝ። ከዚያም ወደ ቤቴ ወስደው በርብረው ወደ ማዕከላዊ ወሰዱኝ። በምርመራው ሂደት ላይ የተገኘ መረጃ የለም። እኛም የሄድንበት መንገድ ግልፅ፣ የተደራጀና የጋራ ስለሆነ ለመሸፋፈን ያደረግነው ሙከራ የለም። ምክንያቱም መከፈል ያለበትን ለመክፈል ዝግጁና ቁርጠኛ ነበርን። በማንነታችን ተጠቅተናል። በማንነቱ የተጠቃ ደግሞ መሥዋዕትነት ለመቀበል ዝግጁ ነው።

**ግዮን፡- የተመሠተረተባችሁ ክስ ምን ይላል? የፍርድ ሂደቱንስ እንዴት አዩት?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡- ክሱ የተደበላለቀ ነው፡፡ መጀመሪያ ስንቀርብ ‹‹ከግንቦት ሰባት ጋር ግንኙነት ፈጥራችኋል›› ተብለን ነበር። ብዙም ሳይቆይ መፈንቅለ-መንግሥት ብለው በዜናም አስጩኸው ለወጡት። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ደግሞ እኛን አስታከው ለመምታት የፈለጉአቸውን ሰዎች ቀላቅለው ‹‹ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዐቱን በኃይል ለመናድ›› በሚል እንደገና ለሦስተኛ ጊዜ አሻሽለውታል። ይህም አላረካቸውም መሰለኝ ‹‹የአድማ ስምምነት›› የሚል ተጨማሪ ክስ አመጡብን። የፍርድ ቤት ሂደቱንም ከአንድ ወር ከ20 ቀን በኋላ ከአራዳ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ወደ ልደታ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀየሩት። የልደታ ፍርድ ቤት ውሳኔን ጨምሮ፣ ጠቅላዩም፣ ሰበሩም በሙሉ ተደማምሮ 52 ቀናትን ነው የፈጀው። እዚህ ላይ ዋና ሥራቸው የነበረው ማጣደፍ ነው። ምክንያት ክሱን ቶሎ ዘግተው እሥር ቤት ለማስገባት ነበር ሐሳባቸው። እኛም ፍርድ ቤቱ ፍትሕ ይሰጠናል የሚል ቅንጣት እምነት የለንም ነበር። ክስተቱ ግን ከ53ቱ መፈንቅለ መንግሥት ሞካሪዎች ጋር ይመሳሰላል። እነሱም በተለየ መንገድ በአጭር ጊዜ ነው የተፈረደባቸው። በወቅቱ ጄነራል መንግሥቱ ነዋይ ‹‹ለጭቁኑ የሀገሬ ሕዝብም እንዲህ የተፋጠነ ፍትሕ ብትሰጡ የእኔ መነሣት ባላስፈለገም ነበር›› ሲሉ የተናገሩትን ያስታውሰኛል። በነገራችን ላይ ጨፍጫፊ የሚባለው የደርግ አስተዳደር እንኳ በ1981 ዓ.ም መፈንቅለ መንግሥት የሞከሩትን መኮንኖች ጉዳይ በፍርድ ቤት ለመቋጨት አንድ ዓመት ገደማ ወስዶበታል።

**ግዮን፡- ማዕከላዊ ምን አጋጠማችሁ?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡- ማዕከላዊ የምድር ሲኦል ነው። ይህንን በተመለከተ በቅርቡ መንግሥት ራሱ ሲኦልነቱን አምኖ ወደ ሙዚየምነት እለውጠዋለሁ በማለት ቃል መግባቱ ቦታው ምን ዓይነት ተቋም እንደ ነበረ ስለሚነግረን የእኔ ምስክርነት አያስፈልገውም።

**ግዮን፡- በእርስዎ ላይ የተላለፈው ውሳኔ ምን ነበር?**

ጄነራል ተፈራ፡- የዕድሜ ልክ እሥራት።

**ግዮን፡- በእሥር የቆዩት ለረጅም ጊዜ መሆኑ ይታወቃል። እንደምትፈቱ ስታውቁ ምን ተሰማዎት?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡- አጠቃላይ እንደምንፈታ ደመ ነፍስህ የሚነግርህ ነገር አለ። በተለይ የሕዝቡ መነሣሣት፣ የሥርዐቱ ግፍ እየባሰበት መሄድ ጊዜ እንደማይወስድ ያሳየን ምልክት ነበር። ስለዚህ ለመፈታታችን ትልቁን ሚና የተጫወተው የሦስት ኃይሎች ዋጋ ይመስለኛል።

**ግዮን፡- የእነማን?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡- የኦሮሞ እና የአማራ ሕዝብ እየተናበቡ ያደረጉት ታላቅ ተጋድሎ እና የከፈሉት ከባድ ዋጋ ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ በውጪ ሀገር ያሉ ኢትዮጵያኖች ስለ እኛ ነፃ መሆን ያሰሙት ድምፅ ነው ልንል እንችላለን።

**ግዮን፡- ያለፉትን ዘጠኝ ዓመታት በቃሊቲና ዝዋይ ወኅኒ ቤት አሳልፈዋል፣ የሌሎች ታሳሪዎች ሁኔታ ምን ይመስል ነበር?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡- ከአማራና ከኦሮሞ ወጣቱ በገፍ እየተጋዘ ይታሠራል። ዕድሜ ልክ ፍርድን ጨምሮ፣ ሃያ አምስት ዓመታትን ያህል እያከናነቡ ወደ ማጎሪያዎቹ ለመላክ ከአሳማኝ ማስረጃ ይልቅ ኦሮሞ ወይም አማራ መሆን ብቻውን በቂ መሆኑን አስተውያለሁ፡፡ የአማራውና የኦሮሞው ተወላጅ በጅምላ ተፈርዶበት እሥር ቤቱን አጣቦታል። የየክልሎቹ መንግሥታትም ይህንን ግፍ ከመቃወም ይልቅ ለረዥም ጊዜ ተባባሪ መሆናቸው ጉዳቱን የከፋ አድርጎታል። ሰሞነኛውን የኦህዴድን እና ከፊል ብአዴንን ተቆርቋሪነት ሳንዘነጋ ማለቴ ነው።

**ግዮን፡- በእሥር ቤት ሳሉ የሀገሪቱን የፖለቲካ ሁኔታ ለማወቅ፣ ዜናዎችን በመከታተል መረጃዎችን ያገኙ ነበር?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡- አንችልም ነበር። ምክንያቱም በስፋት የምናገኘው የመንግሥት ሚዲያን ነው። እነሱ ደግሞ እንደምታውቁት በገዢው ፓርቲ ፕሮፓጋንዳ የተጠመዱ ናቸው! አልፎ አልፎ ከጠያቂዎቻችን ተባራሪ ወሬዎችን ከመስማት የዘለለ የምናገኘው መረጃ የለም። በዚህ ላይ ዘጠኙንም ዓመት በከባድ ጥበቃ ሥር እንዳሳልፍ መገደዴ ከመረጃ አርቆኛል።

**ግዮን፡- በእሥር ላይ እያሉ የጤናዎ እንዴት ነበር? ሕክምና ያገኙ ነበር?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡- ከሞላ ጎደል ጤነኛ ነኝ። ይሄ ማለት ግን ልታየው የሚገባ ችግር አልነበረብኝም ማለት አይደለም። ለምሳሌ በእግሬ ላይ ወደ ስድስት የፈንጅ ፍንጣሪ አለ። በተለይ በክረምት የቅዝቃዜ ወቅት መራመድ ያስቸግረኛል፤ ከፍተኛ ስቃይም ይፈጥርብኛል። በእሥር ቤት ሆነህ ሕክምና እፈልጋለሁ ብትል እንደ ቅንጦት ነው የሚታየው። ማስታገሻ ከመስጠት በስተቀር የረባ ሕክምና አገልግሎት አይሰጥም። ወደፊት ሁኔታዎች የሚፈቅዱልኝ ከሆነ ሕክምናዬን እከታተላለሁ።

**ግዮን፡- በላሊበላ የነበረው አቀባበል ምን ይመስል ነበር? የተሰማዎት ስሜት ምን ነበር?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡- እንደ ተፈታን ሕዝቡ እኛን ማግኘት እንደሚፈልግ የሚገልጽ መልእክት ላከብን። እኔና ጄነራል አሳምነው ፅጌ ሆነን ላሊበላ አየር ማረፊያ ስንደርስ ሕዝቡ መጥቶ ግጥም አለ። በከተማው ባሉ መንገዶች ሕዝቡ ዳርና ዳር ፍስስ ብሎ ወጥቷል። ከላሊበላ ወጣ ብለህ አይናና፣ ቆቦ ከሌሎችም ከቤቱ የቀረ የለም። ከወልድያ ሊጠይቁን የመጡ አሉ። ደስ ያለን ነገር ቢኖር ሥርዐቱ ብዙ ጊዜ “የግል ፍላጎታቸውን ለማሳካት ነው” እያለ ስማችንን ለማጥፋት ሞክሯል፤ ይሄ እንዳልተሳካለት ነው ከሕዝቡ ስሜት የተረዳነው። እኛ ለግል ፍላጎታችን ሳይሆን ‹‹በአንድ አገር ያሉ ሕዝቦች እኩል ይሁኑ! በአማራ ማንነት ላይ የተከፈተው ጥቃት ይቁም!›› የሚለውን ጥያቄ በማንሣታችን፣ ዛሬ ሕዝቡ ከእኛ በላይ ባለቤት አድርጎት ትልቅ ደረጃ እንዳደረሰው አስተውያለሁ። ይሄ የሚፈጥርብህ ስሜት አለ። ያሳለፍነውንም አሰቃቂ መከራ ያስረሳል። መታሠራችን ለሕዝባችን ዘላቂ ጥቅም በመሆኑም አንቆጭበትም።

**ግዮን፡- በስንት ዓመትዎ ትግሉን ተቀላቀሉ? ታጋይ ለመሆንስ መነሻዎ ምን ነበረ?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡- በ19 ዓመቴ አካባቢ በ1976 ዓ.ም ነው። ለትግል አንዱ መነሻ የሆነኝ ደርግ በዚሁ ዓመት ወደ እኛ አካባቢ ሲገባ፤ በዙሪያው ካሉ የዐፄው ሥርዐት ደጋፊዎች ጋር ውጊያ ገጥሞ ነበር። በዚህ ምክንያት አባቴም ‹‹ደርጉን አናስገባም!›› ከሚለው በኩል ነበረና ጥቃት ሰንዝረው አይና የሚባለውን የወረዳውን ከተማ ያዙት። ከዛ ደግሞ ላሊበላ ከተማ ባለው የደርግ ሠራዊት ላይ ጥቃት ከፍተው አንድ አየር በማቃጠል ደመሰሱት። በሁለቱ መሀል ውጊያው ቀጥሎ ደርግም በፈጣን መልሶ ማጥቃት ብርኬ ተብላ የምትጠራውን ትንሽ ከተማ ሙሉ ለሙሉ ሲደመስሳት መሸሽ ጀመርን። በስተሰሜን “መሪ” ወንዝ እና በስተደቡብ ደግሞ “ተከዜ” መሀል ወደ አለ ቦታ አፈገፈግን። ከዚህ በኋላም ከደርግ ጋ የሚዋጋ ኃይልን ሁሉ ወዳጅ የማድረግ ባሕል በአካባቢው ተጀመረ። ከዚህ በፊትም በ1974 ዓ.ም ‹‹የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ›› (ኢሕዴን) መጥቶ የኛን ወረዳ አጥቅቶ ከያዘ በኋላ አስተዳዳሪዎቹን እና የፖለቲካ አመራሮቹን ይዞ ወሰዳቸው። እኛ ቦታ ላይ በተደጋጋሚ ጊዜ የተለያዩ ውጊያዎች ተደርገዋል።

**ግዮን፡- ማን ከማን ጋር?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡- በ1975 ዓ.ም ኢሕዴን ከደርግ ጋር። ኢሕዴኖች እዚያ አካባቢ መንቀሳቀስ እንደ ጀመሩ ትግሉን ለመቀላቀል ስጠይቃቸው ዕድሜህ ገና ነው ብለው መለሱኝ። ያን ጊዜ ሰውነቴ ደቃቃ ስለሆነ እንጂ፤ ወደ ዐሥራ ስምንት ዓመት ገደማ ተጠግቼ ነበር። ኋላ ላይ ግን በ1976 ዓ.ም በቀጥታ ወደ ትግሉ ገባሁ።

**ግዮን፡- ወደ ትግሉ ከተቀላቀሉ በኋላ የነበረዎት የትግል ተሳትፎ ምን ይመስል ነበር?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡- ለዘጠኝ ወር መደበኛ ሥልጠና ወሰድኩ። ቀደም ብለን ስለ ገባን ሌሎች ሠልጣኞች ከተለያየ ቦታ እስኪሰባሰቡ ድረስ ሦስት ወር ትርፍ ሥልጠና ወሰድን። ከዘጠኝ ወር ጠንካራ ሥልጠና በኋላ በአምስት ተዋጊ ሻምበሎች ተከፍለን ተደራጀን። እኔም “በኃይል 73” ተራ ተዋጊ ሆኜ ተመድቤ በአምስት የተለያዩ ውጊያዎች ላይ ተሳትፌያለሁ። የመጀመሪያው “ሽምሽሃ” ላሊበላ አካባቢ አንድ አየር ለማገት የተደረገ ሲሆን፣ ግዳጁም የተሳካ ነበር። ሁለተኛው የ“ጨጨሆ” ነው። ቀጥሎ ማክሰኝት ላይ ነው። ከዚያም የደጎማ ውጊያዎችን ተሳትፈን ከበለሳ አቆራርጠን ወደ አርማጭሆ ስንገሰግስ በአይከል ዙሪያ ተደጋጋሚ ጦርነት አካሄድናል።

እነዚያን ውጊያዎች ከተሳተፍኩ በኋላ ለኮማንዶነት ተመለመልኩ። በአየር ወለድ ለአራት ወር የኮማንዶ ሥልጠና ወሰድኩና በኮማንዶ ክፍሉ ተዋጊ አባል ሆኜ፣ በሌሎች ወደ 12 የሚጠጉ ውጊያዎች ላይ ተሳተፍኩ። →

ከነዚህም አንዱ ሙሴ ባንብ በሚባልና ከትክል ድንጋይ ወጣ ብሎ በሚገኘው አካባቢ ያደረግነውና በሸንፈት ያጠናቀቅነው ዘለግ ያለ ውጊያ ነበር።

በአጠቃላይ ወደ 12 ውጊያዎች ላይ ተሳትፌአለሁ። ከዕብናት ውጊያ በኋላ ወደ አመራርነት በመንደርደር ዘጠኝ አባላት ያሉትን ጓድ መምራት ጀመርኩ። የጓድ መሪ ሆኜም ብዛት ባላቸው ተደጋጋሚና ጠንካራ ውጊያዎች ተሳትፌአለሁ። የመጀመሪያው የትግሌ ምዕራፍ በዚያ ላይ ከተጠናቀቀ በኋላ በሂደት ከፍ ወዳለ ደረጃ ተሸጋገርኩ።

**ግዮን፡- በትግል ሕይወትዎ ከፍ ወዳለ ደረጃ የተሸጋገሩበት ሁኔታ መቼ ተፈጠረ?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡- በ1980 ዓ.ም የመቶ መሪ ሆንኩ። ከዚያም 95 ተዋጊዎች ያሉት የአንድ ሻምበል አዛዥ ሆንኩ። በ1981 ዓ.ም ከኢሕዴን 2ኛ ድርጅታዊ ጉባዔ በኋላ ክረምቱ ላይ ከህወሓት ጋር የጋራ ሥልጠና አዲግራት አካባቢ አደረግን።

**ግዮን፡- የአዲግራቱ ሥልጠና ምንን ያማከለ ነበር?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡- በደርግ ሥርዐት ላይ ወታደራዊ መፈንቅለ-መንግሥት ሙከራ ስለተደረገ፤ ሁለቱ ድርጅቶች ፈጥነው ኃይላቸውን ወደ አንድ በማምጣት ኢሕአዴግን የመመስረት ሥልጠና ላይ ያተኮረ ነበር። በዚህን ጊዜ የሞርታር ሻምበል አዛዥነት ሥልጠና ወሰድኩ። ከሥልጠናው በኋላም "የዘመቻ ሰላም በትግል" ላይ የሞርታር ሻምበል አዛዥ ሆኜ ውጊያውን እንደጨረስኩ፤ በአሸዋ ክፍለ ጦር ውስጥ የአንድ ሻለቃ አዛዥ ሆንኩ። በወቅቱ የአንድ ሻለቃ አዛዥ ከ600 በላይ ተዋጊዎች ነበሩት። በቦረና የወታደራዊ እና በሀገረ ሰላም የፖለቲካ ካድሬ የተባሉ ትላልቅ ሥልጠናዎችን ለአራት ወር ወሰድኩ። ሥልጠናው እንዳበቃም የኢሕዴን የቴዎድሮስ ክፍለ ጦር ምክትል አዛዥ ሆንኩ። ብዙም ሳይቆይ የክፍለ ጦሩ ዋና አዛዥ መሆን ቻልኩ።

**ግዮን፡- በዚያ ፍጥነት አዛዥ የሆኑት በውጊያ ላይ ባሳዩት ልዩ ብቃት ነበር?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡- የተለያዩ የውጊያ ተሳትፎዎቼ እንዳሉ ሆነው፣ በዋናነት ግን የእኛ ኃይል አምቦ ላይ ማጥቃት ሰንዝሮ፣ በደርግ ሲገፋና በደሴ በኩል ያለው ኃይላችን ደግሞ እንዳይንቀሳቀስ ደርግ አስሮ ሲይዘው፤ የቴዎድሮስ ክፍለ ጦር በሁለት አቅጣጫ እንዲያጠቃ ግዳጅ ተሰጠው። አንደኛው አዛገፉ እና ሌሎች ኮሚቴዎች የሚመሩት በግራ አቅጣጫ ገብተው ጥቃት ሲፈጽሙ፤ ደርግ በወሰደባቸው የፀረ-ማጥቃት እርምጃ ወደ ሃምሳ ስምንት የሚሆኑ ታጋዮች፣ ሁለት ዲሽቃና ሁለት የውኃ ቦቴ ለምርኮ ተዳረጉ። እኔ በምመራው በኩል ደግሞ እስከ ማታ ድረስ እልህ አስጨራሽ የማጥቃት ውጊያ አካሄደን ሦስት ወታደራዊ መሬቶችን ለማስለቀቅ ያበቃንን ድል ተቀዳጀን። ከውጊያው በኋላም በረከት ስምዖን በመራው ግምገማ ላይ የኔ የአዋጊነት ሚና ብልጫ አሳይቶ ወደ አዛዥነት መጣሁ።

**ግዮን፡- አዛዥ ከሆኑ በኋላ ነው የደሴን ውጊያ የመሩት?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡- አዎ። የደሴን ውጊያ የመራነው ከወረ-ይመኑ በገራዶ አቅጣጫ ሲሆን፤ ወደ ኩታበር ያለውን በጀርባ ነበር ያጠቃነው። በመጨረሻም በደሴ አቅጣጫ ያለውን ነፃ አወጣነው። እንግዲህ ከተዋጊ አባልነት ጀምሮ በየደረጃው የአመራር ሂደቱን ተከትሎ እስከ ክፍለ ጦር መሪ የደረስኩት በእንዲህ መልኩ



አሜሪካ በጠራችው ስብሰባ ኢትዮጵያን ወክለው የተገኙበት 2008 እ.ኤ.አ ከግራ ወደቀኝ የመጀመሪያው ረድፍ ላይ ሚታዩት ብ/ጄነራል ተፈራ

ተፈትኜ ነበር። በወቅቱ ደግሞ በኢሕአዴግ አደረጃጀት ደረጃ ትልቅ ስም የነበረው የክፍለ ጦር አዛዥነት ነበር።

**ግዮን፡- መቼም በትግሉ ወቅት ፈታኝና አደገኛ አጋጣሚዎች አይጠፉም አይደል?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡- በጣም እንጂ። ለምሳሌ ያህል ሦስት ፈታኝ ውጊያዎችን ማንሳት እችላለሁ። ሲና ውስጥ እኔ ያለሁበት ቡድን ሲንቀሳቀስ፣ የቡድን መሪው የደርግ ወታደሮችን በርቀት አየና "ኑ እንመለስ" ብሎ ጥሎን ሄደ። እኛ ደግሞ "ምንድን ነው ሳይረጋገጥ የምንመለሰው?" ብለን እኔና ሞገሴ የሚባል ታጋይ ከአንድ ገበሬ ጋር በመሆን መሀላቸው ስንገባ ጦሩ እንቅልፍ ጥሎት ተኝቷል። መጀመሪያ የተገናኘነው ከዘበኛው ጋር ስለሆነ "ማነህ?" ስንለው "አንተ ማነህ?" ሲል ተኩስ ከፈተንበት። በዚያ ተኩስ የተኛው ጦር ተነሳና ድብልቅልቅ ያለ ውጊያ ተከፈተ። እኛ ሁለት ነን፤ ድጋፍ ለመጠየቅ እንኳ የመገናኛ ሬዲዮ አልያዝንም። ሙሉ ለሙሉ ተከበን በመጨረሻ መውጫ ስናጣ እኔ ጦሩን ማደናገር ስለፈለኩ፤ ትንሽ የዜና ሬድዮ አወጣሁና ዝም ብዬ ሃሎ ሃሎ አልኩኝ። ጦሩም ኃይል የመጣ መስሎት ግማሹ መሸሽ ሲጀምር፣ ክፍተት በማግኘታችን ዕድሉን ተጠቅመን አመለጥን።

ሌላኛው ከባድ ውጊያ በደቡብ አቅጣጫ ሦስት የአየር ወለድ ሻምበሎችና ዙ-23 ያለበት፣ ከአንድ ጉብታ ላይ ደግሞ በሰሜን በኩል አንድ ተጨማሪ ሻምበል የመሸገበት ነበር። የኛ ብርጌድ 73 የምንላት፣ የተወሰኑ የኢሕዴን አመራሮችና የሕወሓት ኃይሎች በጋራ ያሉባት ናት። የኢሕዴን ኮማንዶዎችና ተዋጊዎች ወዲያው እንደገባን አንዱን ሻምበል ጨረስነው። በደቡብ የገቡት ደግሞ ወደያውኑ ዙ-23ቱን መቱት። ግን የቀረው ኃይል ገትሮ ስለያዘን ብዙ ኪሳራ ደረሰብን። መጨረሻ እኛ ግቡ ስንባል ከአዲስ ዘመን አቅጣጫ በጀርባ ሰርገን ስንገባ፤ ኃይለኛ ጥቃት ተፈፀመብን። ሁለት የኮማንዶ መሪዎች ሲወድቁብን "ለጓዶቻችን ክብር" አልንና ምሽጉን ሰብረን አሰቃቂ የጨበጣ ውጊያ አደረግን። በዚያ የጨበጣ ውጊያ የሁለታችንንም ተዋጊዎች ሬሳ አወዳደቅና የሰውነታቸውን መፈራረስ ስትመለከት ራስህን መቆጣጠር ያቅትሃል። ያ ውጊያ ለወራት ከአዕምሮህ ሳይጠፉ በሐሳብህ ስለሚመላለስ ሌሊት አያስተኛም ነበር።

ሦስተኛው ከባድ ውጊያ ክስተት ነበረች። በ1980 ዓ.ም ግንቦት ወር ማይጨው ላይ የህወሓት ኮማንዶ አንድ ቦታ ላይ እያጠቁ እያለ ደርግ ገትሮ ይይዛቸዋል። ከረጅም ትንቅንቅ በኋላ አልሆን ሲል የኢሕዴን ተዋጊዎች ወደዚሁ ቦታ እንድንሄድ ተደረግን። ከውጊያው ቦታ ስንደርስ የህወሓት ታጋዮች "ቦምብና ጥይት ስለጨረስን የኢሕዴን ታጋዮች የታጠቁትን ፈትተው ይስጡን" አሉ። እኛም በጥያቄያቸው በጣም ተበሳጭተን "ዞር በል! ምን ብለን ነው ለእናንተ ጥይትና ቦንብ የምንሰጠው?! እናንተ በገባችሁበት እኛ እንገባለን" ብለን ተቃወምን። በዚህ ክርክር መሀል የበላይ አዛገፆች እኛ እንድንገባ ፈቀዱ። እንግዲህ ይህ ሁሉ ክርክር ለመሥዋዕትነት ከመቸኮል የመጣ መንፈሳዊ ቅናት ነው እንጂ ሌላ ነገር የለውም። ወዲያው አንዴ ማጥቃት እንደጀመርን ደርግ ተፍረክርኮ ወደመ፤ የተረፈውን ማርከን ወደ ማይጨው ከተማ ገባን።

**ግዮን፡- በህወሓት እና በኢሕዴን የጋራ ትግል ወቅት የአቅምና የኃይል ልዩነት ነበር?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡- ትግሉን የምናካሂደው በጋራ ነው። በውጊያ ተሳትፎ ላይ የህወሓት ኃይል በተዋጋበት የኢሕዴን ኃይልም ይዋጋል። ብዙ ጊዜ ህወሓቶች ከትግራይ ክልል ውጭ የውጊያ እቅድ ሲያወጡ ከኢሕዴን ጋር በጋራ ነው። በ1974ዓ.ም ኢሕዴን ገና እንደተመሠረተ አንድ የሻለቃ ኃይል ሲኖረው፤ ሕወሓት ግን ብርጌድ ሁኖ ሐሙሲት ላይ የጋራ ውጊያ አድርገዋል። በዚህ ወቅት ኢሕዴን የራሱን ድርሻ ይዞ ይዋጋል። ይህ አካሄድ እስከ መጨረሻው ነው የዘለቀው። በመጨረሻዎቹ አካባቢ በተደረገው የደርግ ድምሰሳ፣ የሕወሓት ታጋዮች በተሰለፉበት ሁሉ የኢሕዴን ተዋጊዎችም አሉ። ሁለቱም የየራሳቸውን ግዳጅ ነው የሚወጡት። ውጊያዎችን በጋራ ስንሳተፍም ያስተዋልኩት መጠነኛ ልዩነት የብዛትና የልምድ ጉዳይ ብቻ ነው። ለአብነት የመጨረሻዎቹ ጊዜያትን ብንወስድ ሕወሓት አስራ አንድ ክፍለ ጦር ሲኖረው፤ ኢሕዴን አምስት ክፍለ ጦር ነው የነበረው። ህወሓት ልምድ አለው። ይህ የሆነው ደግሞ እነሱ ከእኛ በሰባት ዓመት ቀድመው በመደራጀታቸው ነው። ይህም ሆኖ ግን መጨረሻዎቹን ዓመታት ከብዛት ልዩነቱ በቀር በብቃትና በጀግንነት ዕኩል ደረጃ ላይ ነበርን።



**...ከኑሮው ላይ እያጎደለ ያበላንና ያጠጣን የአማራ ሕዝብ "እናንተ መንገድ እየመራችሁ ይዘችሁ መጥታችሁ አዘረፋችሁን!" የሚል ብርቱ ተቃውሞ ማሰማት ያዘ...**

**ግዮን፡- የጠቀሷቸው ልዩነቶች በትግሉ ላይ የፈጠሩት ተፅዕኖ የለም ማለት ይቻላል?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡- ሁለቱ ድርጅቶች በጋራ በሚያደርጓቸው ውጊያ ወቅት ልዩነቶችና ችግሮች መፈጠራቸው የሚጠበቅ ነው፡፡ ጦርነት ወታደራዊ ሳይንስ በመሆኑ፣ ከነደፍከው ዕቅድ ውጪ ተገማች ያልሆኑ ጉዳዮች በሜዳው ላይ ስለሚገጥሙህ ችግር መኖሩ አይቀርም፡፡ በሁለቱም ወገን በውጊያ ላይ የሚታዩ ስሕተቶችም እንደነበሩ አይካድም፡፡ ምናልባት እንደ ችግር ሊጠቀስ የሚችለው ከሽምቅ ወደ መደበኛ ተዋጊነት ከተሸጋገርን በኋላ ቋሚ መከላከል ይዘን መዋጋት በመጀመራችን፣ ደርግም በአየርና በከባድ መሣሪያ ደጋግሞ ስለሚደበድብ የመጨነቅ ነገሮች ይፈጠራሉ፡፡ ይሄ ችግር ግን በሁለቱም ወገን የሚታይ ቢሆንም ብዙ ጊዜ ሕወሓቶች የኢሕዴንን ብቻ ለማጉላት ሲሞክሩ ይታያሉ፡፡ ይሁን እንጂ ተቀባይነት የለውም፡፡

ከዚህ ይልቅ ለህወሓት ፈታኝ የነበረበትን ሁኔታ ልግለፅልህ፡፡ ህወሓት ወደ ደቡብ ጎንደር እና ሰሜን ወሎ ሲገባ አብዛኛው ታጋይ "ከዚህ በኋላ የኔ አገር አይደለም፡፡ አልዋጋም!" የሚል ውሳኔ ላይ በመድረሱ ድርጅቱ መፍረስ ጀምሮ ነበር፡፡ እናም በስንት ትግል ነው ከመፍረስ ድኖ መልሶ የተጠናከረው፡፡

**ግዮን፡- የሕወሓት ታጋዮች እዚህ ውሳኔ ላይ ያደረሳቸው ምክንያት ምን ነበር?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡- ከመጀመሪያውኑ የሕወሓት ታጋይ ሲታነፅና ሲገነባ "ከተከዜ ወንዝ በኋላ የአንተ አገር አይደለም" እየተባለ ተሰብኮ ስለነበር፣ ልክ ወደ አማራው ምድር መድረስ ሲጀምር ሀገሩ እንዳልሆነ በመቁጠር በቃኝ ወደ ሀገሬ፣ ወደ ቤተሰቤ እመለሳለሁ በማለቱ ነበር፡፡ መንገድ የጀመሩም እንደነበሩ አስታውሳለሁ፡፡ ይህ እንግዲህ ድርጅቱ ገና በጠዋቱ የፈጸመው ታሪካዊ ሥህተቱ ነው ማለት ይቻላል፡፡

**ግዮን፡- የኢሕዴን መሪዎች የትግል ድርሻስ ምን ይመስል ነበር?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡- ከኢሕአዴግ ምስረታ በፊት እና በኋላ በሚል በሁለት ከፍዬ ነው የምነግርህ፡፡ ኢሕአዴግ ከመመሥረቱ በፊት የኢሕዴን አመራሮች በመጀመሪያ አካባቢ በተደረጉ ውጊያዎች ከፊት መስመር በመሰለፍ፣ ለመስዋዕትነት በነበራቸው ቁርጠኝነት አርአያዎች አድርጓቸው ነበር፡፡ ለምሳሌም ጌታቸው ጀቤሳ(ያሬድ ጥበቡ)፣ አዲሱ ለገሰ፣ በረከት ሰምዖን እና ዑስማን አሸኔ በተራ ተዋጊው ዘንድ እጅግ ዝነኞችና ተወዳጆች ነበሩ፡፡ ከታች ጀምረው ተፈትነው የመጡ ከመሆናቸውም በዘለለ ከአባላቱ ጋር አብረው ውለው ስለሚያድሩ ጠንካራ ግንኙነት ነበራቸው፡፡ በፖለቲካውና በካድሬ ቅስቀሳው በኩል ደግሞ እነ ታምራት ላይኔ፣ ኃይሌ ጥላሁን፣ ሕላዊ ዮሴፍ፣ ታደሰ ካሳ፣ ተፈራ ዋልዋ፣ ሙሉአለም አበበ እና ሌሎችም ጠንካራ መሪዎች ነበሩ፡፡

ከኢሕአዴግ ምስረታ በኋላ ደግሞ ጥቂት የማይባሉት አመራሮች ያንን ፀባያቸውን አውልቀው ያልተጠበቀ የባሕሪ ለውጥ ታይቶባቸዋል፡፡ ችግርን በምክክር የመፍታት ልማድን ጥለው አፋኝ መሪ ሆነው ቁጭ አሉ፡፡ ለአባላቶቻቸው ደንታ ቢስ መሆን በመጀመራቸው ከማሳመን ወደ ማባረር ተሸጋገሩ፡፡ በድንገት አድርባይነት እየተጠናወታቸውም ከድርጅታቸው በላይ ለሕወሓት ጥሩ አገልጋይ እና ጉዳይ አስፈጻሚም ሆነው ዐረፉት፡፡ አልፎ ተርፎም የሕወሓት ቡችላ በመሆን የገዛ አባላቶቻቸውንን መናከስ ጀመሩ፡፡ ያንን መልካም መሪነታቸውን እየተው ተንኮለኛ አለቃ ሆኑ፡፡ አባላቱም እምነተ-ቢስ ሲሆኑበት እንደ መሪ ማየቱን የመተው አዝማሚያ ያመጣው ዛሬ አይደለም፤ ገና በረሃ ሳለን ነው፡፡

**ግዮን፡- የኢህዴን ሊቀመንበር ጌታቸዉ ጀቤሳ (ያሬድ ጥበቡ) በምን ምክንያት ነበር ከድርጅቱ የወጡት?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡- ከላይ ከጠቀስኩት የተለወጠው ባህሪ እና ከህወሓት ጫና ጋር ይያያዛል፡፡ ይህንን ተከትሎም እነ ጀቤሳ፣ አዲሱ፣ በረከትና ኡስማን "ኢሕዴን ድርጅታዊ ነፃነት የለውም፡፡ በህወሓት የታፈነ ነው" የሚል አቋም ይይዛሉ፡፡ እነ ታምራት፣ ኃይሌ እና እነ ታደሰ ካሳ ደግሞ "ህወሓት ዴሞክራሲያዊ ብሔርተኛ ድርጅት ስለሆነ ሌላ ድርጅት አያፍንም፤ የምትሉት ተገቢ አይደለም" የሚል ምላሽ ሲሰጡ፤ እነ ጀቤሳም በግላጭ የሚታየውን እውነታ ለመካድ የሞከሩትን እነዚህን ሰዎች "ህወሓት አስርጎ ያስገባቸው ናቸው" በሚል ሲከሷቸው፤ ኢሕዴን ለሁለት የመሰንጠቅ ጠርዝ ላይ ደረሰ፡፡ ሁኔታውም አለቅጥ እየተካረረ ሲሄድ ህወሓቶችም ጀቤሳን በጠላትነት ማየት ሲጀምሩ አስቀድሞ ለሥራ ውጭ ስለነበረ በዚያው ሳይመለስ ቀረ፡፡ በወቅቱ ክፉኛ ስሜቱ ተጎድቶ የነበረው አዲሱ ለገሰ "ትግሉ የድኻ ልጅን ከማስጨረስ በቀር ለውጥ እየታየበት አይደለም" ብሎ ስንብት እስከ መጠየቅ ደርሶ ነበር፡፡ ነገር ግን በረከትና ኡስማን "ይሄን ትግል እዚህ ደረጃ አድርሰህ እንዴት ትተኸው ትሄዳለህ?" ብለው አግባብተው አስቀሩት፡፡ እነ ታምራት ግን አዲሱ ብቻ ሳይሆን ሌሎቹም እንዲሄዱላቸው ፈልገው ነበር፤ ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች በሠራዊቱ ታዋቂነትና ተወዳጅነት ስለአገኙ በእነሱ የመሪነት ሚና ላይ ጥላ አጥልተውባቸው ነበር፡፡

የሆነ ሆኖ ልዩነቱን ጣራ ያስነካው የህወሓት አመራር የነበረው ግደይ ዘርዓጽዮን ከህወሓት ተባሮ ሱዳን ከሄደ በኋላ የኢሕዴን አባል ልሁን ብሎ ጥያቄ ማቅረቡ ነበር፡፡ የተወሰኑ አመራሮች ለጥያቄው ይሁንታ ቢሰጡም፣ ክፍፍልና እርስ በእርስ ያለመተማመን ስለነገሰ አልተቀበሉትም፡፡ ግደይ ዘርዓጽዮን ግን ስለ ሕወሓት መሪዎች መሰሪነትና ተንኮለኛነት ለኢሕዴን አመራር አባላት በሚገባ አስረድቶ ነበር፡፡ በዚህ ተረክ የተፈጠረው አለመስማመት ልዩነቱን አሰፋው፤ ይሄን ያወቀው መለስ ዜናዊም ወደ ኢሕዴን ቤዝ-አምባ ገስግሶ በመምጣት "ይሄ የማይረባ ድርጅታችሁ የማይረባ ሰው እየሰበሰበ" ብሎ እስከ መሳደብ አድርሶት ነበር፡፡ ስድቡ ግደይ ላይ የተነጣጠረ ነበር፡፡

**ግዮን፡- ህወሓት በጦርነቱም ወቅት ሆነ ስልጣን ከያዘ በኋላ ‹‹ከተለያዩ ክልሎች ብዙ ንብረቶች ወደ ትግራይ ያሸሽ ነበር›› የሚሉ አሉ፡፡ እርስዎ በቦታው የነበሩ ባለታሪክ ኖትና በዚህ ጉዳይ አስተያየትዎ ምንድን ነው?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡- መጀመሪያ በትግሉ ወቅት ከገጠር ወደ ከተማ ስትገባ የተገኘን ንብረት የመዝረፍ ባሕል በህወሓት ብቻ ሳይሆን በኢሕዴንም፣ በኢሕአፓም በሁሉም ነበር፡፡ ደርግም ሶሻሊዝም በሚል ሰበብ የሕዝብን ንብረት አግዶና ወርሶ ስለነበር ኩነቱ ለዘረፋ ይመቻል፡፡ በዚያን ወቅት የትኛውም ከተማ ገብተህ ከኀብረት ሱቅ ጀምረህ አቅምህ የቻለውን ይዘኸው ብትሄድ እንደ ሥህተት አይታይም፡፡ ሌላ ለትግል የምናውለው የሪሶርስ ምንጭ የለንማ፡፡ ነገር ግን ኩነቱ አደገኛና ውስብስብ እየሆነ የመጣው በ1982ዓ.ም ኢሕአዴግ ከተመሰረተ በኋላ በሰሜን ወሎ፤ በደቡብ ወሎና በደቡብ ጎንደር እንዲሁም በመላው ኢትዮጵያ እየተገባ ዘረፋ ሲፈፀም ነው፡፡ ይኸውም ህወሓት በጋራ ከተቆጣጠርነው የአማራ ክልል ጄኔሬተሮች፣ የሕክምና መሣሪያዎች፣ ሕዝቡ በጋራ የሚጠቀምባቸው ትላልቅ ማሽኖችና መጋዘኖችን ሙጥጥ እያደረገ ወደ ትግራይ ማጋዝን የትግሉ አካል አደረገው፡፡ ለአብነት በደቡብ ወሎ ተንታና አካባቢው የማይተኩ ሀገራዊ ውድ ቅርሶችን ህወሓት የሎጆስቲክ ኃይሉን እግር በእግር እየተከተለ ያጋፍፈው ጀመር፡፡ ይሄኔ ነው ሕዝቡ እኛን መውቀስ የጀመረው፡፡ ከኑሮው ላይ እያጎደለ ያበላንና ያጠጣን የአማራ ሕዝብ "እናንተ መንገድ እየመራችሁ ይዛችሁ መጥታችሁ አዘረፋችሁን!" የሚል ብርቱ ተቃውሞ ማሰማት ያዘ፡፡ ከፖለቲካ አመራሩ ውጭ ያለነው አዛገኖችና ብዙሀኑ ታጋዮች ዝም ብለን እጃችንን አጣጥፈን አልተቀመጥንም፡፡ አንዳንድ ቦታ ላይ ዝርፊያውን ለማስቆም "ለምን ትወስዳላችሁ?!" እያልን ጠብመንጃ እስከማቀባበል ደርሰን ነበር፡፡ ድርጊቱ እየተባባሰ ሲሄድ የከተማ ነዋሪዎች አመፅ አደረጉ፡፡ ለዚህ ግንባር ቀዳሚ የየጁ ዋና ከተማ የሰሜን ወሎዋ ወልድያ ነበረች፡፡ በከተማዋ ድብልቅልቅ ያለ አመፅ ተደረገ፡፡ "ከተማችንን ለቃችሁ ውጡልን!" እያሉ ፈጥርቀው ያዙ፡፡ ደብረ-ታቦርና ማርቆስም ሲደግሙት፤ ስብስባ ተደርጎ የኢሕዴን አመራሮች ሕዝቡን ወደ ማረጋጋቱ ዞሩ፡፡

**ግዮን፡- የታገሉለትን ሀገር ሕዝብ ሀብትና ንብረት እስከ መዝረፍ ያደረሰው ምክንያት ምን ይመስሎታል?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡- ዋናው ችግር →



የጀነራል ተፈራ ማሞ ቤተሰቦች 1- ቴዎድሮስ ተፈራ 2- ኢዮብ ተፈራ 3- ሕፃን አባይ ተፈራ እና ባለቤቱ እመቤት

ህወሓት ለታጋዮቹ የየተሳሳተ ስብከት ማድረጉ ነበር፡፡ በዚህ የተነሳም ታጋዮቹ ከትግራይ ክልል ውጭ እያጠቁ ሲመጡ “የመሀል አገሩም የኛው ሀገርና ሃብት ነው” የሚል ስሜት አልነበራቸውም፡፡ ገና ከጀምሩ ከትግራይ አልፈው ወደ ሌላው ክልል ሲገቡ የእነሱ አገር እንዳልሆነ እንዲቆጥሩት ተደርጎ ነው የተሰበኩት፡፡ የዚህ ዓይነቱ ነውር የሆነ አመለካከት ከመነሻው ስለነበር ይመስለኛል መላው ኢትዮጵያን ለዓመታት ሲዘርፉ ተጠያቂ የሚሆኑ የማይመስላቸውም፡፡

በአጠቃላይ ከድል በኋላ የአገሪቱ ስልጣን ሙሉ በሙሉ በህወሓት ስር ወድቋል፡፡ የትም ቦታ ብትሄድ አብዛኛው ተቋማትና ድርጅቶች የህወሓት አባላትና ደጋፊዎች መምነሸነሺያ ሆነዋል፡፡ ህወሓቶች እንደሚታወቁት ለአገራዊ ጥቅምና ጉዳይ ደንታ የላቸውም፡፡ ሁሉን ነገር ወደ ራሴ አካባቢ ብቻ ሲሉ ነው የሚታዩት፡፡ “ያንተም የኔ ነው! የኔም የኔ ነው!” የሚል ያልተፃፈ ህግ አላቸው፡፡

**ግዮን፡- ኢሕዴን በዚህ ጉዳይ ላይ መክሮ የወሰደው እርምጃ ወይም ያቀረበው የመፍትሔ ሐሳብ ነበረ?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡- የተወሰኑ የኢህዴን አመራሮችና ብዙሃኑ አባላት ገና ከመነሻው ጀምሮ ይሄን ታግለውታል፡፡ አገር ከተረጋጋች በኋላ ህወሓት ቁሳቁስ መሰብሰብ ሲጀምር “ለምን?” የሚል ጥያቄ አንስተዋል፡፡ ግን ቁርጠኛ ትግል ያደረገው በ1985 ዓ.ም በኢሕአዴግ ደረጃ በየድርጅቶች ግምገማ ነበር፡፡ ኢሕዴን ስብሰባውን ደሴ ላይ የወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ታምራት ላይኔ እየመራው ተደረገ፡፡ “ለምንድነው የአገሪቱ ሀብት ወደ አንድ አቅጣጫ የሚጓዘው?” የሚል ነገር አነሳን፡፡ “ለምንድነው ሁሉንም የስልጣን ቦታዎች የህወሓት አባላት ብቻ የያዙት?” የሚል አስከተልን፡፡ “በስልጣን ላይ ያሉት ሕዝቡን በዕኩልነትና በፍትሕ አያገለግሉም!” በሚል ወጥረን ያዝን፡፡ ለዚህ የስብሰባው መሪ ታምራት የሰጠን መልስ “እናንተ ከምድረ ምቀኛና ነፍጠኛ ጋር እየዋላችሁ፣ ሕይወት የተከፈለበትን ትግል አጠለሻችሁት” የሚል ከእርሱ የማይጠበቅ ተራ የመንደር መልስ ነበር የመለሰልን፡፡ በወቅቱ ዛሬ በእስር ላይ የሚገኘው አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ተሳታፊ ስለነበረ፣ እኛን ደግፎ አስተያየት ሰጠ፡፡ አንዳርጋቸው ያለው ቃል በቃል “እናንተ ለሕዝቡ እንታገላለን ብላችሁ ለሕዝብ ቃል የገባችሁትን እየተገበራችሁ አይደለም፡፡ የምትውሉት ቤት ስታማርጡ፣ መኪና ስታፈላልጉ ነው እንጂ ሥራ እየሠራችሁ አይደለም” የሚል ነበር፡፡ ለአንዳርጋቸው መልስ የሰጠው ታምራት ላይኔም ቃል በቃል ያለው “እኔ ሥራ ሠራሁ ለመባል በርበሬ ተራ መርካቶ መገኘት የለብኝም” የሚል የወረደ አሽሙር እንደነበር አስታውሳለው፡፡ አንዳርጋቸው ከዚህ በኋላ ነው ድርጅቱን ጥሎ የሄደው፡፡ ለሁለት ዓመት የኢሕዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ነበር፡፡ ከዛም በኋላ አጠር አድርጎ በፃፈው “የአማራ ሕዝብ ከየት ወዴት” በሚለው መፅሀፉም ሆነ በስፋትና በጥልቀት የሀገራችንን ፖለቲካ በዳሰሰበት “ነፃነትን የማያውቅ ነፃ አውጪ” በሚለው ድርሳኑ ይህንኑ አስረግጦ ተናግሯል፡፡ ስለዚህ ኢሕዴን ሊቀመንበሩን ጨምሮ በርካታ አመራሮች የህወሓትን ጥቅም ለማስከበር ስለአፈኑን ዘረፋውንም ሆነ የበላይነቱን ማስተካከል ባንችልም ብዙ ታግለናል፡፡ ሆኖም ጉዳይን ወደ ሕዝብ ስላልወሰድነው እውነቱ ተጨፍልቋል፤ እውነተኛ ታጋዮችም ከአመራሩ ጋር ተደርበን ልንታይ ችለናል፡፡ ይሄ ያማል፡፡

**ግዮን፡- ደርግን ከጣላችሁ በኋላ ያሰፈናችሁት ሥርዐት ፍትሐዊ ነበር ይላሉ?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡- ሥርዐቱ ከመነሻው አድሎ ላይ የቆመ ነበር፡፡ ወደ ሥልጣን የመጣው ሕወሓት መራሹ መንግሥት የኢትዮጵያ ጉዳይ ጉዳዬ አይደለም የሚያስብሉ ትላልቅ ስሕተቶችን ፈጽሟል፡፡ የኤርትራና አሰብ ጉዳይ የተስተናገደበትን ጨምሮ በርካታ ማሳያዎች አሉ፡፡ የ1967ቱ ማኒፌስቷቸውንም በአደባባይ እንደቀየሩት ደጋግመው ቢያውጁም፣ መሬት የረገጠው እውነት ግን ይህንን አያሳይም፡፡ ያ ማኔፌስቶ ትግራይን ገንጥሎ ነፃ ሀገርን መመስርት የሚያካትት እንደነበረ ካልዘነጋነው የዛሬውን ሁኔታ ለመረዳት አያስቸግርም፡፡ በረሓ ላይ ይዘጋጁ የነበሩትን የማታገያ ጽሑፎችንም ብታይ “የትግራይ ወታደራዊ መስመር” የሚለውን ሰርዘው፤ “የኢትዮጵያ ወታደራዊ መስመር”፣ “የትግራይ አብዮት ከየት ወዴት” የሚለውን “የኢትዮጵያ አብዮት ከየት ወዴት” እያሉ ከቀየሯቸው በኋላ ነው የኀብረት ግንባር የሚል ስልታዊ የጠቅላይነት መንገድ መጥረጊያ ያመጡት፡፡

**ግዮን፡- አሁን የሚነግሩን የኢትዮጵያን የመምራት ሥልጣን በማን እጅ እንደ ወደቀና በመምራት ላይ ያለውን ኃይል አመጣጥ ነው?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡- በሚገባ! ‹‹የኢትዮጵያ ጉዳይ የኔ ጉዳይ አይደለም›› ይል የነበረው ሕወሓት “የኢትዮጵያ ጉዳይ” ማለት ጀመረ፡፡ ዋነኛው ይሄን ያለበት ምክንያት ደግሞ “ቁሳዊ ሰቀቀኑን” እና የማቴሪያል እጥረቱን ለመፍታት ሲል ነው፡፡ እንግዲህ ወደ ጥያቄህ ስመጣ ፍትሐዊ ነው አይደለም ለማለት መነሻ ሥሩን ማወቅ ይጠይቃል፡፡ ወደ ሥልጣን የመጣው ኃይል ከመነሻው አገራዊ አጀንዳ ያልነበረው ነው፡፡ ከመሪዎቹም አብዛኞች ኤርትራ ውስጥ አድገው የሻዕቢያ ዓይነት ዝንባሌ የሚታይባቸው ሲሆኑ የተወሰኑት ደግሞ ኤርትራዊ ደም ያላቸው ናቸው፡፡ እዚህ ላይ የሚለየው ሕዝቡና ብዙኃኑ ተራ ታጋይ ነው፡፡ የትግራይ ሕዝብ ከመጀመሪያው ጀምሮ ቅንጣት ታክል ኢትዮጵያዊነቱን ጥያቄ ውስጥ አስገብቶ አያውቅም፡፡ በሀገር ግንባታው ሂደትም ሆነ ከውጪ ወራሪዎች ጋር በተደረገ ጦርነት ወንድሙ ከሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር አብሮ የለፋና የተዋደቀ መሆኑ መዘንጋት የለበትም፡፡

**ግዮን፡- የትግራይን ሕዝብ ማለትዎ ነው?**

ብ/ጄነራል ተፈራ፡-በሚገባ! አንድ ምሳሌ ልጥቀስ፡፡ አዲግራት ላይ በደቡብ አቅጣጫ በኩል ሥልጠና እየወሰድን ሳለ ዝናብ አስቸገረንና የሞርታር አስልጣኝ ከሆነው ከህወሓቱ መብራቱ ጋር በአንድ ገበሬ ቤት ተጠለልን፡፡ ቡና አፍልተው፣ ዳቦ አቅርበው አስተናገደውን እየተጫወትን እያለ እኔ “አቦይ የኤርትራ ነገር እኮ ቁርጥ እየሆነ መጣ ልትለየን ነው” አልኩት፡፡ ወዲያውኑ በቁጣ ብድግ አለና “እንዴት እንደዚህ ይሆናል! ኤርትራ እኮ የኢትዮጵያ አካል ናት! ደርግ ትክክል ነው” በማለት ጮኸብን፡፡ የትግራይን ሕዝብ ስታየው፤ በመሠረቱ በኢትዮጵያ ጉዳይ የማይደራደር ጠጠር ያለ ሕዝብ ስለሆነ ይህ መለየት አለበት፡፡ በአሁኑ ጊዜ የህወሓትን ስውር ተንኮልና የሕዝቡን የልብ ትርታ የማደበላለቅ ሁኔታ ይታያል፤ ይሄ ተገቢ አይደለም፡፡ መሪዎቹ ግን መጀመሪያውኑም ስለ ኢትዮጵያ ተጨንቀውም፣ አስበውም አያውቁም፡፡ ለአብሮነት ሕይወት አልተፈጠሩም፡፡ ኢትዮጵያን የኛ አካል ናት ብለው ስለማያስቧት እንደ ጠላት ነው የሚቆጥሯት፡፡ አማራውን እንደ ጠላት ያዩታል፡፡ አማራውን ከኦሮሞው፣ ኦሮሞውን ከሱማሌው፣ አማራውን ከትግራዩ፣ አንዱን ክልል ከሌላው ክልል አጣልተው ያጫርሱትና መልሰው እነሱው ዳኛ ይሆናሉ፡፡ አንተ ነፍጠኛ ስለሆንክ ነው፣ አንተኛው ጠባብና ትምክህተኛ ስለሆንክ ነው…እያሉ፤ በዚህ ቅራኔ ውስጥ ደፍቀውን በሥልጣናቸው ላይ ሁነው መኖር ነው የሚፈልጉት፡፡

ሌላው ከአማራውና ኦሮሞው ውጪ ያለውን ብሔረሰብ በተመለከተ ደግሞ የዘለለ ቢዘል የትም አይደርስም የሚል ትዕቢት ያሳያሉ፡፡ ሲጠሩት እንኳን “አናሳው ማኅበረሰብ” ብለው ነው፡፡ የአናሳው ሕዝብ ግቡ ቁሳዊ ሰቀቀንን መፍታት ነው እንጂ ነፃነት የሚባል ነገር ለእሱ ምኑም አይደለም ነው የሚሉት፡፡ በጥቅሉ ሀገራዊ በሆነ ቁልፍ ጉዳይ ላይ የተመሰረተ ፍላጎት የላቸውም፡፡

**ግዮን፡- ከቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ጋር ተገናኝተው ያውቃሉ? ከተገናኙስ ስለምን ጠየቋቸው? ምላሹስ ምን ነበር?**

ውድ አንባቢያን የዚህን ቀጣይ ክፍል በሚቀጥለው የግዮን እትም እናቀርባለን ይጠብቁን፡፡

# በወቅታዊ የሀገር ጉዳይ የቤተ ክርስቲያን ሚና



ዓባይነህ ካሤ(ዲ/ን)

ዘመኑ በሀገራችን ሰማይ ላይ የምሩን አዝምሟል። እንደ መስቀል ደመራ ምሶሶ ወደ የትኛው አቅጣጫ እንደሚወድቅ ያልለየለት የፖለቲካ ውጥረት አንዣብቧል። ጥቁሩ ደመና የምሕረት ወይ የትካት (የጥፋት) ዝናብ ያውርድ አያውርድ አልለየለትም። በሥልጣን ላይ ያለው አመራር በውስጡ ንዝንዝ ተሰንጎ ተይዟል። እንደዚህ ያለውን ሁኔታ መጠፍነግ እንለው ዘንድ እንችላለን። በደጅ ያሉ የፖለቲካ ሰዎች ከጊዜው ለማትረፍ ላይ ታች ይወጣሉ ይወርዳሉ። ብዙኀን መገናኛ የመሰላቸውን ትንታኔ በየአቅጣጫው ያስሔዱታል። ማኅበራዊ የብዙኀን መገናኛውም በተለያየ ትክ ትክ ተጨናንቋል። ቃሉ ይመጥነው እንደኾነ እንጃ እንጅ አነቃቂ (activist እርግጥ አንዳንዶቹ አቀጣጣይ ቢባሉ ይመረጣል) የተባሉ ሰዎች ዘራቸው በዝቷል።

አስቸኳይ አዋጅ የሚባል እጅ መጠምዘዣ ደመና ውስጥ የወደቀችው እናት ኢትዮጵያ ያለ ጠያቂ ያለ ምክንያት በልጆቿ ደም እየታጠበች ቀጥላለች። ሺ ሞት ተደግሶላት ሺ ሞቶችን ድል አድርጋ የወጣች ሀገር ናትና የመከራው መብዛት ሊያደናግጥ አይገባም። ወደ ሦስት ዓመት እየተጠጋ ባለው ጊዜ ውስጥ አንድም ቀን አላረፈችም። ዘንድሮማ በዓለ ጥምቀትም ጠሙን አላደረም። ታቦት አልታፈረም። ለሀገር ድንበር ዘማቹ ታቦት፣ ተደርጎ በማያውቅ ሥራ ክብሩ የተነካ ዘንድሮ ነው። ሙስሊሙ የሚያከብረውን ታቦት ወታደሩ ተተናኮለው።

የቅሪላ ማልፊያ ሜዳዎቿ ሳይቀሩ የሞት አዋጅ የሚፈጸምባቸው ኾነዋል። ጎሳ - ጎሳ፣ ጎጥ - ጎጥ የሚሸታትቱ ወሬዎች እንደ አዲስ ይጎለጎሉ ጀምረዋል። በጢሳቸው የታፈነው እየበዛ መጥቷል። ዋለልኝ የሚባል ሰው በኢትዮጵያችን ላይ እንደዋለባት አለ።

በዚህች ምድር ላይ የእግዚአብሔር መንግሥት ተወካይ የኾነችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በዚህ ፈተና ውስጥ እንድትገባ እየተገደደች ነው። ለዚህች መንግሥት አገልጋይ ይኾናል ተብሎ የተዋቀረው ቤተ ክህነት ቀንደኛ የፖለቲካ እና የጎጣ ጎጥ ዘውገኛነት መናኸሪያ ኾኗል። በበዓለ ጥምቀቱ በኢትዮጵያ ታሪክ ኾኖ የማያውቅ ደም ማፍሰስ ሲደረግ ከሀገረ ስብከቱ ሊቃነ ጳጳሳት በስተቀር ትንፍሽ ያለ የለም።

ተጠቅላይነቱ ወደ ቤተ ክህነቱ በጠራራ ፀሐይ ደረቱን ነፍቶ በመግባቱ ዓላማውን ረስቷል፣ አቅሉንም ስቷል። ቤተ ክህነቱ ባይጠቀለል ኖሮ ወጉና ሥርዓቱ እንዲህ አይደለም። በዓለ መስቀል በተለመደው አደባባይ እንዳይደረግ ሲከለከል እንደማንኛውም ታዛቢ እግሩን እያስበላ ቤተ ክህነቱ ጽድቅ የሌለው አርምሞ ውስጥ ገብቷል። ራመድ ያሉ አንዳንድ አባቶችን አትርፎልናልና የድርሻቸውን በጊዜው በአስደናቂ ሁኔታ በማድረግ መክተው ጨርሰን አንገት እንዳንደፋ አድርገውናል። የማይረሳ አይረሳም! ዋልድባውያን ወገን እንደሌለው የታሠረ ሁሉ ሲፈታ አቤት የሚልላቸው አልተገኘም። የአንድ ደብር አለቃ ሊያደርገው የሚችለውን ምሕላ እያወጀ ብቻ በሰቀቀን ኑሩ የሚል ቤተ ክህነት ቁጥሩ የትየለሌ ነው።

ወኅኒ ቤቶች እስረኞችን በመፍታት ይራቆታሉ ተብሎ ሲጠበቅ በፈረቃ ለማሠራት የታሰበ ይመስል በገፍ ማሠር እንደገና ተጀመረ። ትጥቅ ለማስፈታት ተብሎ ገበሬው በጥይት እየተቆላ ይገኛል። መብቱን የሚጠይቅ ወይም የሚሞግት ሰው ወንጀል ሠርተሃል ይባላል። ሐሳብን በነጻነት መግለጥ ተከለከለ የሚለው ቃል ማሰብን እስከመከልከል ይደርሳል። ሰው ያላሰበውን አይናገርም ወይ አይጽፍም። ካደረገውም ቅዠት እንጅ ሐሳብ አይደለም። ሰው መኾን ከማሰብ ጋር አንድ ነው። ስለዚህ ሊያስብ የተፈጠረን አትናገር አትጻፍ ማለት ማሰብን መከልከል ነው። በአጭሩ ማሰብ ተከልክሏል። ስለኾነም አሳቢዎች እንዲመክኑ ተደርጓል።

በአጭሩ ጠቅላይ ሚንስትሩ እንደተናገሩት ሀገሪቱ በፖለቲካ ቀውስ ላይ ትገኛለች። ታዲያ በዚህ ቀውስ በነገሠበት ጊዜ የሰላሟ ደጅ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ምን ሚና ሊኖራት ይገባል? ለምን? የሚለውን መዳሰስ ይገባል። እናም በመጠኑ ብናያቸው አይከፋም።

ቅድሰት ቤተ ክርስቲያን ሚናዋ ብዙ ነው። በጥቅሉ ግን የሚከተሉትን ዐራት ነጥቦች ማየቱ ፍንጭ ይሰጣል።

## ፩. አስታራቂነት

በኢትዮጵያ ምድር ከመደበኛው የሕግ አሠራር ይልቅ ረዥም ዘመን ያስቆጠረ ትውፊታዊ ሕግ (Customary Law) ከፍ ያለ ተቀባይነት አለው። በዚህ ትውፊታዊ ሥርዐተ ሕግ ውስጥ የቤተ ክርስቲያን እና የሀገር ሽማግሌዎች ተጽእኖ በጉልህ ይታይበታል። ቤተ ክርስቲያን በኹለት መልክ ሱታፌ ስታደርግ ኖራለች። አንደኛው ሕግጋተ እግዚአብሔርን መሠረት ባደረገ ሲኾን ኹለተኛው ደግሞ በአበ ነፍስ በኩል ነው።

**...ይህን መንፈሳዊ ብቃት ይዞ መገኘት አለመቻል ብዙዎችን ሲያሸሻቸው ይታያል። ጨርሰን አላጣንምና አሁን የግድ ጀግና የቤተ ክርስቲያን ተቆርቋሪ ያስፈልጋል። ጥፋት እስካለ ድረስ የሚገሰጽ አለና...**

ሕግጋተ እግዚአብሔርን መሠረት ባደረገ ሁኔታ ቅድመ ፍትሐ ነገሥት እና ድኅረ ፍትሐ ነገሥት ባሉት አዝማናት ድርሻዋ ይህ ነው ተብሎ በቀላሉ ሊሰፈር አይችልም። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ ውስጥ መንፈሳዊ ተቋም ብቻ ሳትኾን ማኅበራዊም ተቋምነት ያላት ናት። በማድላት የመናገር ሳይኾን በፍጹም እውነት ነው። እንደ ትምህርት ሚኒስትር ኾና ሕዝቡን የራሷን ሆሄያት ቀርጻ ፊደል ከማስቆጠር እስከ ማንበብና መጻፍ ከዚያም ሲያልፍ ደግሞ እስከ ፍልስፍና የምታደርስ ለኢትዮጵያ የዕውቀት ቤቷ ነበረች። ከቀለም ዝግጅት እስከ ብራና መዳመጥ አልፎም ጽፎ እስከ መደጎስ የሠለጠነባት ባሕረ ጥበባት ናት።

በጤና በኩልም ከጠበል ቦታዎቿ ጀምሮ እስከ በቁት አባቶቿ የሕዝቡ መጠጊያ ኾና የኖረች ምስካየ ኅዙናን (የሐዘንተኞች መጠጊያ) ኾና አገልግላለች። ሆስፒታል፣ ክሊኒክ፣ ጤና ጣብያ፣ ጤና ኬላ፣ ላብራቶሪ . . . ወዘተ የተባሉ የጤና ማዕከላት ሳይኖሩ ሁሉም ሪፈራል የሚጻፍለት ወደ ጠበል ቦታ ነበረ። ያጣ የነጣ ወድቆ የሚጦርባት የጡረታ ሚንስትርም ነበረች፤ ዛሬም ናት። ዐውደ ቀመር አዘጋጅታ የፀሐይና የጨረቃ የከዋክብትንም ምስጢር ተረድታ በራሱ የዘመን መቁጠሪያ ኮራ ብሎ እንዲኖር ያስቻለች የማንነት መመኪያ ናት። በዚህ ጉዳይ ብዙ ማለት ይቻላል። በተጠቀሱት ብቻ ማኅበራዊ ገጽታዋን ከተመለከትን እርቀ ሰላምን በማውረድ የነበራትን ሚና በወፍ በረር እንየው።

የነጻነት እና የእኩልነት ሕግ የት ይገኛል? ከተባለ ከመጽሐፍ ቅዱስ መኾኑን ማንም ሊስተው አይችልም። ከሕገ እግዚአብሔር የተገኙትን ሕግጋት ፍትሕ ሥጋዊና ፍትሕ መንፈሳዊ ብላ በመክፈል ፍትሕ ሥጋዊን አብያተ መንግሥቱ እንዲጠቀሙበት ያበረከተች ናት። ማበርከት ብቻ ሳይኾን የፍትሐ ነገሥቱ ሊቃውንት የሕጉን ትርጉም (Commentary) እንዲሰጡ ስታደርግ ኖራለች።

ሥርዓተ መንግሥት በመባል የሚታወቀውን ባለ ፳፩ አንቀጽ የመጀመሪያውን የተጻፈ ሕግ ይህች ቤተ ክርስቲያን ናት። በ፲፬ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያዎች አካባቢ በንጉሥ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ይህን የተጻፈ ሕግ አዘጋጅታለች። ቀጥሎም ፈውስ መንፈሳዊ የተባለ በ፲፭ኛው ክፍለ ዘመን በንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን የጻፈች የሀገር አሳቢ መኾኗ ሊካድ አይቻልም። ይህም ባለ ፳፬ አንቀጽ እንደነበረ ይነገራል። ፍትሐ ነገሥት የመጣው ከእነዚህ ሕግጋት ዘመን ወዲህ ሲኾን ሀገር በቀልም ባይኾን የተገኘው ከቤተ ክርስቲያን ነው። በዚህም የሀገር ሰላም እንዲጠበቅ፣ ግጭቶች እንዲበርዱ፣ እርቀ ሰላም እንዲወርድ ስትጫወት የኖረችው ብዙ አለ።

በአበ ነፍስና በንስሐ ልጅ ግንኙነት የብዙዎች ሰላም ተጠብቆ እንዲኖር፣ ከተናጋም እንዲመለስ በማድረግ የቤት ተቤት ጥበቃ ስታደርግ →

የኖረች የእርቀ ሰላም ውቅያኖስ ናት። ፈረንጅ አልተናገረውም እንጂ "የቀማ ይመልስ የበደለ ይካስ" የሚለው ንግግር ከቤተ ክርስቲያን የተገኘ አንድ መሠረታዊ የሕግ መርሕ ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባው ነበረ። ዞሮ ዞሮ ቤተ ክርስቲያን በአደባባይም በጓዳም የሰላም አስጠባቂነት ገጽታ ያላት እንደኾነች አለመስማማት አይቻልም።

ፈርጀ ብዙ ከነበሩት ማኅበራዊ አገልግሎቷ አንዱ መሳፍንቱም ነገሥታቱም በተለያየ ዘመን ከራሳቸው ወገን ጋር በተጠረቋቆሱ ጊዜ ከእርሷ ቀድሞ የሚገኝ የሰላም በር ከፋች አልነበረም። አንዳንድ ሰዎች በተለየ ሁኔታ ቢመለከቱትም ሥርዐተ መንግሥት ከዛጉዌ ወደ ሰሎሞናዊ አስተዳደር በሠላም እንዲዘዋወር ያደረገችው አስተዋጽኦ በቀላል የሚገመት አይደለም። ሒደቱን በተመለከተ ራሱን በቻለ ርእስ ማየት ያስፈልጋልና ወደ ዝርዝር መግባቱ በይደር ቢታለፍ ይሻላል።

በዚያም ዘመን እንደነበረችው ሁሉ ዛሬም ኢትዮጵያ በሥልጣን ጠያቂው ሕዝብ፣ ሥልጣን ላይ ባለው እና ለሥልጣን በሚታገሉ አካላት መካከል ውጥረት ውስጥ ወድቃለች። በዚያ ዘመን ያለችው ቤተ ክርስቲያን ዛሬም አለችና ልጆቿ በተለያየ ቁመና ሲተላለቁ የዳር ተመልካች ኾና ልትቀር አትችልም። ስለኾነም ወደ ጉዳዩ ተጎትታ ሳይኾን ባለቤት ነኝ ብላ ትገባ ዘንድ ይጠበቃል። እስክትጋበዝ ወይም እስክትጠራ የምትጠብቅበት አንዳችም ምክንያት የላትም። በተቸጋገሩት ሰዎች እና በመንግሥት መካከል ገብታ እንደ ግድግዳ ተጋርዳ ገላጋይ መኾን ይጠበቅባታል።

## ፪. ገሳጺነት

ደኻ ተበደለ ፍትሕ ተጓደለ ብሎ እስከ ቤተ መንግሥት ሔዶ መገሰጽ ነባር መለያዋ ነው። ይህም ከእግዚአብሔር ሥልጣኑ እና መልእክቱ በተሰጣቸው አባቶች ሲገለጥ ኖሯል። የመጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ጉዞ ይህንን ያረጋግጥልናል። ንጉሥ ሄሮድስ ቅምጥልነት አብዝቶ በትዳር ጉዳይ ከመስመር ያለፈ ነገር ሲሠራ ቢያገኘው፤ ቀጥ ብሎ እርሱ ወዳለበት ሔዶ "የወንድምህን ሚስት ላንተ ልታደርግ አልተፈቀደልህም" ብሎ ገስጾታል። ማር ፮፥፲፰።

የሩቁን ትተን የቅርብ ጊዜ ታሪካችን እንደሚያመለክተው በንጉሡ ጊዜ የነበሩት እንደ ባሕታዊ አባ ጉኒና፣ አባ ገብረ ጊዮርጊስ እና አባ ገብረ ሥላሴ ያሉት መናኞች ከንጉሡ እስከ አብዮተኞች ያሉትን ባለሥልጣናት በመገሰጽ ይታወቃሉ። አንዳንድ ጸጋ የተሰጣቸውን መምህራንም ቅድስተ ቤተ ክርስቲያን "መምህር ወመገስጽ ዘኢያደሉ ለገጽ - ፊት ዐይተው የማያደሉ መምህርም ገሳጺም" በሚል አጠራር ይጠራሉ።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ "መምህር ወመገስጽ" የሚለው የሚገባው ታላቅ መብራት ነው። ንግሥቲቱ ብርክልያ እስክትቆጣ ድረስ በጊዜው የነበረውን ክፉ አስተዳደር በዝምታ አላለፈም። በእነዚህና በሌሎች ምክንያቶች የገሳጺነት ሚና ሊኖራት ይገባል። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አጥፊዎችንም ለመገሰጽ፣ ተበዳዮችንም ይቅር እንዲሉ በማግባባት ከፍተኛ ሚና ይኖራታል ከሚባልበት ዘመን አንዱ ይህ አሁን ያለንበት ወቅት ነው። እንዳላዩ ማለፍ የሚቻልበት አይደለም።

ይህንን ሥራ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በተቋምነቷ ወይም ደግሞ አንድም ብዙም ኾነው ብፁዓን አበው ወይም አበው ቀሳውስት፣ አበው መነኮሳት ሊያደርጉት ይችላሉ። የዋልድባ መነኮሳት ያደረጉት ይህንን ነው። ከገዳሙ የተሰጣቸውን መልእክት ይዘው ለቤተ ክህነቱም ለቤተ መንግሥቱም አመለከቱ። በጊዜው የነበሩትን ጠቅላይ ሚንስትር አነጋገሩ። መልስ ግን አልመጣም። ነገሩን ሰምተው ያልፈጸሙትን ሁሉ ጠራርጎ ወሰዳቸው። በዚህም የተነሣ መከራ ጸናባቸው። ይህ ተልእኮ መከራ እንዳለው ግልጽ ነው። ነገር ግን አማራጩ መጋፈጥ ብቻ ነው። ቅዱስ ዮሐንስ ተናገረ ታሠረ፣ ተመተረ። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተናገረ በጥፊ ተመታ። እነ ባሕታዊ አባ ጉኒና ተናገሩ የራሳቸው የቤተ ክህነት ሰዎች (ዛሬም በሕይወት ያሉ ይኖራሉ) ዓይናቸውን በሰይጣናዊ አሠራር አጠፏቸው። እነ አባ ገብረ ሥላሴ ሲታሠሩ፣ ሲደበደቡ ሲፈቱ ኖሩ።

ይህን መንፈሳዊ ብቃት ይዞ መገኘት አለመቻል ብዙዎችን ሲያሸሻቸው ይታያል። ጨርሰን አላጣንምና አሁን የግድ ጀግና የቤተ ክርስቲያን ተቆርቋሪ ያስፈልጋል። ጥፋት እስካለ ድረስ የሚገሰጽ አለና። ከባድ እንዳይኾን ግን ቅዱስ ሲኖዶስ ለብቻ አጀንዳ ይዞ ቢመክርበት እና ከአባቶች ይህንን የሚከታተል አንድ ልዑክ ቢሰይም እንዴት ባማረ። ትውልዱም ከጠያቂነት በዳነ ነበር።

## ፫. ሐሳብ አቅራቢነት

ቅንነት ያለበት ሐሳብ ማንንም አያስጨንቅም። ማንንም አያስፈራም፣ ማንንም አያስደነግጥም፣ ከማንም ጋርም አያጣላም። ስለዚህ የእርቅ ሐሳብ ይዛ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ወደ መንግሥትም ወደ ሕዝብም ወደ ፓርቲዎችም ወደ ታዋቂ ግለሰቦችም ብትሔድ የተሻለ መንገድ ልትሔድ እንደምትችል ይገመታል።

በቅድሚያ በዚህ ጉዳይ ላይ ሐሳብ ሊኖራቸው የሚችሉ ግለሰቦችን ፈላልጋ ማሰባሰብ ከዚያም ከእነርሱ ጋር ተቀምጣ መምከር። ያንን የምክር ሐሳብ ይዞ የተፈላቀቁትን አካላት እያቀረቡ መነጋገር ይቻላል። አንድ የሰላም ጉባኤ ጽ/ቤት ብታዋቅር ብዙዎች ወደ እርሷ እንዲመለከቱ ያደርጋል። የጥናት መድረኮችን ማዘጋጀት፣

**...ዘረኝነት በሚወገዝባት ቤተ ክርስቲያን የዘረኝነት ተቋም የተገነባባት እስክትመስል ደርሳለች። ጥቂቶች ኾነው ብዙዎች የኾኑባት ቁመና ይዛለች። አዲስ መልክ እንድታወጣ ተገድዳለች። በአስተዳደሯ ላይ ጥያቄ ያላቸው አባቶች በሲኖዶሳቸው መምከራቸው ወንጀል ኾኖ በመንበረ ፓትርያርኩ ቅጽር ተደብድበዋል...**

በውይይት ሐሳቦችን ማዳበር የነጠረውን ሐሳብ ለእርቅ ምክረ ሐሳብ ሰነድ አድርጎ ማቅረብ።

አይቻልም ብሎ ማሰብ ሐሞት ያፈስሳል። እንዲህ ባደርግ እነ እገሌ ምን ይሉኛል ብሎ አለመፍራት። ሀገር የምትባለውን ምሶሶ በማሰብ ወደፊት መግፋት ይፈልጋል። ዝም ብሎ ቁጭ ብሎ በጾም ላይ ምሕላ በማወጅ ብቻ ከዳር ማድረስ አይቻልም። ሀብቴን ባርክልኝ እያለ ቅዱስ ሚካኤልን በጸሎት ደጅ የሚጠና አንድ ሰው ነበረ። ሰውየው ይጸልያል እንጅ ሥራ አይሠራም። አንድ ቀን ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ለዚህ ሰው ተገለጠለትና ጸሎትህ ዘወትር ባርክልኝ ነው። አንተ ደግሞ ሥራ አትሠራ ወይ ሥራ አትወድ። ምኑን ልባርክልህ? ብሎት ተሰወረ ይባላል። ዛሬም ሐሳብ ሳይዙ ዝም ብሎ ጸሎት ብቻ ማለት ሊታሰብበት ይገባል። ይህ ማለት ግን ጸሎት ለምን ይታወጃል ብሎ ከመቃወም ጋር በምንም ሁኔታ አይገኛኝም። ዝም አላሉም እንዲባል ያኽል ለማምለጫ እንዳይኾን በሐሳቦች ቢዳብር የበለጠ ሕያው ትርጉም ይኖረዋል። ያ ሁሉ ጸሎት ሲደረግ ለሀገር የሚጠቅም ሐሳብ የሚያመጡትንም እግዚአብሔር ይከስትልናል።

## ፬. ተሳታፊነት

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መቸም ቢኾን በሀገር ጉዳይ ባለቤት እንጂ የሩቅ ተመልካች አይደለችም። ይልቁንም ውጥንቅጧ እየወጣ ባለችው ሀገር ጉዳይ ዕረፍት ሊኖራት ሊሰማትም አይችልም። ስለዚህ ማግባባቱን መግፋት፣ የሚገፋ ከሌለም የመምራት ሚና ከታላቋ ቤተ ክርስቲያን ይጠበቃል።

### ለመኾኑ ለምንድን ነው ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ማድረግ ያለባት?

አንድ የሞኝ ጥቅስ እየጠቀሱ ደንዝዘው የቀሩ ብዙዎቻ አሉ። እርሱም ሃይማኖት እና መንግሥት የተለያዩ ናቸው የሚል ቃል። ወዳጄ ይህ የሚሠራው ሀገር ስትኖር ነው። ሀገር ከሌለች የትኛውም ሕግ ወደ መሬት ብቅ አይልም። ስለዚህ መጀመሪያ ሀገር እንድትኖር መሥራት ይቀድማል። የተሠራች ሀገር ቁጭ ብሎ በሚጠብቅ ትውልድ መካከል እንደዚያ ያለው ጥቅስ ይሠራል። ሴኪዩሪያሊዝም ቦታ የሚያገኘው የተረጋጋች ሀገር ስትኖር ብቻ እንደኾነ ልባችን ደጋግሞ ሊያስበው ይገባዋል። ስለዚህ በሚከተሉት ሦስት ምክንያቶች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የራሷን ሚና ትወጣ ዘንድ እንጠብቃለን።

## ፭. ግዴታዋ ስለኾነ

ሀገር ከሌለ ሕዝብ የለም። ሕዝብ ከሌለ ቤተ ክርስቲያን አትኖርም። ሕዝብ ሲያልቅ ሕዝቤ አለቀ ማለት አለባት። የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት በአሁኑ ጊዜ በተባበሩት መንግሥታት ትንበያ ስሌት መሠረት ወደ ፻፯ (አንድ መቶ ሰባት) ሚልዮን ይደርሳል። ከዚህ ውስጥ ወደ ሃምሳ ከመቶ ያኽሉ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልጅ ተከታይ ነው። በቁጥር ስናሰላው ወደ ፶፫▯፭ ሚልዮኑ (ሃምሳ ሦስት ሚልዮን አምስት መቶ ሺሕ) የቤተ ክርስቲያኒቱ ተከታይ ነው።

ይህን ያህል ቁጥር ሀገሪቱን እየመራ ያለውም አካል አንድ ዘጠነኛውን ያህል አባል የለውም። በዚህ ደረጃ ያለ ፓርቲ የሀገር ጉዳይ ይመለከተኛል ብሎ ላይ ታች ሲል ቤተ ክርስቲያን ይህን ሁሉ ሰው አቅፋ እንዴት ላይመለከታት ይችላል?

## ፩. የቀደመ ክብሯን (ሌጋሲዋን) ለማስጠበቅ

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በተለያዩ ሁኔታዎች በሀገር ጉዳይ ቀጥተኛ ተሳታፊ ኾና ድርሻዋን ስትወጣ የኖረች ታላቅ ተቋም ናት። አይደለም በሀገር ልጆች መካከል ጣልያን ኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ባወጀችበት ወቅት ቤተ ክህነቱ ወኪሉን ልኮ የዲፕሎማሲ ጥረት ማድረጉ አይዘነጋም። ሰላማዊ መንገድ ሳይሳካ ሲቀር ደግሞ ታቦቷን ይዛ ከፍልሚያው ሜዳ የገባች ባለውለታ ናት። ይህንን የሚያስመካ ጥንተ ታሪክ ማስቀጠል አለባት። የአባቶቻችን ልጆች መኖራቸው በዚህ ይታወቃል።

ዛሬም የምትታመሰው ኢትዮጵያ ናት። የሀገር ልጆች ከውጭ ሀገር እስከ ሀገር ቤት ተደራጅተው ሲተላለቁ በምን አንጀቷ ዝም ልትል ትችላለች ብዬ እጠይቃለሁ። ስለዚህ አሁን ቤተ ክርስቲያን ወደ መድረክ ብቅ ልትል ይገባል። አባቶቻችን ከየተደበቁበት ዋሻ ወጣ ብለው ከጸሎት በተጨማሪ የሚጠበቅባቸውን ሲያደርጉ ማየት የሚሻ ትውልድ መጥቷል። ሳይኾን ከቀረ ደግሞ ይቅር አይልም። ጊዜው ሁሉንም ነገር በመዳፍ ይዘን የምንሔድበት ነው። ስለዚህ ሌጋሲዋ ይጠበቅ ዘንድ ቀጣይ ሥራ መኖር አለበት።

## ፫. መጻኢውን ተጽኖ ለመከላከል

ባለፉት ፵፬ ዓመታት ቤተ ክርስቲያን በርከት ያሉ ጫናዎች ከፈርጣማው ቤተ መንግሥት ተሸክማ ኖራለች። ባለፈ ባገደመ አገዛዝ ስትደፈቅ ኖራለች። በንጉሡም ጊዜ ቢኾን ያን ያኽል ነጻነት አግኝታ ነበር ብሎ መከራከር አይቻልም።

በሀገራችን በኢትዮጵያ ነገ ለውጥ ይመጣል። ለውጡ ምን ዓይነት ነው? ምንስ ይዞ ሊመጣ ይችላል? ከቤተ ክርስቲያን አንጻር የሚመጣው ለውጥ አሉታዊነት እና አዎንታዊነት ምንድን ነው? ቅድመ ዝግጅታችንስ ምን ሊኾን ይገባዋል? ወዘተ የሚሉትን እያመላለስን ልናስባቸው ይገባል። ምንም ይሁን ምን ነገ የሚመጣው ለውጥ ቤተ ክርስቲያንን በሦስት አቅጣጫዎች ሊያሳስባት ይገባል። አንደኛ ከራሷ ሕልውና አንጻር፣ ኹለተኛ በሀገሪቱ ላይ ከሚኾነው አንጻር፣ ሦስተኛ ይህን አጋጣሚ እነማን ለምን ሊጠቀሙበት ይችላሉ? ከሚለው አንጻር ዝግጅት ይፈልጋል። ያለፉት ኹለት አዝማነ ታሪኮቻችን በብርቱ ወቅሰውን አልፈዋል። ኹለቱም አብዮቶች፤ ዘመነ ደርግ እና ዘመነ ኢሕአዴግ እነዚህ ኹለቱ።

ደርግ ዕንቁ ልጇን ቀርጥፎ በላባት። እንዲያውም አንዳንዶች ከደርግ በላይ ደርግነት የተጣባቸው የቤተ ክህነቱ ሰዎች ለደርግ አደግድገው መስገድ ሥራቸው ኾነ። ለጣዖታቸውም አቡነ ቴዎፍሎስን የመሰሉ አውራ አባት ለመሥዋዕት አሳልፈው ሰጡ። ግጥም አድርገው ሲፈርሙ ጣቶቻቸው አልተንቀጠቀጡም። አንዳንዶችም ለመፈረም ጣት አላስፈለጋቸውም። ከሀገር አልፈው ዓለም አቀፉዊ ርእይ የነበራቸውን በመቶ ዓመታት አንድ ጊዜ የማይገኙ ውድ የሀገር አምባ እንደዋዛ ተሰብስበው አስበሉ። ሺ ጊዜ ቢቆጨን አንመልሰው ነገር!

አቡነ ቴዎፍሎስ እንዴት ያሉ ዓለም ቀፋዊ ብቃት እና ቁመና ያላቸው እንደነበሩ ዕድሜ ጠገቡ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ አንድ አፍታ ላውጋችሁ በተሰኘው መጽሐፋቸው የዐይን ምስክርነታቸውን የሰጡበትን አንድ ታሪክ ባወሳ ያረጋግጥልኛል። ገድሉ የተፈጸመው በምደረ ምስር (ግብጽ) ነው። የናስር መንግሥት አብዮታዊነት ገንፍሎበት ፓትርያርኩን አቡነ ዮሳብን ከሥልጣን ያነሣል። በግዞትም ወደ አንድ ገዳም እንዲገቡ ይደረጋል።

ይህ ነገር ለብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ (ያን ጊዜ ፓትርያርክ ገና አልኾኑም) አልተዋጠላቸውም። "መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ምን ያገባዋልና ፓትርያርኩን ከሥልጣን ያወርዳል?" በማለት ፈርጣማ አቋማቸውን አሰሙ። አቋምን መግለጥ ብቻ ሳይኾን የተግባርም ሰው ነበሩና ወዲያው ማድረግ ያለባቸውን ወደ ማድረግ ተሸጋገሩ። እናም እዚያው ግብጽ ሀገር በትምህርት ላይ የነበሩትን የዛሬውን ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌን እና ሌሎችንም ይዘው በቀጥታ አቡነ ዮሳብ ወደተጋዙበት ገዳም ያመራሉ። እዚያም ደርሰው ፓትርያርኩን አቡነ ዮሳብን ወደ መንበረ ፕትርክናቸው ይዘዋቸው በቀጥታ ያመራሉ።

ወደ መንበረ ፓትርያርኩ እንደደረሱም የቤተ ክርስቲያኒቱ አባቶች እና ከፍተኛ ባለሥልጣናት በርካታ ቁጥር ካለው ሕዝብ ጋር ይቀበላቸዋል። ከዚያ በኋላ ወታደራዊ የግብጽ መንግሥት ሁኔታውን የተቀበለ መስሎ መልሶ በዘዴ ወደ ግዞት ፓትርያርኩን ወሰዳቸው እንጅ ብፁዕነታቸው ያደረጉትስ የጀግንነት ታሪክ አስደናቂ ነበረ። ሃይማኖት እንዲህ ቁርጠኛ ታደርጋለች። አይደለም በገዛ ሀገር ላይ ኾኖ በባዕድ ምድርም እንዲህ ይደረጋል።

**...በአጨሩ ጠቅላይ ሚንስትሩ እንደተናገሩት ሀገሪቱ በፖለቲካ ቀውስ ላይ ትገኛለች። ታዲያ በዚህ ቀውስ በነገሠበት ጊዜ የሰላሟ ደጅ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ምን ሚና ሊኖራት ይገባል? ለምን? የሚለውን መዳሰስ ይገባል...**

ያ ግብጽ ድረስ ወርደው የተከላከሉት የመንፈስ ልዕልና ግን በእርሳቸው የግፍ ዘመን ብቻቸውን አስቀራቸው። በግብጾች ዘንድ እርሳቸውን የመሰለ ባይገኝ ከኢትዮጵያ ድረስ ሔደው ያንን ደማቅ ታሪክ ጻፉ። ከኢትዮጵያውያንም ኾነ ከግብጻውያን መካካል በእርሳቸው ተራ የሚገባ ግን አልተገኘም። በራስ ካሣ ግቢ እኒያን የመሰሉ አብሪ ኮከብ የጭካኔ ተግባር ሲፈጸምባቸው ከማስፈጸም በቀር የተቃወሙት በጣት የሚቆጠሩ እንደነበሩ ጌታቸው ኃይሌ ደኅና አድርገው ጽፈዋል።

መገለጫ ናቸውና ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን አነሣን እንጅ "ካህናትን የማስለም" ማለትም የሶሻሊዝም አብዮት ሰባክያን ሐዋርያ ለማድረግ ብዙ ተቆፍሯል። ሽጉጥና መስቀል መቀላቀል የጀመረው ያን ጊዜ ነው። ለሙስሊሞቹ እና ለፕሮቴስታንቶቹ አንጻራዊ ርኅራኄ ያሳየው ያ አገዛዝ ቤተ ክርስቲያንን በብረት እግሮቹ ለመርገጥ ብዙ ደክሟል። የክርስቲያን ማኅበራት በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ማኅበራት ተተክተዋል። አብያተ ክርስቲያናትን ወደ ቤተ መዘክርነት (ሚዩዝየም) የመለወጥ ርብርብ ተደርጎባታል።

ጥቂት አለፍ ብሎ በደርግ እግር የተተካው መንግሥት ሲመጣም ቤተ ክህነቱ ጠባዩ አልተቀየረም። ከኢህአዴግ በላይ ኢህአዴግ የኾኑ ልብሰ መነኮስ ብቅ ብለው ቤተ ክርስቲያኒቱን ያተራምሷት ያዙ። ይህን እውነት ከራሳቸው ከኢህአዴግ ባለሥልጣናት አንዱ የተናገረው መኾኑን ላስታውስ። በአንድ ወቅት አበው ጳጳሳት እና የመንግሥት ባለሥልጣናትን በግድ የሚያገናኝ ስብሰባ በጠቅላይ ቤተ ክህነቱ ግቢ ውስጥ ይደረጋል። ይህም በአቡነ ጳውሎስ ዘመን የኾነ ነው።

በዚያ ስብሰባ ላይ አስረጂ ተብለው ዛሬም በማተራመስ ሥራ ላይ ተጠምደው ያሉ አንድ ሦስት ሰዎች "ቤተ ክርስቲያንን ተገን አድርገው ደገኛውን መንግሥት ለመጣል የሚሠሩ አሉ፣ መንግሥታችን ያጎናጸፈንን ዴሞክራሲ በኃይል ለመናድ እና የልማት ስትራቴጂውን ለማደናቀፍ . . ." እያሉ ሲዘላብዱ አንዱ ጉምቱ የመንግሥት ሰው አስቆማቸው። አባታችን እሱ እሱን ለእኛ ይተውልን ብሎ አሳፈራቸው። ግን አያፍሩምና ከጉባኤውም በኋላ እዚያው ናቸው። ተው ሲባሉ አይተውም። በቤተ ክህነቱ ለቤተ መንግሥቱ የሚሠሩ ብዙ ጥቃቅን ሠራዊቶች አሉ። በእኛ ደመወዝ ለሌላ ይኖራሉ።

የቅዳሴ ጊዜ ያለምንም ቀኖናዊ ሥርዐት እየተለወጠ የመጣው የካድሬዎች የስብሰባ ጊዜ እንዳይናወጥ በሚል ነው። ወጣቶች በአንገታቸው ማኅተብ ወይም መስቀል ማሠራቸው ወንጀል ተደርጎ የተቆጠረበት ጊዜ ነበረ። ነጠላ መልበስን የሚከለክሉ አዋጆች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ጦም እንዳይጦሙ የሚያንገላታ መመሪያ እየተቆነጠረ ሲሰፈርላት ከራርማለች። የጥምቀተ ባሕር ቦታዎቻችን እየተነጠቁ በሃይማኖት ለማይመስሉን ሲሰጡ ሠላሳ ዓመት ሊሞላን ነው። ዘረኝነት በሚወገዝባት ቤተ ክርስቲያን የዘረኝነት ተቋም የተገነባባት እስክትመስል ደርሳለች። ጥቂቶች ኾነው ብዙዎች የኾኑባት ቁመና ይዛለች። አዲስ መልክ እንድታወጣ ተገድዳለች። በአስተዳደሯ ላይ ጥያቄ ያላቸው አባቶች በሲኖዶሳቸው መምከራቸው ወንጀል ኾኖ በመንበረ ፓትርያርኩ ቅጽር ተደብድበዋል። ብዙ መጥቀስ ይቻላል፤ በደልን መዘርዘሩ ለመነሻ እንዲኾን እንጅ ሰው ለመክሰስ ስላልኾነ ይበቃል።

እነዚህ ኹለት የታሪክ ኩነታት አንድ ብርቱ ነገር ካላስተማሩን ችግሩ ከውጭው ኃይል ሳይኾን ከእኛው ነው ብለን ለመደምደም እንገደዳለን። በለውጥ ጊዜያት ሁሉ የቤተ ክርስቲያን እጆቿን መጠምዘዝ እንደሚፈለግ ሌላ ማስረጃ ፍለጋ አንሔድም። በአንጻሩ ጠምዛዥ ከሩቅ የማይመጡ፣ ከውስጣችን ያሉ ለሌላ የሚሠሩ መኾናቸውንም አብረን ልንገነዘበው ይገባል። እንደዚህ ያለውን አደጋ ለመከላከል ጥረት የሚያደርግ አካል አለመኖሩ በእጅጉ ያሳስባል። ማሸርገድ ሳይኾን መብትን ማስከበር፣ መብትን ከማስከበር አልፎም ለሀገር ሰላም መሥራትን ኃላፊነቱ አድርጎ የሚይዝ ከዚያ የሚያደርሰውም ከኾነ ከሰይፍ ፊት ለመቆም ብቃት ያለው ሰው የለንም። ምድር በደም ጎርፍ እየተጥለቀለቀች ደሙን ረግጦ ከመራመድ በቀር ደሙን ለመጥረግ የሚሠራ አላገኘንምና።

ገዳማውያን ሲታሠሩ፣ ቅናተ ዮሐንስ እንዲወልቅ ሲገደዱ፣ አብያተ ክርስቲያናት ሲቃጠሉና ሲደፈሩ፣ ክርስቲያኖች ሲታረዱ፣ . . . "እንዲህ ያልን እንደኾነ እነ እገሌ ባለሥልጣናትን ይከፋቸዋል" እንጂ እግዚአብሔርን ይከፋዋል የማይሉ አለቦታቸው የተቀመጡ ሰዎችን ሺ ጊዜ ብንወቅስ ውኃ ወቀጣ ይኾንብናል። የሌለውን ሊሰጥ አይችልምና። ከኩርንችት ወይን አይለቀምም።



በተረፈ ወርቁ

# ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ጀግናችን ማን ነው?!

የሺሕ ዘመናት ታሪክና ሥልጣኔ እንዳለው ጥንታዊ ሀገርና ሕዝብ ሁላችንንም የሚያስማማ በአኅጉራችን አፍሪካም ሆነ በመላው ዓለም ምልክት ወይም መለያ የሚሆነን ብሔራዊ ጀግናችን ማን ነው?! የሚለው ርእሰ ጉዳይ ከመቼውም ጊዜ በላይ ዛሬ ዛሬ የሁላችንንም አእምሮ የሚይዝ ጥያቄ እየሆነ መጥቷል ማለት የሚቻል ይመስለኛል፡፡

ይህን ጥያቄ እንዳነሳ የገፋፋኝ ዋነኛው ምክንያት ከጥቂት ወራት በፊት በአፍሪካ ኅብረት መሰብሰቢያ አዳራሽ በተካፈልኩበት አንድ ዓለም አቀፍ ስብሰባ ላይ በርእስነት ባነሠኹት ጉዳይ ጋር ተያይዞ ከአንድ የአኅጉራችን ሰው ከሆነ ደቡብ አፍሪካዊ ወጣት የቀረበልኝ ጥያቄ ነው፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡፡

ከጥቂት ወራቶች በፊት መቀመጫውን በደቡብ አፍሪካዊቷ ዋና ከተማ በጆሐንሰበርግ ያደረገው አፍሪካ 2.0 የተባለ ድርጅት፣ ከአፍሪካ ኅብረት ጋር በመተባባር በአኅጉረ አፍሪካ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ‹‹የአኅጉሪቱ ወጣቶች ተሳትፎና ሓላፊነት ምን መሆን አለበት?!›› በሚል በአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽንና በአፍሪካ ኅብረት መሰብሰቢያ አዳራሽ ለአንድ ሳምንት ባዘጋጀው ስብሰባና የውይይት መድረክ ላይ ለመሳተፍ ዕድሉን አግኝቼ ነበር፡፡

በዚህ ከተለያዩ የአፍሪካ አገራትና ከተቀረው ዓለም የተጋበዙ አፍሪካውያን ወጣቶች፣ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች፣ ደራሲያን፣ አፍሪካውያን ምሁራን፣ የአፍሪካ ዲያስፖራ፣ የኪነ ጥበብ ባለ ሙያዎችና ሌለሎች በርካታ ተጋባዥ እንግዶች በተገኙበት በዚህ መድረክ ላይ በአፍሪካ ታሪክ፣ ባህል፣ ቅርስ፣ ሰላም፣ ፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ዙሪያ ላይ በተለያዩ ምሁራን በርካታ የጥናት ወረቀቶች ቀርበው ሰፋ ያለ ውይይትም የተደረገበት ሰፊ መድረክ ነበር፡፡

በዚህ ስብሰባ ላይ በነበረን የሻይ ዕረፍትም ከተለያዩ ከአፍሪካም ሆነ ከውጪ ዓለም ከመጡ ወጣቶችና እንግዶች ጋር ትውውቅና የሐሳብ ውይይት እንድናደርግ ከመድረኩ አዘጋጆች መልእክት ከመተላለፉም ባሻገር፤ ተሳታፊዎች በቡድን በቡድን ሆነው ሐሳባቸውን እንዲለዋወጡ መድረክ ተመቻችቶልን ነበር፡፡ ታዲያ በዚህ የሻይ እረፍት ላይ ከደቡብ አፍሪካ ከመጣ ከአንድ ወጣት ጋር ሆነን ሀገራችን ኢትዮጵያ ለአፍሪካና በተለይም ደግሞ ለደቡብ አፍሪካ ነጻነት የከፈለችውን ዋጋና ክቡር መሥዋዕትነት በተመለከተ ከታሪከ እያጣቀስን ውይይት አድርገን ነበር፡፡

በዚህ ውይይታችንም መካከል እግራችንን ለማፍታታትና አየር እየተቀበልን ዘና ለማለት በማሰብ በአፍሪካ ኅብረት ውብና ሰፊ ግቢ ውስጥ መንሸራሸር ያዝን፡፡ከዚህ እንግዳዬ ጋርም የቀድሞውን የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የአሁኑን የአፍሪካ ኅብረት አመሠራረት ታሪካዊ ሂደት





እየተነጋገርንና ኢትዮጵያ ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት/በኋላም ለአፍሪካ ኅብረት ዕውን መሆን የተጫወተችውን ከፍተኛ ሚና እያደነቀልኝ በኅብረቱ አዳራሽ ፊት ለፊት ለጋናው ፓን አፍሪካኒስት ለዶ/ር ክዋሜ ንኩርማ መታሰቢያ ወደቆመው ሐውልት በቀስታ አመራን፡፡

ደቡብ አፍሪካዊው እንግዳም ሐውልቱ ጋር እንደደረስንም፤‹‹ኦ ዶ/ር ንክዋሜ ንኩርማ!›› አለ በአድናቆትና በመገረም ስሜት ቆም ብሎ፡፡ በዶ/ር ንኩርማ ሐውልት ሥር ቆመንም የፓን አፍሪካኒዝም አቀንቃኝ አባቶች ስለሆኑት ስለ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ ጆሞ ኬንያታ፣ ሴዳር ሰንጎርና ስለ ፓን አፍሪካን እንቅስቃሴ ታሪካዊ አመጣጥ ጥቂት ሐሳቦችን ተለዋወጥን፡፡ ይህ ደቡብ አፍሪካዊ ወጣት፣‹‹ይገርማል አገራችሁ እንዲህ ዓይነት ለአፍሪካና ለጥቁር ሕዝቦች ሁሉ ጭምር መኩሪያ የሆነ ገናና ታሪከ፣ አኩሪ ሥልጣኔና ቅርስ እንዳላት በርካታ አፍሪካውያን ወጣቶችና ብዙ የአገሬ ሕዝብ እምብዛም አያውቅም፡፡ ታሪካችሁን፣ ራሳችሁን በማስተዋወቅ ረገድ ብዙም የሠራችሁ አይመስለኝም፡፡

ይህን አኩሪ ታሪካችሁን ለሌሎች አፍሪካውያን ወንድሞቻችሁና ለተቀረው ዓለም ጭምር ለማሳወቅ ብዙ ሥራ ይጠብቃችኋል፡፡ እንዴት ይህ ሁሉ በሺሕ ዘመን የሚቆጠር ታሪክ፣ ነፃነት፣ ቅርስና ባህል ያላችሁ ሕዝቦች የተቀረው ዓለም ‹‹የረኀብና የጦርነት ምድር›› ብቻ አድርጎ ሊስላችሁ አይገባም፡፡ ይህን የተዛባ የምዕራቡ ዓለም ሚዲያዎች ምልከታ ለማስለወጥ ጊዜው አሁን የመሰለኛል፡፡አስከትሎም ይህ ደቡብ አፍሪካዊ ወጣት በኅብረቱ ግቢ ለጋናው ፓን አፍሪካኒስት የቆመውን ግዙፍ ሐውልት እያደነቀ እንዲህ አለኝ፤

ይህ የመታሰቢያ ሐውልት ለአፍሪካውያን ሁሉ ኩራት የሆነ የሚደንቅ ሥራ ነው፡፡ ለዛሬው ነፃነትና ክብር ያበቁንን አፍሪካውያን አባቶቻችንን ልናከብራቸው፣ ልንዘክራቸው፣ ልናወድሳቸውና ሥራቸውንም ለትውልድ እንዲተላለፍ ማድረግ የሚገባን ይመስለኛል፡፡ ደቡብ አፍሪካዊው ወጣት ከዚህ አስተያየቱና አድናቆቱ በኋላም‹‹ለመሆኑ የሀገራችሁ ምልክት የኾነ፣ ብሔራዊ ጀግናችሁ ማን ነው?›› የሚል ያልጠበኩትን ጥያቄ እንደዋዛ ወርወር አደረገልኝ፡፡ ጥያቄው ያልጠበኩት ብቻ ሳይሆን እስከ ዛሬ የኢትዮጵያዊነት ማንነት፣ ታሪክ፣ ቅርስና የነጻነት ሕያው መንፈስን ሊወክል ይችላል በሚል የተሰየመ ብሔራዊ ጀግና አለን/ነበርን እንዴ የሚለውን ጥያቄ ዳግመኛ በአእምሮዬ ጓዳ ውስጥ አጫረብኝ፡፡ እናም ለዚህ ዱብዳ ጥያቄ መልስ ምን ምላሽ መስጠት እንዳለብኝ ለጊዜው ግራ ተጋባሁ፡፡

ግን ደግሞ ለዚህ ያልጠበቅኩት ጥያቄ መልስ ለመስጠት እንዳለብኝ አሰብኩ፡፡ እንደ ታሪክ እና የሚዲያ ባለሙያ በአገራችን የሕዝቦቿ ታሪክ፣ ነጻነት፣ ማንነት፣ ቅርስና ብሔራዊ ኩራት ተጠብቆ እንዲቆይ ክቡር ሕይወታቸውን መሥዋዕት ያደረጉ ለቁጥር የሚያታክቱ አያሌ ጀግኖች እንዳሉን ከገለጽኩለት በኋላ ስለ እነዚህ አያሌ ጀግኖቻችን በአጭሩ ላስረዳው ሞከርኩ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ታሪካችንም በመነሳትም የቋራው ካሣ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ የዓለምን ሲሶ በቅኝ/በባርነት ስትገዛ የነበረችውንና ‹‹በግዛቷ ፀሐይ አትጠልቅም!›› ተብሎ ተነገረላትን አገር ታላቋ ብሪታንያን እንዴት እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ

እንደሞገታትና እንደተፋለማት እንዲህ ተረኩለት።

በዛ ዓለም ሁሉ ጥቁርን እንደ ዕቃ ወይም ሸቀጥ በሚገዛበትና በሚለወጥበት፣ ጥቁር ሕዝብ የእንስሳ ያህል በተቆጠረበት የአፍሪካና ሕዝቦቿ የሰቆቃ ዘመን፣ የሐበሻው ንጉሥ ጀግናው መይሳው ካሣ ‹‹ማንም ከማንም አይበልጥም፣ ማንም ከማንም አያንስም›› በሚል የእንግሊዝ መልእከተኞችን እግረ ሙቅ አስገብተው መደራደሪያ አደረጓቸው። ይህንም ተከትሎ እንግሊዛውያኑ እንዴት በአንድ ‹‹አረመኔ ጥቁር ንጉሥ›› ተደፈረን በማለት በጄኔራል ናፒር የተመራው ጦር ልኮ ነበር። ይሁን እንጂ ዐፄ ቴዎድሮስን እጃቸውን ይዞ ለታላቋ ብሪታንያ ንግሥት ለማስረከብ ክተት ሠራዊት፣ ምታ ነጋሪት ብሎ ወደ ሐበሻ ምድር ከመጣው የእንግሊዝ ጦር ጋር ከተፋለሙ በኋላ ድል ባይቀናቸውም እኚህ ጀግና፣ የሐበሻው ንጉሥ፣ መይሣው ካሣ እጄን ለነጭ ለአልሰጥም በማለት በመቅደላ አፋፍ ላይ በገዛ ሽጉጣቸው ራሳቸውን ለሀገራቸው ነጻነትና ክብር እንደሠዉ ገለጽኩለት።

ከዐፄ ቴዎድሮስ በኋላም የመጡት ዐፄ ዮሐንስም ‹‹ኢትዮጵያ አገርህ ዘውድህ፣ ክብርህ፣ እናትህ፣ ሚስትህ፣ ልጅህ፣ መቃብር ናት። ›› በሚል እንደ ተራ ወታደር በጠላት መካከል ገብተው ከደርቡሽ ጦር ጋር ሲፋለሙ በመተማ ጦር ግንባር ለኢትዮጵያ ፍቅር፣ ለሰንደቀዓላማዋ ክብርና ለሃይማኖታቸው ሲሉ አንገታቸውን ለሰይፍ አሳልፈው የሰጡ ታላቅ ኢትዮጵያዊ/አፍሪካዊ ጀግና መሆናቸውን ተረኩለት።

በመቀጠልም ዓለምን ኹሉ ያስደነቀውን የአፄ ምኒልክንና የእቴጌ ጣይቱን የዓድዋ ዘመቻና አንጸባራቂ ድልም በመተረክ፣ የዐድዋው ድል በመላው ጥቁር ሕዝብ መካከል የፓን-አፍሪካ እንቅስቃሴ መሠረት እንደጣለና እነዚህ ነገሥታቶቻችንና ጀግኖቻችን ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለመላው አፍሪካና ጥቁር ሕዝብ ሁሉ የነጻነትና የአንድነት ኩራት ምንጭ እንደሆኑ ጭምር ላብራራለት ሞከርኩ። ለአፍሪካ አገራት ሉዓላዊነትና ለሕዝቦቿ ነፃነት፣ ለአሁኑ የአፍሪካ ኅብረት ለቀድሞ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዕውን መሆን ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ያደረጉትን ብርቱ ተጋድሎና ጥረትም በአጭሩ ጨምሬ ተረኩለት።

ይህን ታሪካዊ ገለፃዬን የሰማው እንግዳ፣‹‹ታዲያ ለጥቁረ ሕዝቦች ሁሉ ኩራት ለሆነው ለዐድዋ ድልና ጦርነቱን ለመሩት ለእኚያ ለአፍሪካና ለመላው ጥቁር ሕዝቦች ሁሉ ኩራት ለሆኑት ታላቅ ጀግና ለዐፄ ምኒልክና ለእቴጌ ጣይቱ እንዴት መታሰቢያ ሳይኖራቸው ቀረ፤ የአፍሪካን አንድነት ዕውን ለማድረግ ይህን ያህል መሥዋዕትነት ለከፈሉት ዐፄ ኃይለ ሥላሴስ እንዴት በዚህ ግቢ ውስጥ አንድ መታሰቢያ ሐውልት ተነፈጋቸው?! ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የአፍሪካ አባት ተብለው የሚጠሩና በዓለም አቀፍ ደረጃ ሳይቀር ከፍተኛ ዕውቅና፣ ክብር ያላቸው ታላቅ መሪና ዲፕሎማት ናቸው። ነጩ ዓለም ሳይቀር ይህን የሚመሰክርላቸው፣ በእጅጉ የሚያከብራቸው፣ የሚፈራቸው ሰው መሆናቸውን አሳምሬ አውቃለሁ።

የሚገርምህ በሀገሬም ሆነ በሌላው ዓለም አንተ ስማቸው ከገለጽክልኝ ጀግኖቻችሁ በበለጠ ትልቅ ዕውቅና ስም ያላቸው ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ናቸው። እናም እንዴት እኚህን ንጉሣችሁን የሀገራችሁ ምልክትና ብሔራዊ ጀግናችሁ ልታደርጓቸው አልቻላችሁም ማለት ነው?! ለመሆኑ በመዲናችሁ በአዲስ አበባ ለዐፄ ኃይለ ሥላሴ የቆመ የመታሰቢያ ሐውልት አላቸውን?›› በማለት ሌላ አንገት የሚያስደፋ ፈታኝ የሆነ ጥያቄን አቀረበልኝ። ብቻ እንደው በደፈናው ለዚህ እንግዳዬ ትክክል ነህ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ ክብርና ዕውቅና ያላቸው ታላቅ ሰው ነበሩ። ለእኚህ ‹‹የአፍሪካ አባት›› ተብለው ለሚጠሩት ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የአፍሪካ መዲና በሆነችው አዲስ አበባ ሐውልታቸውን





ለማቆም የተለያዩ ጥረቶች እየተደረጉ መሆኑን በደፈናው ነገርኩት። ከዚህ ደቡቡ አፍሪካዊ ወጣት ጋር በሌሎች ጉዳዮች ላይ እየተወያየን ወደ ስብሰባው አዳራሽ ተመለስን።

ከዚህ ደቡብ አፍሪካዊ ወጣት ያነሳልኝ ጥያቄ ጋር ግን ዛሬም ድረስ በአእምሮዬ ሲመላለስ ነበር የቆየው። ለመሆኑ ለኢትዮጵያችን ብሔራዊ ጀግናዋ ማን ይሆን?! እስቲ ይህን ጽሑፍ ለምታነቡ ሁሉ የእዚህን አፍሪካዊ ወገናችን ጥያቄ ለእናንተም ደግሜ ላቅርብ። የሺ ዘመናት ታሪክና የገናና ሥልጣኔ ባለቤት የኾነች ‹‹የኢትዮጵያችን ብሔራዊ ጀግናዋ፣ ለሀገራችን ብሔራዊ ምልክት የሚሆን ማን እንደሆነ ጠይቃችሁ ታውቃላችሁን?!››

ከቅርብ ዘመን ታሪካችን እንኳን ብንነሳ ቋራው ካሣ፣ አፄ ቴዎድሮስ የጀግንነታቸውን ያህል ጀግንነታቸው በማይዋጥላቸው ሰዎች ዘንድ ጨካኝና ጨፍጫፊ እንደሆኑ ተደርገው ነው የሚቆጠሩት። ዐፄ ዮሐንስም ቢሆኑ በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ በመተማ ዐውደ ግንባር ለኢትዮጵያ ነጻነት አንገታቸውን ለሰይፍ እንዳልሰጡ ኹሉ፤ ውለታቸው ተዘንግቶ ሀገር ያስደፈሩ፣ እንግሊዞችን መርተው ዐፄ ቴዎድሮስን ያስገደሉ ናቸው በሚል አብዝተው ሲብጠለጠሉ ነው የምንሰማው። ወደ ዐፄ ምኒልክም ስንመጣ ደግሞ የባሰ ነገር ነው የምንሰማው። የቅኝ ገዢዋ የአቢሲኒያ ንጉሥ ተደርገው የሚቆጠሩት እኚህ ሰው ለአፍሪካና ለመላው ጥቁር ሕዝብ ነጻነት ፋና ወጊ እንዳልሆኑ ሁሉ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የኦሮሞና ሌሎች ሕዝቦችን የጨፈጨፉና ያስጨፈጨፉ ንጉሥ/መሪ መሆናቸውን ነው አንዳንዶች የሚከራከሩት።

በአጠቃላይ በቀደሙ የሀገራችን የታሪክ ፈርጦችና ጀግኖቻችን ላይ አንዳንች ስምምነት የሌለን ወደ መሆን የመጣን ሁላችንም እንደ ሀገርም ሆነ እንደ ሕዝብ ይወክለናል የምንለው ብሔራዊ ጀግና አልባ፣ የአንድነታችን፣ የነጻነታችንና የልዑላዊነታችን ምልክት የሚሆነን ብሔራዊ ጀግናችንን በስምምነት ለመምረጥም ሆነ ለመወሰን ተለያየና የተከፋፈለ ልብ ያለን ሕዝቦች ኾነናል። ካለፉት ገዢዎቻችን ከበጎነታቸውና መልካም ሥራዎቻቸው ይልቅ ክፉታቸውንና እኩይ ሥራቸውን ብቻ እየመረጥንና እያገነንን እርስ በርሳችን ተለያይተን ለበቀል የምንፈላለግ ሕዝቦች ወደ መሆንም ከተሸጋገርን ሰንብተናል።

ባለፈው ሩብ ክፍለ ዘመንም በሀገራችን የተዘረጋው የብሔር ፖለቲካና በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥትም በሕዝብ ዘንድ ያለውን ቅቡልነት ለማረጋገጥ በሚያደርገው ያላሰለሰ ጥረት የቀድሞ ሥርዐትና መሪዎች በሀገሪቱ ታሪክና በሕዝቡ ሕይወት ውስጥ የነበራቸውን ሚና እና አስተዋጽዖ በብዙ መንገድ እንዲሸረሸር አድርጓል። በዚህም ምክንያት በአብዛኛው የኅብረተሰብ ክፍል ዘንድ በሀገሪቱ ታሪክ የቀድሞ መሪዎች ዙሪያ የጋራ መግባባት እንዳይኖርን ሆነናል።

የብሔር ፖለቲካን ያለ ቅጥ በማጦዝ የብሔረ ፅንፈኝነትን እያስፋፉ፣ ለሉዓላዊነትና ነጻነት የታገሉ ብሔራዊ ጀግኖችን እየገፉ በመሄዱ ሀገራዊ መግባባትና የአንድነት ስሜት ከኅብረተሰቡ ውስጥ ተሟጦ በማለቅ ላይ እንዳለ በተለያዩ ጊዜያት ብሔርን/ዘርን መሠረት አድርገው የተከሠቱ ግጭቶችና ውዝግቦች ጥሩ ማሳያ ናቸው ማለት ይቻላል። በዚህም ምክንያት በአብዛኛው የኅብረተሰብ ክፍል ዘንድ በሀገሪቱ ታሪክና የቀድሞ መሪዎችና ጀግኖቻችን ዙርያ የጋራ መግባባት እንዳይኖረን አድርጓል። እናም በታሪካችን የምንስማማበት፣ ከክልልና ከጎሳ/ከዘር ድንበር ወጥተን ብሔራዊ ጀግናችን ወይም ምልክታችን ነው የምንለው ሰው ለመምረጥ የተሳነን ሕዝቦች ሆነናል።

ሺሕ ዘመናትን ሚያስከነዳ ታላቅ ታሪክ፣ ገናና ሥልጣኔ ባለቤት የሆነች ሀገራችን፣ የሰው ልጆች መገኛ ምድር፣ የነጻነት፣ የአይደፈሬነትና ጀግንነት ዓርማ፣ የአፍሪካ የመላው ጥቁር ሕዝቦች የነጻነት ትእምርት/ምልክት ተደርጋ በምትቆጠር ኢትዮጵያችን ሁላችንንም በአንድነትና በፍቅር መንፈስ የሚያስተሳስረን፣ ብሔራዊ ጀግናችንን መሰየም ወይም መፍጠር አልቻልንም። እስቲ ይህን ጽሑፍ የምታነቡ ሁሉ ለእናንተ ይህን ጥያቄ ደግሜ ላንሳ። ሁላችንንም ሊያስማማን የሚችል የሀገራችን የኢትዮጵያ ምልክት የሚሆን ብሔራዊ ጀግናችን/ጀግኖቻችን ማን ነው/ናቸው ብላችሁ ታስባላችሁ?!

እንደሚታወቀው በደቡብ አፍሪካ ኔልሰን ማንዴላ፣ በኬንያ ጆሞ ኬንያታ፣ በጋና ዶ/ር ክዋሜ ንኩርማ፣ በሕንድ ማኅተመ ጋንዲ፣ በአሜሪካ ፕሬዚዳንቶቹ - ጆርጅ ዋሽንግተን፣ ቶማስ ጀፈርሰን፣ አብርሃም ሊንከን የየሀገራቸው ብሔራዊ ጀግና እና ምልክት ተደርገው በዜጎቻቸው ልብና ሕሊና ውስጥ ሕያው ሆነው፤ ከትውልድ ወደ ትውልድ ታሪካቸውና ለሀገራቸው ያደረጉት ሥራ፣ ውለታ በክብር ይዘከራል፣ ይታሰባል። ለእኛስ በዚህ ዓይነት ብሔራዊ ኩራት፣ ወኔና ስሜት የምናስባቸው፣ የምናከብራቸው ለሁላችንም ምልክት የሚሆነን ብሔራዊ ጀግናችን ወይም ጀግኖቻችን ማን ነው/ማን ናቸው?! ይህ ሁላችንም በስምምነት ምላሽ ልንፈልግበት የሚሻ ዐቢይ ጉዳይ ነው።

ሰላም!!

# “ዐፄ ምኒልክን ሳያከብሩ ለመርዓዊ ሽልማት ቢሰጡ ምንዋጋለው?”

## አርቲስት መርዓዊ ስጦት

አርቲስት መርዓዊ ስጦት በኢትዮጵያ ዘመናዊ ሙዚቃ ላይ የራሳቸው አሻራ ካላቸው ሙዚቀኞች መሀል አንዱ ነው፡፡ ከ1942 ዓ.ም ጀምሮ ጡረታ እስከወጣበት ከዚያም በጤና ምክንያት ተለይቶ የሚታወቅበትን ትራምፔት መጫወት እስካቆመበት ጊዜ ድረስ በተለይም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር ወርቃማ የሙዚቃ ዓመታት አሳልፏል፡፡ ለሙያው ክብርም ከሀገር ውስጥና ከውጭ የተለያዩ ሽልማቶችና የምስክር ወረቀቶችን ተቀብሏል፡፡ መርዓዊን ተክለአረጋዊ አነጋግሮታል፡፡



ግዮን፡- መርዓዊ ስንት ዓመት ሆነህ ዘንድሮ?

መርዓዊ፡- ያለፈው መስከረም 82 ዓመቴን ይዣለሁ፡፡

ግዮን፡- መርዓዊ ምን ማለት ነው?

መርዓዊ፡- እንደ ነገሩኝ በግእዝ “ሙሽራ” ማለት ነው፡፡

ግዮን፡- ለዚህ ይሆን ዘወትር ሙሽራ መስለህ የምትታየው?

መርዓዊ፡- አዬ አንተ! ምኑ ነው ሙሽራ ያስመሰለኝ? በእርግጥ አርቲስት ሙሽራ ነው፡፡ በእኛ ዘመን ያለ ማንም አርቲስት ካልቸገረው በቀር ተዝረክርኮ አይታይም፡፡ ሁሉ ሽክ እንዳለ ነው፡፡ ሙያችንንም፣ ራሳችንንም ስለምናከብር ነው ይህ የሚሆነው፡፡

ግዮን፡- ጋሽ መርዓዊ የአንተ ብቻ ሳይሆን የአባትህ ስምም ለየት ይላል፡፡ ስጦት ማለትስ ምን ማለት ነው?

መርዓዊ፡- ብዙውን ጊዜ ‹‹ስጦታ›› እያሉ ነው የሚጠሩኝ፡፡ የጡረታ መዝገቤ ላይ እንኳ ስጦታ ነው የሚሉት፡፡ ግን ደግሞ ገጠራዊ አነጋገር ሆኖ ነው እንጂ ስጦት ማለት ያው ስጦታ ማለት ነው፡፡

ግዮን፡- ወሎዬ ነህ?

መርዓዊ፡- አዎ፡፡

ግዮን፡- ወሎዬ ነህ ሲባል ግን፤ ወሎ የት?

መርዓዊ፡- አምባሰል ወረዳ፤ ዳቃ የምትባል ቦታ ነው የተወለድኩት፡፡ የዐሥር ዓመት ልጅ ስሆን ደግሞ ወደ ደሴ ሄድኩ፡፡

ግዮን፡- ወደ አዲስ አበባስ እንዴት መጣህ?

መርዓዊ፡- የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የቴአትርና ሙዚቃ ማስፋፊያ ‹‹ቴዎድሮስ›› እና ‹‹ጎንደሬው ገ/ማርያም›› የተባሉ ቲያትርና ሙዚቃ ሊያሳዩ መጥተው በከተማ ውስጥ ቅስቀሳ ያደርጉ ነበረ፡፡

ግዮን፡- በስንት ዓመተ ምህረት?

መርዓዊ፡- በ1941 ዓ.ም መጨረሻ ነበር፡፡ ነፍሱን ይማረውና ተፈራ አቡነውልድ በ1942ዓ.ም መግቢያ ላይ የማዘጋጃ ቤት ሳክስፎን ተጫዋች ነበረ፡፡ ያኔ እየዞሩ ቅስቀሳ ሲያደርጉ ሲምባል እየመታ ሳየው በዚያ ተሳብኩ፡፡ አንድ ብር ከፍዬ ገባሁና ስወጣ በእዚያ የነበሩትን ዐለቆች፤ የቴአትር ክፍል ኃላፊን አቶ ተስፋዬ ተሰማንና የሙዚቃ ኃላፊውን ኃ/ጊዮርጊስ ገመዳን አገኘኋቸው፡፡ ‹‹አስተምሩኝ›› ብዬ ለመንኳቸው፡፡ እነሱም ‹‹አዲስ አበባ ከመጣህ እናስተምርሃለን›› አሉኝ፡፡ በዚያ ነው እንግዲህ የመጣሁት፡፡

ግዮን፡- ማዘጋጃ ቤት ስትቀጠር ደመወዝህ ስንት ነበር?

መርዓዊ፡- አንተ ደግሞ… ምን እንደሱ ብሎ ነገር ነበር? አንድ ብር ነው ለሳሙና የሚሰጠን፡፡

ግዮን፡- በስንት ጊዜ?

መርዓዊ፡- በወር፡፡

ግዮን፡- በቃ?

መርዓዊ፡- አዎን! አንዱን ዓመት እንደዚያ ነው፡፡ ምግባችንን ያበሉናል፣ ልብስ ያሰፉልናል፤ እኛም ምንም አንፈልግም፡፡ ኋላ ላይ ዐሥር ብር ይሰጠኝ ነበር፡፡ ከዚያ በ1947 ዓ.ም የቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ቴአትር ቤት ለመመሥረት ምርጫ በሚደረግ ጊዜ ደመወዜ ከ40 ብር 120 ብር ሲደርስ፤ ‹‹ምን ላደርግበት ነው?›› ብዬ ብሩን ቀጣጥዬ በቁመቴ ለካሁት፡፡

ግዮን፡- ስለብሔራዊ ቴአትር አመሠራረት በዚህ አጋጣሚ ብትነግረን?

መርዓዊ፡- ለቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ 25ኛ ዓመት የዘውድ በዓል አሁን የማዘጋጃ ቤት ሕንፃ ባለበት ቦታ ላይ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ እንዲሠራ ነበር የፈለጉት፡፡ በኋላ ላይ ግን የአሁኑን ብሔራዊ ቴአትር ጣሊያኖች ሲኒማ ማርኮኒ ብለው ጀምረውት ስለነበር እሱን ጨርሳችሁ ግቡ ተብሎ በ3.5 ሚሊዮን ብር ወጪ በሦስት ወር ተጠናቆ ነው በ1948 ዓ.ም በዚያ የገባነው፡፡ ቴአትር ቤቱን የሠሩትም የፈረንሳይ አርክቴክቶች ናቸው፡፡

ግዮን፡- ቴአትር ቤቱ ሥራ ሲጀምር ከነበሩት ቀዳሚ ሙዚቀኞች መሀል ነበርክ?

መርዓዊ፡- አዎን እንጂ! ስልሳ የሚሆኑ ሙዚቀኞች ከ1939 ጀምሮ ነው ሲሠለጥኑና ሲሠሩ የነበሩት፡፡ እኔ ደግሞ የተቀጠርኩት በ1942 ዓ.ም ነበር፡፡ ከመካከላችንም ምርጫ ተካሂዶ ሙዚቃ የምንጫወተው ወደ ሙዚቃ፣ የቴአትር ሙያተኞችም ወደ ቴአትሩ ክፍል ተመደብን፡፡ ይህ ከሆነ በኋላ ከቴአትር ቤቱ ኦርኬስትራ አባላት መካከል አንዱ እኔ ሆንኩ ማለት ነው፡፡

ግዮን፡- ከስንት ዓመት አገልግሎት በኋላ ጡረታ ወጣህ?

መርዓዊ፡- በሙዚቃውም ይሁን ለሃያ ሰባት ዓመታት የኦርኬስትራው ኃላፊ ሆኜ ካገለገልኩ በኋላ በ1986 ዓ.ም ነው ጡረታ የወጣሁት፡፡

ግዮን፡- ታዋቂ የሆንክበትን ክላርኔት የተባለ የሙዚቃ መሣሪያ እንዴት ልታጠና ቻልክ?

መርዓዊ፡- ማዘጋጃ ቤት እያለሁ ሙሴ ነርሲስ መረጡኝ፡፡ ከዚያ ኃ/ጊዮርጊስ ገመዳ አስተማረኝ፡፡ ልጅ ስለሆንኩና አጭርም ስለሆንኩ ነው ክላርኔት እንዳጠና የተደረገው፡፡

ግዮን፡- ለኢትዮጵያ ሙዚቃ ወርቃማው ጊዜ የምትለው የትኛውን ዘመን ነው?

መርዓዊ፡- ከ1952 ዓ.ም ጀምሮ የቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ቴአትር፣ የክብር ዘበኛ፣ የፖሊስና የጦር ሠራዊት ኦርኬስትራዎች አብረው ሲሠሩ በነበረበት ዘመን ከፍተኛ ለውጥ መጥቷል ብዬ አስባለሁ፡፡ የክብር ዘበኞች፤ ከዚህም ከዚያም እያሉ ዓመቱን ሙሉ አስበውበት ነው

የሚቀርቡት፡፡ ጥላሁን ገሠሠም ከሀገር ፍቅር ወጥቶ በክብር ዘበኛ ኦርኬስትራ ‹‹ጥላ ከለላዬ›› የሚለውን ዘፈን ሲዘፍን ነው የማውቀው፡፡ ጥላሁን ውስጤ ገብቶ የቀረው በዚያን ጊዜ ነው፡፡ በ1946 ዓ.ም እኔ የ16 ዓመት ስሆን፤ ጥላሁን 14 ዓመት ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ የአበሻ ልብስ ለብሶ፣ የቀርክሃ ጃንጥላ ይዞ ሲዘፍን ካየሁት ጊዜ ጀምሮ ዛሬ ድረስ ውስጤ አጠቃላይ ሥዕሉ አለ፡፡ እስክሞትም አብሮኝ ይኖራል፡፡ ክብር ዘበኛ ጥላሁንን ይዞ፣ ጦር ሠራዊቶች እነታምራት ሞላን፣ እነዓለማየሁ እሸቴን ይዘው፤ በስተኋላ ደግሞ ምኒልክ ወስናቸው፣ ጠለላ ከበደ፣ እነጌጡ አየለ፣ ፍቅርተ ደሳለኝ ተጨምረው፤ ከፍተኛ የሙዚቃ ዕድገት መጥቷል፡፡ እስከ 1966ዓ.ም በእውነት የኢትዮጵያ ሙዚቃ ወርቃማ ጊዜ ነበር ማለት እችላለሁ፡፡ እስካሁን ጊዜ ድረስ የሚደመጡት ዘመን አይሽሬ ሙዚቃዎች የተሠሩት በዚያን ጊዜ ነው፡፡

**ግዮን፡- የደርግ ሥርዐት ለሙዚቃ እንዲሁም ለኪነ-ጥበብ ያለውን ድርሻ፤ አንዳንዶች ለራሱ ፕሮፓጋንዳ አስቦም ቢሆን እንዳስፋፋውና ድጋፍ እንዳደረገለት ሲናገሩ፤ ሌሎች ደግሞ በተለይም ከሳንሱር፣ ከርዕሰ ጉዳይ መረጣና ከትዕዛዝ ጋር አያይዘው፤ በሙዚቃም ሆነ በአጠቃላይ በኪነ-ጥበብ ላይ ጉዳት እንዳደረሰ የሚቆጥሩት አሉ፡፡ አንተ ወደየትኛው ነህ?**

መርዓዊ፡- ሳንሱር በንጉሡ ጊዜም ነበር፡፡ ደርግ ግን ሁሉንም አብዮታዊ አደረገው፡፡ በሙሉ አሸገው ማለት ይቻላል፡፡ የመዝናኛ ሙዚቃ አልፈለገም፡፡ እኛም ደግሞ ስሜታዊ ሆነን ወደዚያው ነው ያዘነበልነው፡፡

**ግዮን፡- ወዴት?**

መርዓዊ፡- ደርጉ ወደሚፈልገው፡፡ ለምሳሌ መሬት ላራሹ የሚለውን ሙዚቃ፤ ከታምራት አበበ ጋር ያዘጋጀሁት አንዱ እኔ ነኝ፡፡ በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለፈለት መስሎን አብዛኛውን ሙዚቃ ወደ አብዮታዊ መዝሙር የወሰድነው እኛ ነን፡፡

**ግዮን፡- ሳትገደዱ በፍላጎታችሁም ትሠሩ ነበር?**

መርዓዊ፡- እንደውም እኛ ነን የገፋፋነው፡፡ ደርግ ‹‹ያለምንም ደም... ›› ሲል፤ እኛ ደግሞ ‹‹ኢትዮጵያ ተነሽ!›› የሚለውን ሙዚቃ አዘጋጀን፡፡ የሙዚቃው ግጥም የጸጋዬ ገብረመድኅን ነው፡፡ ዜማው የእኔና የሃይማኖት ዓለሙ ሲሆን፤ አቀናባሪው ደግሞ እኔው ነበርኩ፡፡ ‹‹አብዮታዊት እናት ሀገር ወይም ሞት!›› የሚለውን ዜማ የ1969 ዓ.ም የሶማሌያን ወረራ ምክንያት አድርገን በማዘጋጃ ቤት ስናቀርብ፤ አዳራሽ ሙሉ ሕዝብ ነው የተላቀሰው፡፡ ያኔ ‹‹ሀገር ልሙት ወይም አድኑኝ ነው የምትለው›› ሲባል፤ ሕዝቡ አምጾ ነው አደባባይ የወጣው፡፡ የሶማሌያው ጦርነት፣ የሰሜንም ጦርነት ተደምሮ፣ ኢትዮጵያዊው ሁሉ እልህ ይዞት፣ በተለይም የመንግሥት ሠራተኞች የነበርነው ሙዚቀኞች አብዛኞቻችን የአብዮቱ ደጋፊዎች ነበርን ብዬ ነው የማምነው፡፡ ይህ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡

**ግዮን፡- ምን ያህል አብዮታዊ ሙዚቃዎችን ተጫውተሃል?**

መርዓዊ፡- መዓት ናቸው፡፡ ብዙ ሠርቻለሁ፣ አቀናብሬአለሁ፡፡ እንደውም ሌላ ሙዚቃ፣ የፍቅር ምናምን ስሠራ ደስ አይለኝም ነበር፡፡ እውነቱ ይኼ ነው፡፡

**ግዮን፡- በወቅቱ አብረውህ የሠሩ ሁሉ፤ ትልቁም ትንሹም ኢሕአዴግ ከገባ በኋላ ተገዶ እንደሠራህ ነው የሚወራው፡፡ አንተ ግን በፍቅር መሥራትህን በግልጽ ተናገርክ፡፡ እንዴት ነው ይሄ ነገር?**

መርዓዊ፡- እንዴ! ‹‹ገንጣይ አስገንጣይ... ›› ብዬ የዘመርኩት እኔ አይደለሁም? ካሴቱ እኮ በእጃቸው አለ፡፡ እዚህ ብሔራዊ ቴአትር መጥተው ሲያነጋግሩን ‹‹እናንተን ከደርግ ለይተን አናያችሁም›› ብለውናል እኮ፡፡ በሰላም ስለገቡ እንጂ፤ በጦርነት ቢሆን አንደሚረሽኑን ነው የሚሰማን፡፡ ስለዚህ እኛም ዘምረናል፣ እነሱም እየዘመሩ ገብተዋል፡፡ ይልቅ የሚቆጨኝ አሁን ነው፡፡ ለልማትና ለሀገር ዕድገት መሥራት ሲገባቸው፤ በየቴአትር ቤቱ አይሠሩም፡፡ ዓባይን በሚመለከት ጠንካራ ሥራ መች ወጣ? ትልቅ ሙዚቃ የሠሩት ሙሉ ገበየሁና ብንያም ኃ/ሥላሴ ናቸው፡፡ ‹‹ብሔር ብሔረሰቦች... ›› እያሉ በሠሩት መዝሙር እቀናለሁ፡፡ ምክንያቱም ዜማው ሕዝባዊ ነው፡፡ የሚሠራው ለሀገር፣ ለዓባይ፣ ለዕድገታችን ነው፡፡ አይደለም እንዴ? እንዲሁ ከበሮ ለመምታትማ ኢሕአዴግ የራሱ ከበሮ መቺዎች አሉት፡፡ ‹‹ዝፈኑልኝ›› አላለም፡፡ ለሀገራችሁ ዘምሩ ነው ያለን፤ ዘመርን፡፡

**ግዮን፡- በደርግ ጊዜ በሠራሃቸው ሥራዎች ቅሬታ ወይም ጸጸት ይሰማሃል?**

መርዓዊ፡- ለምን? እንደውም እኮራለሁ እንጂ! የምን ጸጸት ነው? በሥራዎቼ በጣም እኮራባቸዋለሁ፡፡ እኔ ሰው ጠቁሜ አላስገደልኩም፡፡ የዘመርኩት ለኢትዮጵያ ዕድገት ነው፡፡ አሁንም የጤናዬ ጉዳይ ባያግደኝ ለሀገሬ እሠራለሁ፡፡ ነገ ርካሽ የሚሆን ሽንጥና ዳሌ እንዳመሰግን አልፈልግም፡፡ እግዚአብሔር ነገ የራሱ ፕሮግራም አለው፡፡ ፕሮግራሙ እስኪሟላ መሥራት ያለብን ለሀገራችን ነው፡፡

**ግዮን፡- በሥራህ ዓለም አቀፍ የጎልድ ሜርኩሪ ተሸላሚ ሆነሃል፡፡ ከአንተ ሌላ ይህን ሽልማት ያገኙት የሀገራችን ሰዎች እነማን ናቸው?**

መርዓዊ፡- እነሎሬት ጸጋዬ ገብረመድኅን፣ የዓለም ሎሬት አፈወርቅ ተክሌ፣ ሐዲስ ዓለማየሁ፣ ከበደ ሚካኤል፣ይድነቃቸው ተሰማና ራሳቸው ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ተሸልመዋል፡፡ ለዐሥራ ስምንት ሰዎች ሲሰጥ እኔና አንዲት ከገበሬ ማኅበር የመጣች ኢትዮጵያዊት ነን በኑሯችን ዝቅ ያልን እንጂ፤ ሌሎቹ የኢትዮጵያ ዕንቁ ሰዎች ናቸው፡፡ ለምሣሌ እኔ ሽልማቱን ላለመውሰድ ወደ አንድ ወር ገደማ አንገራግሬ ነበር፡፡

**ግዮን፡- ለምን አንገራገርክ?**

መርዓዊ፡- ጥላሁን ገሠሠን ያህል ትልቅ አርቲስት እያለ ሽልማቱ ለእኔ አይገባኝም ብዬ ነው፡፡ መጋቢት 18 ቀን 2006 ዓ.ም የባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ‹‹ሁለ-ገብ የጥበብ አባት›› ብለው የኢትዮጵያ ባሕል ማእከል ዕውቅና ሽልማት ሲሰጡም ተቃውሜአለሁ፡፡

**ግዮን፡- በምን የተነሣ?**

መርዓዊ፡- ዐፄ ምኒልክን ሳያከብሩ ለመርዓዊ ሽልማት ቢሰጡ ምን ዋጋ አለው? ዐፄ ምኒልክ በሚሰደቡበት ዘመን መርዓዊ ዘፈነ ተብሎ ሽልማት መስጠቱና ‹‹እናከብርሃለን›› የሚለው አይስማማኝም፡፡ መጀመሪያ ምኒልክን ያክብሩልኝ፡፡ ዓለም አቀፍ የወርቅ ሜርኩሪ ሽልማቱን እንኳ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር ነው የሰጠሁት፡፡ ሽልማቱ አብረውኝ የሠሩት ሙዚቀኞች ሁሉ ሽልማት ነው፡፡

**ግዮን፡- ከሌሎች በተለየ ሁኔታ ለጥላሁን ገሠሠ ስላለህ አክብሮት የሚሰማህን ብትነግረን?**

መርዓዊ፡- ምኑን ልናገር? ጥላሁን ከ‹‹ጥላ ከለላዬ›› ጀምሮ አንዱም ሥራው ያልወደቀበት ነው፡፡ ድምፁ ብቻ አይደለም፤ እንቅስቃሴው ልዩ ነው፡፡ እንደሱ ያለ ድምፃዊ ዳግመኛ በዚህች ሀገር ይፈጠራል ብዬ አላምንም፡፡ የድምፁ ጣዕም ልዩ ነው፡፡ ከተክለ-ሰውነቱ ጀምሮ፣ ሥራው... እጅግ በጣም ነው የማከብረው፡፡ የአምልኮት ያህል! እንደውም በእሱ የተነሣ ራሴን ገድያለሁ፡፡

**ግዮን፡- እንዴት ማለት?**

መርዓዊ፡- አንገቱ ከተቆረጠ በኋላ ወደ መድረክ ሲመለስ፤ የልደቱን በዓል በሚመለከት በብሔራዊ ቴአትር በተሰናዳ ዝግጅት ላይ፣ ‹‹እንኳ አተረፈህ ጥላሁን ገሠሠ፤ ዳግም ልደትህ በሕይወትህ ታደሠ...›› የሚል ግጥምና ዜማ አውጥቼ በወቅቱ የነበረው ሥራ አስኪያጅ ከለከለኝ፡፡ ከዚያ በራሴ ፈቃድ ደርግ የጨመረልኝን አምስት ዓመት ትቼ ጡረታዬን በማስከበር ወጣሁ፡፡ በዚያም ምክንያት ነበር ራሴን ላጠፋ የነበረው፡፡ ሦስት አራት ቀን ራሴን ስቼ ነበር፡፡ ጥላሁንም እግዚአብሔር ይስጠው፤ ለሼህ መሐመድ አላሙዲን ተናግሮ አሜሪካ ሄጄ እንድታከም አድርጎኛል፡፡ አቶ አብነት ገ/መስቀልን የማውቀው በዚያ ምክንያት ነው፡፡ ልቤ ላይ ባትሪ ገብቶልኝ መጀመሪያ 26 ሺሕ፣ በኋላም 36 ሺሕ ብር የከፈለልኝ አብነት ነው፡፡ እኔማ ከየት አባቴ አመጣለሁ?

**ግዮን፡- ምን ያህል ግጥምና ዜማዎችን ሠርተሃል? የአንተን ሥራዎች የተጫወቱትስ እነማን ናቸው?**

መርዓዊ፡- ቁጥሩን አላስታውሰውም፡፡ ግን በጣም በርካታ ናቸው፡፡ ብቻ በብሔራዊ ቴአትር የባንዱ ኃላፊ ስለነበርኩ አዲስ ዓመት በባተ ቁጥር የራሴን የፈጠራ ሥራዎች አቀርብ ነበር፡፡ ከሁሉም ጎልቶ የሚታየኝ ምኒልክ ወስናቸው የተጫወተውና ‹‹አፈር አትንፈገኝ... ›› የሚለው ነው፡፡ ሌላው ‹‹ብዕር! ብዕር›› የሚለውም ነው፡፡ ለምሳሌ አርምስትሮንግ ጨረቃን ሲረግጥ አልቅሻለሁ፡፡ ወዲያውም ‹‹ጨረቃን በሰው እጅ›› ብዬ ግጥም በመጻፍ ተስፋዬ ሳህሉ ተጫውቶታል፡፡


**ግዮን፡- በሀገርም ይሁን በውጭ ስላገኘሃቸው ሽልማቶች ብትነግረን?**

መርዓዊ፡- ትልቁ ዓለም አቀፍ የወርቅ ሜሪኩሪ ሽልማት ነው፡፡ ሁለተኛው ባህል ሚኒስቴር ‹‹ከፍተኛ ምስጉን ሠራተኛ›› በማለት ያበረከተልኝ የወርቅ ሽልማት ነው፡፡ ከእነዚህ ሌላ ዋሽንግተን በሄድኩበት አጋጣሚ በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ አርቲስቶች ሜዳሊያና ከእኔ ጋር ለ22 ዓመታት የኖረውንና አሁንም የማይ ለየኝን የእጅ ሰዓት ሸልመውኛል፡፡ በአፍሪካ ሀገራት እየተዘዋወርን ለሠራነው ሥራ የተለያዩ ዲፕሎማዎች ተሰጥተውናል፡፡

**ግዮን፡- በአንተ ዕድሜ ያሉና በተለያዩ ሙያዎች ያገለገሉ ሰዎች ለሥራቸው የተከፈላቸው ዋጋ አነስተኛ በመሆኑ ቅር ይሰኛሉ፡፡ አንተስ ‹‹ለሕዝብና ለሀገሬ የሠራሁትን ያህል ያገኘሁት ነገር የለም... ›› የሚል ስሜት አለህ?**

መርዓዊ፡- የሚገርም እኮ ነው! ከኢድናሞል በታች ሀርመኒ ሆቴል ያለበትን አካባቢ አውቀዋለሁ፡፡ አንድ ሦስት ዓመታት ቆይቼ ወደ ሥፍራው ስሄድ፤ በፎቅ ተጥለቅልቋል፡፡ በምን ብሩን አግኝተው ሠሩት አልኩ፡፡ እኔ ዕድሜዬን ሙሉ ‹‹ኢትዮጵያ!... ኢትዮጵያ!... ›› ስል፤ የቀበሌ ቤት ብቻ ነው ያተረፍኩት፡፡ በሙያህ ያተረፍከው ሀብት ካልከኝ የእኔ ሀብት ሕዝቡ ነው፡፡ በተረፈ ልጆቼ ናቸው ሀብቶቼ፡፡ እኔ ኢትዮጵያን ፍቅሯን፣ ሰላሟን፣ ነጻነቷን ነው የምፈልገው፡፡ እንደ ሠራሁት ባለማግኘቴ ምንም አይቆጨኝም፡፡ ባለፈው ሀገሬ ኢኮኖሚዋ ባለማደጉ በቂ ልትከፍለኝ አልቻለችም፡፡ ስለሌላት ነው ያልሰጠችኝ፡፡ ጡረታ ስወጣ 390 ብር ነው ይገኘ የወጣሁት፡፡ ከእኔ በታች የነበረ፣ ዐለቃው የነበርኩ ሰው ደግሞ አንድ ሺሕ 8 መቶ ብር አግኝቶ ወጥቷል፡፡

የጊዜና የሁኔታዎች አለመገጣጠም እንጂ መርዓዊን ለመጉዳት የተደረገ ነገር የለም፡፡ ሀገሬ አልከለከለችኝም፡፡ በነበራት ዕድገት አገልግዬአታለሁ፡፡ እሷም አቆይታኛለች፡፡ ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሣሁን አሁን በሚሊዮን የሚቆጠር ብር የሚከፈለው ነው፡፡ አባቱ ትከሻው ላይ አድርጎት ሲመጣ እናይ ነበር፡፡ ዛሬ ምናለ አባቱ አፈር መስኮት ኖሮት ብድግ ብሎ ባየው እላለሁ፡፡ ይህ ልጅ በሙዚቃ ከፍተኛውን ገንዘብና ዝናና ክብር ያገኘ ልጅ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ያረካሃል እንጂ አያስቀናም፡፡ የቆሻሻ መኪና እየታጠበ እኮ ነው ለሥራ ተሳፍረን እንሄድበት የነበረው፡፡ ዛሬ ሥራችን አድጎ ይህን ውጤት ሲያመጣ ደስ ነው የሚልህ፡፡ ያለፈው አልፎ ኢትዮጵያ መታደስ አለባት፡፡ ፖለቲካውን በስምምነት ከያዙት ኢትዮጵያ ታላቅ ሀገር ናት፡፡



የሱፍ ጌታቸው

# የሃይማኖት አባቶች ሀገር የት ነው?

እምነት ሥነ ምግባራዊ ዕድገት ነው:: ፍትሐዊ አገልግሎት ነው:: የእኩልነት ሚዛናዊ እውነት ነው:: የፍቅር እና የበጎነት ጎዳና ይሆናል:: ስለ ፍጡራን መጨነቅ ይፈጠራል:: በመልካም ማዘዝ ከክፋት መከልከል ሃይማኖታዊ ግብ አለው:: በደል ማውገዝ፤ በዳይን ማረቅ የሰው ባሕሪ ቢሆንም የሃይማኖት አባቶች የሃይማኖት ተቋም ትልቅ እሴት፤ ጥንድ ኃላፊነት ለመሆኑ ብዙዎች ይስማማሉ::

በሙስሊሙ ማኅበረሰብ የነቃ ተሳትፎ ካላቸው አቶ ሐሰን ዓሊ በሃይማኖት ተቋማት ወቅታዊ የሀገር ሁኔታ ተወያየን ሐሳባቸው ሲጨመቅ ይህ ወጣው፤ «ባሳለፍነው 27 ዓመታት የሃይማኖት ተቋማት በሕዝባቸው ዘንድ ተቀባይነት እንዳይኖራቸው በመንግሥት ደረጃ ተሠርቷል:: ይህም ተሳክቷል፤ እነሱም ከመንፈሳዊ ባሕሪያቸው ተፋተው ካድሬ የሚያስብል ደረጃ ደርሰዋል:: በሽምግልናም ሆነ ሀገራዊ ጉዳይ እንዳይሰሙ ሆነዋል:: ለሕዝብ የሚነግሩት ነገር መንግሥት ከሚያስፈራራው ነገር የተለየ አይደለም:: ከሚያከብራቸው የሚያፍርባቸው ሕዝብ ይበልጣል:: የተለየ ሐሳብ አማራጭ አለን የሚሉ "የፖለቲካ ፓርቲዎች" እንኳን በሀገር ደረጃ እርስ በርሳቸውም፤ እንዳይስማሙ እንዳይጠናከሩ፣ የመወያያ እና የመፍትሔ አካል እንዳይሆኑ አፈራርሰዋቸዋል:: በሕዝብ እምነት የማይጥልበት ደረጃ ደርሷል::

"የፍትሕ ሥርዐቱም" ፣ ከሕዝብ ይልቅ የገዢው በደል መሣሪያ ሆኗል:: በሀገሪቱ ውስጥ ለሚፈጠር ያለመግባባት መፍትሔ የሚሰጥ የሚሸመግል እሴቶችን የሚጠብቅ በተቋም ደረጃ ለማግኘት የማይታሰብ ደረጃ ሆኗል:: መስኩ በኢ-ፍትሃዊነት ጨቅይቷል "ኮራብት" ሆኗል... ይላሉ:: ለዚህ ሐሳብ ስሙን የቀየርኩት አማር ባነሳነው ሐሳብ ላይ ይህን ብሎናል "ትክክለኛ መንፈሳዊ የሆኑ ሕዝብ የሚያከብራቸው፤ የተናገሩትን የሚሰማቸው፣ የመፍትሔ አካል መሆን የሚችሉት ሕዝባቸውን በማስጠንቀቅ እንጂ መንግሥትን መሞገት ዋጋ ያስከፍላል:: ሥርዐቱም ለእንደዚህ ዓይነቶች ቦታ የለውም፤ ይቀጥፋቸዋል ያሥራቸዋል፣ ያሳድዳቸዋል" ይላል::

አቶ ሀሰን ዓሊም የወጣት አማርን ሐሳብ ይጋራል " ከየትኛውም መስክ ኅብረተሰብ ውስጥ ተቀባይነት ያላቸው ተፅዕኖ መፍጠር የሚችሉት ሰዎች መንግሥት በጤናማነት አይመለከተውም፤ ሀገሪቱ ካለችበት ችግር ለመታደግ እፈልጋለሁ የሚል "መንግሥት" እንደ መንግሥት የሃይማኖት አባቶች ምክር አያስፈልገውም:: የሃይማኖት አባቶች ምክር የሚያስፈልገው ለሕዝብ ነው:: አሁን ፖለቲካው ከሯል:: መንግሥት ሀገር ለመታደግ ምን ማድረግ እንደሚገባው? ምን እንደተጠየቀ ያውቃል፤ ያንን ጥያቄ በኃላፊነት እና በቅንነት መፈጸም ነው ሲል " ሲል ሐሳቡን ያስረግጣል::

ለሰው ልጅ ሀገሩ የክብር ጌጡ ነው:: የማንነት ምንነቱ ሀገር ነው:: "ሰው በሀገሩ..." የሚለው ሐረግ ሰፊ ሐሳብ ያገተ ነው:: ይህ ፅንሰ ሐሳብ ብዙዎች ዘንድ መጠቀሱ ሀገር የቡድን፣ የግል እሴቶች ውህደት...የኃላፊነት ማማነትን ያመላክታል::

"ሃይማኖት የግል ነው ፤ሀገር ግን የጋራ ነው" የሚለው የብዙዎች ስምምነት መርህ በመከባበር የጋራ ሀገር የመጠበቅ፣ የማዳን ኃላፊነትን ያሳያል:: የሃይማኖት እሴት ለሀገር ደህንነት ሠላም ዋስትና የመሆን ተልዕኮን ያመለክታል:: "በሀገር ጉዳይ ሰጪም ተቀባይም የለም፤ ሀገር ሕያው ናት" ይላል ጸሐፊው፤

የሃይማኖት መሪዎች የሃይማኖት ተቋማት ቤተ-አምልኮ በጋራ የሀገራችን ጉዳይ፣ አዋጅ ያልገታው፣ የአደባባይ ግድያ ያላስበረገገው ፣በደም የዋጀለት፣ሕይወት እየከፈለለት ያለው የሀገር ወቅታዊ የሕዝብ ብሶት የለውጥ ጥየቄ፣ የፖለቲካ ትኩሳት፣ መንግሥት ባላስገኘው መፍትሔ የሃይማኖት መሪዎች ሀገር ከመታደግ፣ ሠላም ከማስገኘት አንፃር ምን እያደረጉ ነው የሚለው የብዙ ዜጎች ጥያቄ ነው::

ወጣት ዑስታዝ መሐመድ አባተ የማስትሬት ዲግሪውን ከወደ ሱዳን ያገኘ ሲሆን" በደምፃችን ይሰማ!" የሙስሊሞች ሠላማዊ ንቅናቄ በብዙ ወጣቶች ዘንድ ተሰሚነት ያለው አክቲቪስት ነው:: በሙስሊሙ የመፍትሔ አፈላላጊ የእስር ዘመቻ በአቡበከር ፋይል ታስረው አሁን በመጨረሻ በምሕረት ከተፈቱ አራት ወንድሞች አንዱ ነው:: ባነሳንው ፍሬ ጉዳይ እንዲህ አለን «የሀገር ጉዳይ ለድርድር የሚቀርብ አይደለም» ኢስላም የሠላም ፈርጦችን ያበረታታል:: የሃይማኖት ተቋማት አሁን ያለውን የሀገሪቱን ያለመረጋጋት ሁኔታ ሀገርንም፣ መንግሥትንም ይታደጋሉ ብዬ አላምንም:: ሕዝብ እነሱን አይሰማም:: የየትኛውንም ሃይማኖት ይወክሉ እነሱ በቴሌቪዥን መስኮት የሚመጡት የመንግሥትን አቋም በሃይማኖት ካባ ሊነግሩን መሆኑን ሁሉም ስለሚያውቅ « በዚህ ሥርዐት ሃይማኖት ነፃ የሚወጣው መቼ ነው?» የሚል ጥያቄ በማንሣት የሚያጉረመርም ይበዛል:: የሃይማኖት ክብር የሌላቸው የሃይማኖት ካባ የለበሱ "ካድሬዎች" የሚል ወቀሳው ይቆረቁራል የማያምኑበትን የሚያደርጉ ያሳዝናሉ::

ከሃይማኖት ተቋማት ውጪ ባመኑበት፣ በተማሩበት ለፈጣሪያቸው ቃል የተገዙ ፣ ትውልድን የሚያቀኑ፣ ለሀገር ሠላም የመፍትሔ ጋት የሆኑ መሻኺካዎች፣ ዑለማዎች ፣ዱዐቶች ብዙዎቹ አሁን ያለው ተጨባጭ ሁኔታ፣ የፖለቲካው ፍሰት ዙሪያ በቂ የመረጃ እጥረት ይገጥማቸዋል:: ለሕዝባቸው ቅርብ የሆኑ የሃይማኖት ዱዓቶች መንግሥት ከሕዝብ ጋር ያለው የሻከረ አካሄድ ለማረቅ፣ ኢ–ፍትሕዊነቱን "ተው!" ለማለት ፈተናው ከባድ እንደሆነ ቢታመንም ፤ከእውነት ወገን የሆነችውን እውነት በመናገር በዚያም እውነት ላይ መፅናት ፤የተናገሩት እውነት ዋጋ ማስከፈሉ አይቀሬ ይሆናል::

በእውነታቸው ዙሪያ የሚሰባሰበው የመበራ ከቱን ያህል፣ በተቃራኒው የእውነታቸው ጠያቂ የሆነው መንግሥት ሊነሳባቸው ይችላል:: በተናገሩት እውነት ሕዝብ ከስሜታዊነት ወጥቶ ሀገር እና ሕዝብ ሊታደግ የሚችልበትን፣ አትራፊ የሆነ ከግጭት የፀዳ አቅጣጫ ሊኖራቸው ይገባል:: አብዛኛው የሀገሬ ሕዝብ በሃይማኖቱ ፅናት ላይ ላለው ሰው ልዩ ከበሬታ አለው:: የሚሉትን ይሰማል:: በሰጡት አቅጣጫ ለመትመም አያወላዳም፣ ከመንግሥት ትከሻ እና ከለላ በራሳቸው የቆሙ የሃይማኖት አባቶች በምድራዊ ሀገራቸው ምንዳ የሰማዩን ቤታቸውን፣ ሀገራቸው የሚፈልጉ ናቸው:: እነሱ ተፅኖ ፈጣሪነታቸው የላቀ በመሆኑ ሀገር የመታደግ ሚናቸው ወሳኝ ቢሆንም፤ መንግሥት እጁን ዘርግቶ የሚቀበላቸው አይሆንም ሲል ስጋቱን ይገልፃል::

የሀገር ሠላም ለሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ ሠላም ነው:: የቤተ አምልኮ ደህንነት ነው:: ለአማኞች የአምልኮ ነፃነት ነው:: ነብዩ መሐመድ (ሰላም እዝነት በሳቸው ላይ ይሁን) ነብይ ሆነው በተላኩበት የመጀመሪያው ዘመን ትውልዳቸውን በእምነታቸው ምክንያት ሀገር አልባ አድርገውባቸዋል:: እሳቸው፣"ፍትሀዊና ሀቀኛ መሪ ይኑር! ፈጣሪ በአንድነቱ በብቸኝነቱ ይመለክ! ለሰው ልጅ ጉዳት የሚያስከትል ማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በሙሉ ይጥፋ! የሰው ልጅ ሁሉ በፈጣሪ ፊት እንደ ማበጠሪያ ጥርሶች እኩል ናቸው፤ አንዱ ከሌላው ሊበልጥ የሚችለው ፈጣሪውን በማክበር ነው:: ሰው በመበላለጡ፣ በቀለሙ ፣በጎሳው...በሀብቱ... በማኅበራዊ ኑሮ ደረጃው አይደለም" የሚለውን ሲያስተምሩ ሁሉም የአስተምህሮታቸው እውነትነት ቢያምኑም የግል ጥቅማቸውን የሚነካ ስለነበር ስለ አስተምህሮቱ ሐቀኝነት ይልቅ በጠላትነት ፈረጇቸው፤ እና ነብዩ መሐመድ ( ሰለም እዝነት በሳቸው ላይ ይሁን) በወቅቱ ላጋጠማቸው ተቃውሞና ችግር ውስን ለሆኑ ተከታዮቻቸው መጠለያ የሚሹበት ወቅት ነበር ...እፎይታና ሠላም የሚያገኙበት ሀገር፣ መንግሥትና ሕዝብ ያሻቸው ነበር:: እሳቸውም አሉ፣ "እናንተ ተከታዮቼ ሆይ! ያጋጠማችሁ ችግር እስከሚቀል ወደ ሐበሻ ሀገር ሂዱ፤ እርሷ ዘንድ የማይበድል ሀቀኛ ንጉሥ አለባት፤ ማንም እርሷ ዘንድ በደል አይደርስበትም፤ የእውነት ምድር ናት::" ሲሉ ባልደረቦቻቸውን አሳሰቡ፤ እንግዲህ በሀገር ላይ የግፍ በትር ሲበረታ፣ መንፈሳዊ ሕይወትም ይቀጭጫል:: መስተጓጎሉም ይከፋል፤ ሠላም ይደፈርሳል፤ በእርግጥ ኢማን የፈተና ፍሬ ናት::

ዜጎች ዛሬም በእጥፍ ሀገር ፍለጋ በባሕር፣ በየብስ...የመከራ ጉዞን ተጋፍጠው እየተሰደዱ ነው:: ከየቀዬአቸው እየተፈናቀሉ ነው:: ሥርዐቱ




በዜጎቹ ላይ በመክፋቱ በሚያስከትለው ቁጣ የአፈሙዙ እልቂት በዛ፡፡ የሕዝብ ለሕዝብ መጨራረሱ በረታ፡፡ ደራሲና ፖለቲከኛው ዳንኤል ተፈራ እንዳለው "ሀገር የተቀማ ትውልድ" ሆንን፡፡

"ለዜጎቿ ይህች ሀገር ከምንም በፊት ታስፈልጋለች፡፡ ልቡ ያልኮበለለ ዜጋን ማግኘት ፈተና ሆኗል፡፡ ወቅታዊ የፖለቲካ ጡዘት ያሳስባል፡፡ ሥልጣን የሕዝብ ንቀት ማራገፊያ መሆኑ ያሳቅቃል፡፡ ኢትዮጵያን የመሪዎቿ ሀገር ብቻ የማድረግ ሽኩቻ ማክትሚያው ርቋል፡፡ ሀገር ማለት ሰው ነው እና "ሀገርን" "ሰውን" ከፖለቲካው ሥልጣን በላይ ትኩረት ልንሰጠው ይገባል የሚል የሃይማኖት መሪ አጣን" የሚሉ የአማኞች ቁጥር ሽቅብ ነው፡፡

የሙስሊሙ የመፍትሔ አፈላላጊ ኮሜቴ ጸሐፊ አህመድ ሙስጠፋ "የሃይማኖት አባት የሀገር ካስማ ናቸው፤ ይሁን እንጂ ሥርዐቱ የሃይማኖት ወገን ንዶታል፡፡" ይላል፡፡

ዛሬ እነሱ በሚያስፈልጉን ወቅት ለፖለቲካው እንጂ ለፈጣሪው ታማኝ ያልሆነ፣ ለመንግሥት እንጂ ከሕዝብ ታማኝነት የራቀ፣ ለእውነት ያልቆመ፣ የፍትሕ ሳንካ የሆኑ የሃይማኖት ጭንብል የለበሱ ዐቅመቢሶች ፈልተዋል፡፡ እነዚሁ ሽቅብ ይመጣሉ በሀገርም በሕዝብም ለሚከሰቱ ቀውሶች ከችግር ፈቺነት ይልቅ የችግር፣ የግጭት እሳት ይሆናሉ የሚለው ሐሳብ ተራምዷል፡፡

የሙስሊሙ የመፍትሔ አፈላላጊ ጸሐፊ አህመድ ሙስጠፋ እንደሚለው "የችግሩ መሠረት ሃይማኖት ሕዝብ አደንዛዥ እፅ ነው ብሎ በማርክስ ርዕዮት ያደገ ሥርዐት፣ ሃይማኖት ያለውን ዋጋ መቀበል ይከብደዋል፡፡ ሚና አልባ፣ ሰው አልባ የሃይማኖት ተቋማት ሕዝብ ላይ ተፅዕኖ ፈጥረው ሀገር ይታደጋሉ ለማለት ይቸግረኛል» ይላል፡፡

የመስጂድ ኢማሞች፣ ዑለሞች፣ መሻኺኮች፣ ዳዒዎች የሚያገለግሉት ማንን ነው የሚል መጠይቅ መምዘዝ ጉንጭ አልፋ ሙግት ውስጥ ሊከት ይችላል፤ እነሱም ተመካክረው የሚመልሱልን ዓይነት ሆነው ሁሉም በአንድ ድምፅ " አላህን ነው" ይሉን ይሆናል፡፡ እኛም ይህን ኒያቸውን( ሐሳባቸውን) የመጋፋት አቅም የለንም፡፡ የሚያስተምሩን ሐቅ የሚነግሩን እውነት በደልን አይተን ዝም የሚያስብለን አይደለም "የቻለ ይከልክል በድርጊት፤ ያልቻለ ይናገር በምላሱ፤ ያልሆነለት በልቡ ይጥላ" ብላችሁናል ሁሉም የአቅሙን ተሳትፏል የሚሉ በርካታ ናቸው፡፡

ከእናንተ ብዙዎች ግን "ዝምታን" መርጣችኋል፤ የመሪዎች በትር አማኞችን ሲያደቅ የት ናችሁ?! በሹመኞች ትዕዛዝ ዜጎች ሲገደሉ "ሰላተል ጀናዛ" አሰግዳችሁ ለምን ነፍስ ቀጠፋችሁ ብላችሁ ሽቅብ መንግሥትን መሞገት ሰጋችሁ? የሀገር ልጆች በፖለቲካ ሴራ ዜጎች ወገኖቻቸውን አፈናቅለው ታዛ አጥተው በጋለ አሸዋ ጭው ባለ በረሓ ሲፈሱ፣ ዱር ሲከትሙ፤ በዚህ ውስጥም በጥይት ተመትተው 'ከፈን ያጣ ሬሳ' ጎዳናውን ሞልቶ ሕዝብ በበትረ ሥልጣኑ የግፍ በትር ሲወቀር... ሲታሰር... ሲሰደድ...በነፃነት ፍለጋው ሲገደል...ሆ! ብሎ ሕዝባዊ ቁጣውን ሲገልፅ...የቤተ እምነት መሪዎች ፣የሃይማኖት ተቋም አካሎች ትኩስ ሬሳ የታቀፈውን የሐዘን ከል የለበሰውን ሕዝብ ሲወቅሱ እንጂ ፈርኦናዊ የሥልጣን ግፍ ስታወግዙ ያለመሰማቱ የሃይማኖት መሪዎች በምድር ሀገራቸው የት ነው? ያስብላል፡፡ እውነትን አስተማሪዎች እውነትን መናገር እውነትን መጋፈጥ ምነው ሰጉ ያስብላል?!

የፖለቲካ ግብ በሥልጣን ግብ ሀገርን ማስተዳደር ነው፡፡ ፍትህ...እኩልነት...ነፃነት ማስፈን ዲሞክራሲያዊ ባህሪ ነው የሚለው የመስኩ ባለሞያዎች መርሕ ለሀገር ሹመኞች ከዲስኩር የዘለለ የሂደት፣ ለውጥ ተስፋ ያለማየታችን ብዙዎቻችንን የለውጥ ናፋቂ ትውልድ አድርጎናል፡፡ ሃይማኖት ሰማያዊ ግብ ይዞ ሥነ ምግባራዊ ድምቀት አላብሶ ከተጨቋኝ ጎን ቆሞ፣ ጨቋኝን ማውገዝ ትልቅ እሴት መሆኑን ሽቅብ ለሃይማኖት መሪዎች ማስታወስ ድፍረት እንዳይሆንብን ያሰጋል!

አሁን ባለው የሀገር ሠላም መደፍረስ፣ የዜጎች ያለመረጋጋት ተጠያቂው ማን ሊሆን እንደሚችል የሃይማኖት ካባ የለበሱ የሥርዐቱ የሃይማኖት ክንፍ የሆኑ የፖለቲካ ሹመኞችን መጠየቅ የግፍ ዘመን ማራዘም ነው ይላሉ፡፡ ሃይማኖቱ በፖለቲካው እየተገዛ ከፈጣሪ ፍራቻ ይልቅ የአምባገነኖች ትዕዛዝ የፈጣሪ ትዕዛዝ እንደሆነ የማድረግ ተፅዕኖው እየበረታ መምጣቱ ያሳስባል፡፡ የእነዚህ የካድሬ ዑስታዞች የሌሊት ወፍ ባሕሪ መላበስ የሙናፊቅነት ድርጊታቸው መጎን የዜጎች ደህንነት የሀገር ሰላም የበትረ ሥልጣን መረጋጋት ሊያስገኝ ያለመቻሉ ልብ ሊባል ይገባል፡፡

ሃይማኖት በደልን ጥዩፍ ነው፡፡ ፍትሐዊነት ጌጡ ነው፡፡ በቅዱስ ቁርዓን "እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ለአላህ ቀጥተኞች ሁኑ ሕዝቦችንም በመጥላት፣ ባለማስተካከል ላይ አይገፋፉችሁ፤ አስተካክሉ!... "(5:8 ) በሌላ የቁርዓን አንቀፅ "...በሰዎች መካከል በፈረዳችሁ ጊዜ በትክክል እንድትፈርዱ ታዛችኋል... " ይላል በነብዩ መሐመድ (ሰላምና እዝነት በሳቸው ላይ ይውረድ ) አስተምህሮት ሰዎች ሁሉ ልክ እንደ ማበጠሪያ ጥርሶች እኩል ናቸው ማለታቸው ይኸው የፍትሕን እኩልነት የሚያሳየን ነው፡፡

ፍትሕ የሁሉም
ጌጥ ሲሆን የሠላም በርሃን የሀገር ፀሐይ
ይሆናል፡፡

# "በመለስ ዜናዊ ሞት ክፉኛ ተደብድቤ ሕይወቴ በተዐምር ተርፏል"

**አቶ ዘሪሁን ገብረእግዚአብሔር**



አቶ ዘሪሁን ገብረ እግዚአብሔር ታደሰ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ በርካታ ዓመታትን አሳልፈዋል። በተሳተፉባቸው የፖለቲካ ፖርቲዎች ዉስጥ ገኸሮውን ፓርቲ በመቃወም ሰላማዊ ትግል አካሂደዋል።

ኢሕአዴግ የፀረ-ሽብር አዋጅን ባወጣ ማግስት የ‹‹ሽብርተኝነት ተግባር ፈፅመዋል›› በሚል ክስ በቁጥጥር ሥር ካዋላቸው የፖለቲካ ሰዎች መሐልም ግንባር ቀደሙ ናቸው። በጊዜው በተመሰረተባቸው ክስ የ17 አመት እስርና የ50 ሺሕ ብር ቅጣት የተወሰነባቸው አቶ ዘሪሁን ከቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ሞት ጋር በተያያዘ በእስር ላይ እያሉ ከባድ ድብደባ ተፈፅሞባቸዋል። በቅርቡ መንግሥት የፖለቲካ እስረኞችን በምሕረትና ክስ በማቋረጥ ማሰናበቱን ይፋ ሲያደርግ ከሰባት ዓመት እስር በኋላ የተፈቱት አቶ ዘሪሁን ገ/እግዚአብሔርን የግዮን መጽሔቱ ሮቤል ምትኩ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ አነጋግሯቸዋል።

**ግዮን፡- እንኳን ለቤትዎ አበቃዎ። ውይይታችንን ስለራስዎ አጠር ያለ ማብራሪያ በመስጠት ብንጀምርስ?**

አቶ ዘሪሁን፡- አመሰግናለሁ። የተወለድኩት አዲስ አበባ በልዩ ስሙ መርካቶ ተብሎ የሚጠራው አካባቢ ነው። አሁን የምኖረው ኳስ ሜዳ አካባቢ ነው። አንደኛ ደረጃ ትምህርቴን ደብረዘይት አፄ ልብነ ድንግል ት/ቤት ሁለተኛ ደረጃ በመድኃኔ ዓለም ት/ቤት ነው ያጠናቀቅኩት። የፖለቲካ ተሳትፎዬ ከደርግ ጊዜ ነው የሚጀምረው። በ1983 ዓ.ም ኢሕአዴግ ወደ ስልጣን ከመጣ በኋላ ግን ከፍ ባለ ደረጃ ወደ ፖለቲካው በመሸጋገር (በመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት) መኢህድ የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚና የወጣቶች ክንፍ አደራጅ በመሆን ረዘም ላለ ጊዜ ሰርቻለሁ። በወቅቱ የድርጅቱ መሪ የነበሩት ፕሮፌሰር አስራት በእስር ላይ እያሉ እኔም ከድርጅቱ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ጋር በተያይዘ ሰንዳፋ እስር ቤት ከሻለቃ አድማሱና ዮዲት እምሩ ጋር ለወራት ታስሬያለሁ። መዐህድ ዘግየት ብሎ መኢአድ ወይም መላው የኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ተብሎ ሲቀየር በተፈጠሩ ሂደቶች ውስጥ በነበረው ያለ መግግባባት ራሴን አግልዬ ወደ ኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ፖርቲ መጥቻለሁ። ይህን ፖርቲ የመሠረትነው በ1996 ዓ.ም አጋማሽ ላይ ነው፤ ድርጅቱ ሲመሰረት መጀመሪያ ላይ ዋና ጸሐፊ ነበርኩ። ከሦስት አመት በኋላ የፖርቲው ፕሬዘዳንት ሆንኩ፤ ስታሰር የድርጅቱ ኃላፊ ነበርኩ።

**ግዮን፡- ለእስር የተዳረጉበት ምክንያት ምንድነው የተያዙትስ መቼ ነበር?**

አቶ ዘሪሁን፡- የተያዝኩት ሰኔ 12/2003 ዓ.ም ነው፤ በዕለቱ ከጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ ጋር ቀጠሮ ነበረኝ። ወደ እሱ ለመሄድ ስንቀሳቀስ መንገድ ላይ ወታደሮች ከበው "ምንድነው?" ስል "የፀረ ሽብር ግብረ ኃይል ይፈልግሃል" በማለት በካቴና አስረው መኪና ላይ ጫኑኝ። በወቅቱ ስያዝ በቪዲዮ እየተቀረፅኩ ነበር። እንደያዙኝ በቀጥታ ወደ ቤት ወሰዱኝ። ፍጹም አስነዋሪ በሆነ መልኩ ቤት ውስጥ ለሦስት ሰዓት ያህል ፍተሻ አደረጉ። የቤተሰብ ሃላፊ መሆኔን ስለሚያውቁ ብዙ ከባድ ነገሮችን በብርበራው ሰዓት አካሂደዋል። ፋሽስት እንኳን የማይሠራውን አስነዋሪ ተግባር ፈጽመዋል። ይሄንን ሁሉ ነገር ካደረጉ በኋላ ፍተሻውን ለሚመራው ሰው ስልክ ተደውሎለት ሲጠየቅ "ምንም ነገር አላገኘንበትም" የሚል ምላሽ ለአለቃው ያስተላልፋል። ይሄኔ ይዘኸውና ይሉታል ፤ወታደሮች በዛው መልክ አጅበው ማዕከላዊ ወሰዱኝ።

**ግዮን፡- ማዕከላዊ ሲደርሱስ ምን ገጠምዎት?**

አቶ ዘሪሁን፡- ማዕከላዊ እንደ ደረስኩ ስሜን መዘግበው ቀጥታ ወደ ኃላፊዎቹ እነ ተክላይ ቢሮ ወሰዱኝ። እነሱ ቢሮ ካስቀመጡኝ በኋላ ‹‹ ከኤልያስ ክፍሌ ጋር ማን አገናኛችሁ? ምን እንደምትሠራ እናውቃለን፤ ሁሉንም ነገር ሳትደብቅ ንገረን" አሉኝ። እኔም ምንም የማውቀው ነገር የለም አልኳቸው። በተፈጥሮዬ ትንሽ ቆጣ የማለት ባህሪ ስለበረኝ እነርሱ ምንድነው ታድያ በትዕቢት የምትመልሰው በማለት ለማዋከብ ሲሞክሩ ባህሪዬ እንደሆነ ለማስረዳት ሞከርኩ። በወቅቱ ሊሰሙኝ ፈቃደኛ አልነበሩም። እንደውም ‹‹እንኳን አንተን ጠቅላይ ሚኒስትሩን እዚህ አምጥተን እንገርፋቸዋለን" ሲሉኝ እሱ የእራሳችሁ ጉዳይ ነው የሚል ምላሽ ሰጠኋቸው። ‹‹በኋላ ስትገረፍ ታወጣለህ ሂድ ውረድ›› በማለት ከሃላፊዎች ቢሮ አስወጡኝና በተለምዶ ስምንት ቁጥር የምትባለው ጨለማ ክፍል አብገቡኝ፤ ከቤተሰብም እንዳልገናኝ ከተደረገ በኋላ በሁለተኛው ቀን ለምርመራ ጠሩኝ።

**ግዮን፡- ለምርመራ የተጠሩት ቀን ነበር ማታ?**

አቶ ዘሪሁን፡- ማታ ነው። የሆነ ቢሮ ካስገቡኝ በኋላ ትንሽ ቦክስ ዱላ ነገር አቀመሱኝ... ምንድነው ስላቸው ‹‹እያንዳንዱን ነገር አውጣ፤ የግንቦት ሰባት አባል ነህ፣ ቴሌን ልታቀጥል ነበር፣ ፋብሪካ ልታነድ ነበር፤ መብራት ሃይልን ልታወድም ነበር›› የሚል ጥያቄ መጣ። እኔም ስለምትሉት ጉዳይ አላውቅም፤ማስረጃ ካላችሁ በህግ ጠይቁኝ አልኳቸው። ያሰማራኸውን ሃይልና ሴልህን አምጣ ተናገር በማለት ከባድና ዘግናኝ ድብደባ ፈፀሙብኝ ‹‹ከኤልያስ ክፍሌ ትዕዛዝ እየተሰጠህ ታስፈፅማለህ፤ እሱ የሻዕቢያና የግንቦት ሰባት ተላላኪ ነው›› በማለት ከባድ ምርመራ አደረጉብኝ። እኔ ደግሞ ‹‹ኤልያስ ክፍሌን የማውቀው በጋዜጠኛነት እንጂ ሽብርተኛ መሆኑን አላውቅም›› የሚል ምላሽ ብሰጥም ሊሰሙኝ ፈቃደኛ አልሆኑም። ራስህን ከመጉዳትህና ሌላ ነገር ከመድረሱ

ከፊት እውነቱን ንገረን እያሉ በተደጋጋሚ በተለያየ ጊዜ እየጠሩ እጄን በካቴና አስረው ሰቅለውና ገልብጠው ገረፉኝ ፤ደበደቡኝ፡፡ ይኸው እንደምታየው እጄ እንዲህ የተጎዳው ማዕከላዊ ወንጀል ምራመራ በቆየሁባቸው ሶስት ወራት በደረሰብኝ ዘግናኝ ድብደባ ነው፡፡

**ግዮን፡- ወደ ክስ ሂደቱ ስትገቡ አቃቤ ሕግ በእናንተ ላይ የከፈተው ክስ ምን ነበር?**

አቶ ዘሪሁን፡- አንደኛው ህገ ወጥና ለሽብር ተግባር የሚውል ገንዘብ ከውጭ ተቀብላችሁ በአገር ውስጥ አንቀሳቅሳችኋል፡፡ ሁለተኛው ከኦነግ ኦብነግና በወቅቱ ጥምረትና ግንባር ከፈጠሩ ተቃዋሚዎች ጋር የሽብር ሥራን በአገር ውስጥ ለመፈጸም አስባችኋል የሚል ነው፡፡ ሦስተኛው ልማታዊ ናቸው የሚባሉ ትልልቅ ድርጅቶችን ለማውደም አሲራችኋል፤ አራተኛው በአገሪቱ ውስጥ ያሉ ባለሀብቶችን ንብረት ለማውደም አቅዳችኋል የሚል ሲሆን፤ አምስተኛው ተባባሪ ሴሎችን ለመዘርጋት የሚል ክስ ነው የተመሰረተብን፡፡

**ግዮን፡- በክሱ ውስጥ የተካተታችሁት ማን ማን ነበራችሁ?**

አቶ ዘሪሁን፡- በአንደኛ ደረጃ ሀገር ውስጥ የሌለው ኤልያስ ክፍሌ ነው፡፡ ሌላው ውብሸት ታዬ፣ ርዕዮት ዓለሙ ሂሩት ክፍሌና እኔ ነኝ፡፡

**ግዮን፡- የተከሰሳችሁት የፀረ ሽብር አዋጅ በወጣ ማግስት ከመሆኑ አኳያ በወቅቱ ይህን የመሰለ ጠጣር ያለ ክስ ሲቀርብባችሁ በእናንተ ላይ የነበረውን ስሜት ያስታውሱታል?**

አቶ ዘሪሁን፡- የፀረ ሽብር ዐዋጁ እንደወጣ የመጀመሪያው ታሳሪዎች እንደ መሆናችን ትንሽ የሚያስፈራ ነገር ነበረው፡፡ በዛ ላይ ስለ ተከሰስነው ነገር ምንም የምናውቀው ነገር አልነበረም፤ ከህጉ አንጻር እስከ ሞት ድረስ የሚያስቀጣ ክስ ስለነበር መጀመሪያ ላይ ትንሽ ደንግጬ ነበር፡፡ እነ ውብሸት በጋዜጠኝነት የተሳሳተ መረጃ በማቅረብ ነው የተከሰሱት፡፡ እኔ ላይ የወጣው ግን ሞት የሚያስፈርደው ክስ ነበር፡፡ በኋላ ላይ ነገሮችን ስትለምድ፤ ጠበቃህን ስታነጋግርና ሰዎችን ስታማክር መንፈስህ ይረጋጋል እንጂ እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ሲያጋጥምህ መጀመሪያ ላይ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ትረበሻለህ፡፡

**ግዮን፡- ለመጀመሪያ ጊዜ ፍርድ ቤት የቀረባችሁበትን ሂደት ቢያጫውቱን?**

አቶ ዘሪሁን፡- ወደ ፍርድ ቤት ስንመጣ እኛና የስዊድን ጋዜጠኞች ከፍተኛው ፍርድ ቤት ከምሽቱ 12፡30 ላይ ነበር የቀረብነው፤ በጓሮ በር ወስደው አንድ ቢሮ ውስጥ ዳኛ አስቀምጠው ጠበቁን፡፡ እንዴት በዚህ ምሽት ለዛውም ያለ ችሎት ጉዳያችን ይታይል ስንል ዝም ብላችሁ ቅረቡ እያሉ አካልበው አቀረቡን፡፡ ከዛ በፊት ጊዮርጊስ ያለው ፍርድ ቤት ሶስቴ ፖሊስ ጊዜ ቀጠሮ ጠይቆብን ተፈቅዶለታል፡፡ እዛ የነበረው ሁኔታ ቀልድ ነው ማለት እችላለሁ፡፡ ዳኞቹ የፖሊስ ታዛዥ ናቸው የሚለው ቃል የእኛን ችግር ይገልፀዋል፡፡ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ከሶስት ወር እስር በኋላ ስንቀርብ ብዙም የተለየ ነገር አልጠበቅንም፤ በምሽት እያንዳንዳችን ዘጠኝ መቶ ገፅ ክስ ተቀብለን ከመመለስ ውጪ፡፡

**ግዮን፡- ቤተሰብ እናንተን ለመጠየቅ የተፈቀደለት ከምን ያህል ጊዜ በኋላ ነው?**

አቶ ዘሪሁን፡-ከሶስት ወር በኋላ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ከቀረብን ከቀናት በኋላ ነው ቤተሰቤን ያገኘሁት፡፡ 900 ገፅ ክሴን በኩርቱ ፌስታል አድርጌ ልሰጣቸው ስወጣ ደነገጡ፡፡ በጊዜው ባለቤቴ ከመጠን በላይ ደንግጣ ራሷን መቆጣጠር አትችልም ነበር፡፡ ያንን ክስ ወረቀት ይዛ በቀጥታ የሄደችው ወደ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ጋር ነው፡፡ ክሱን ሲያይ እሱም በጣም ደነገጠ፡፡ በማግስቱ ወዲያውኑ እኛ ጋር መጣና ‹‹እይቼዋለሁ አይዟችሁ በርቱ እንደሚሆን እናደርጋለን፤ የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ እኛም ነገ የእናንተ ዕጣ ነው የሚደርሰን” በማለት አጽናናን፡፡ በእውነት በዚህ አጋጣሚ ላመሰግነው እወዳለሁ፡፡ መጥቶ ያረጋጋን እሱ ነው፡፡ በተለያዩ ጊዜያት በተደጋጋሚ መጥቶ ከጠየቀን ከአንድ ዓመት በኋላ እንዳለው እሱም በዚሁ የፀረ ሽብር ክስ ተከሶ እዛው እንደታሰርን ወደ ቃሊቲ መጣ፡፡ ነገር ግን እንዲህ ዓይነት ችግር ያጋጥማል አይዟችሁ ያለን፤ ያበረታን እሱ ነው፡፡

**ግዮን፡-ከማዕከላዊ ወደ ቃሊቲ የተዛወሩት መቼ ነበረ? በዚያስ ያለው ሁኔታ ምን ይመስላል?**

አቶ ዘሪሁን፡- ጳጐሜ 5/2003 ዓ.ም ነው ወደ ቃሊቲ የተዘዋወርነው፡፡ ቃሊቲ ዞን አንድ ነበር የታሰርነው፡፡ እዛ ያለው አሰቃቂና እንዲሁም ሰብአዊነት የጎደለው የእስረኛ አያያዝ በጣም ያሳዝናል፡፡ ኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በአፍሪካ ውስጥ በርካታ ዘግናኝ እስር ቤቶች አሉ እያለ ብዙ ዜና ሲያቀርብ እሰማለሁ፡፡ የ“ራሷ እያረረባት የሰው ታማስላለች” ማለት ይሄ ነው፡፡ እስረኛ ሰብአዊ ጥቃት የሚፈጸምበት ከማዕከላዊ ቀጥሎ እስር ቤቶች ውስጥ ነው፡፡ ዜጎች አካላቸው የሚጎልበትና የሚሞቱበት፤ በጠራራ ፀሐይ ዜጎች ተገለው በምን እንደሞቱ የማይጠየቅበት፤ ዘግናኝ የሆነ እስር ቤት ያለባት ሀገር መሆኗን ያወቅኩት ቃሊቲ ስገባ ነው፤በአጭሩ ምድራዊ ሲኦል ብለው ይቀለኛል፡፡ ዞን አንድ ለአንድ ወር ከቆየሁ በኋላ ጨለማ ቤት ወስደው አሰሩኝ፡፡ እዛም ልክ እንደ ጣቢያ ምራመር ይደረግብሃል፡፡ ሌላ ቶርቸር አለ፤ ፍርድ ቤቶች ወስነው የሚልኳቸው እስረኞቻቸውን ተመልሰው የማያዩበት ቦታ ነው፡፡ በጊዜው ወደ ስድስተኛ ቤት ወስደው እኔም ውብሸትም ጨለማ ቤት አቆዩን፡፡ አንዳንዴ ወደ ፍርድ ቤት በቀን ሁለት ጊዜ የምንወሰድበት ሁኔታም ነበር፡፡ ዳኞቹ ለይስሙላ የተቀመጡ፤ በተልዕኮ የሚፈፅሙ ናቸው፡፡ የፍትሕን የበላይነት ጠብቀው የአንተን ነፃነትና ወንጀለኛነት በትክክል የሚያዩ አልነበሩም፡፡ የሚገርምህ ነገር እስር ላይ እያለሁ አሳሪዎቼ ‹‹እዚሁ ትሞታታለህ



እንጂ አንተማ አትወጣም›› ይሉኝ ነበር፡፡ ብዙም ሳይቆይ የ17 ዓመት እስርና የ50 ሺሕ ብር ቅጣት ተላለፈብኝ፡፡

**ግዮን፡- ከቃሊቲ ወደ ቂሊንጦ ማረሚያ ቤት እንደተዘዋወሩ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር የአቶ መለስ ዜናዊ ህልፈተ ህይወትን ተከትሎ ከባድ ድብደባ እንደ ተፈፀመብዎት በጊዜው ሰምተን ነበር፡፡ እስኪ ያንን ሂደት ወደኋላ መለስ ብለው ይጫወቱን?**

አቶ ዘሪሁን፡- በኢትዮጵያዊያን ባህል መሰረት ጠላትህም ቢሞት አትደሰትም፡፡ ይሄ ጥሩ ባህላችን ነው፤ ነገር ግን በወቅቱ በእኔ ላይ የተደረገው ከዚህ የተገላቢጦሽ ነው፡፡ እኚህ ግለሰብ እንደሞቱ የሰማነው እንደማንኛውም ዜጋ ከወር በፊት ነው ፤በተለያዩ ሰዎች መረጃው ይመጣ ስለነበር የመሞታቸው ዜና ደርሶናል፡፡ ወሬው አንድ ወር ከሆነው በኋላ እውነት ተናግሮ የማያውቀው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ዘግይቶም ቢሆን ህልፈተ ዜናቸውን አቀረበ፡፡ እኔ ይሄ ዜና በቴሌቪዥን ሲተላለፍ ፈገግ የማለት ነገር አሳየሁ፡፡ እኔን ፈገግ(ሳቅ) ያደረገኝ የሰነበተና ቋንጣ የሆነ ወሬ እንደ አዲስ ዜና ባቀረበው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ሁኔታ ነው፡፡ ይሄንን ያዩ የሕወሓት ብሄር ተወላጅ የሆኑ የእስረኛ ደህንነቶች ሄደው ለበላይ አለቆች ተናገሩ፡፡ በዕለቱ ከምሽቱ 11 ሰአት ሲሆን ስሜ ተጠራና ወሰዱኝ፡፡ የእስር ቤቱ ሃላፊዎችጋር ከመድረሴ የዱላ መአት አወረዱብኝ፤ በካቴና አስረው እንዳልንቀሳቀስ አድርገው መሬት ላይ ከጣሉኝ በኋላ እጅግ ዘግናኝ በሆነ ሁኔታ ቀጠቀጡኝ፡፡ በወቅቱ ሕይወቴ የተረፈው በተአምር ነው፡፡ ያልተጎዳሁበት ቦታ አልነበረም፡፡ ፊቴ፣ እጄ፣ እግሬ፣ ሰውነቴ በጠቅላላ በደም ነው የራሰው፡፡ ዐሥራ አምስት የሚሆኑ ሰዎች ዘግናኝ በሆነ ሁኔታ ተባብረው ያለ እረፍት ቀጠቀጡኝና በደም እየታጠብኩ መልሰው ከክፍሌ አስገቡኝ፡፡ በጊዜው በጣም በመጎዳቴ አንዳንድ ሰዎች ህክምና ያግኝ ቢሏቸው‹‹ እንዲሁ እያያችሁት ይሙት›› የሚል ምላሽ ሰጧቸው፡፡ በጊዜው ሕክምና እንዳላገኝ ቢከለክሉኝም የእግዚአብሔር ፍቃዱ ሆኖ ልተርፍ ችያለሁ፡፡

**ግዮን፡- ከፍርድ በኋላ እፈታለሁ ብለው አስበው ያውቃሉ?**

አቶ ዘሪሁን፡- ለሕዝብ ነፃነትና ትግል መሥዋዕት ለመሆን አስበህ እስከ ተነሳህ ድረስ የሚመጣብህን ማንኛውንም ነገር በፀጋ ተቀብለህ እስከ መጨረሻው ለመቀጠል የአላማ ፅናት ሊኖርህ ይገባል፡፡ የታሰርኩበት ጉዳይ ያመንኩበት አላማ ስለነበር ምንም የሚያስጨንቀኝ ነገር አልነበረም፡፡ ነገር ግን አንድ ቀን በአቋራጭ ሊመጣ የሚችል አንዳንድ ነገሮች እንዳሉ ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታዎች ይጠቁሙን ነበር፡፡ እስሩን ላንጨርሰው እንደምንችል አንዳንድ ምልክቶች እስር ላይ ሆነን አይተናል፡፡ ያ ተስፋችን በሕዝቡ ግፊትና ጥያቄ ዕውን ሆኖ ዳግም ከቤተሰቦቻችን ጋር ልንገናኝ ችለናል፡፡ በዚህ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለውለታችን ነው፤ በመፈታቴ በጣም ደስ ብሎኛል፡፡

**ግዮን፡- አሁን ከእስር ተለቀዋል… በቀጣይ ከእርስዎና ድርጅትዎ ምን እንጠብቅ?**

አቶ ዘሪሁን፡- የኢትዮጵያ ፖለቲካ ሂደት ገና ከቆፈኑ አልተላቀቀም፤ ያለው ሥርዐት የአንድ ብሔር የበላይነት የሰፈነበት ነው፡፡ ይሄ መቀየር፣ ሕዝቦች እኩል በሆነ መንገድ ተጠቃሚ መሆን አለባቸው፡፡ እኔም ሆንኩ ሌሎች የፖለቲካ ሰዎችና ጋዜጠኞች ለእዚህ ነው የታገልነው፡፡ ወደፊትም በዚህ መንገድ እጓዛለሁ፡፡ ድርጅቴ በእስር ላይ እያለሁ ከፓርቲው ሊ/መንበርነቴ አላነሳኝም፡፡ አሁን ስፈታም ያንኑ ቦታ ነው መልሰው ያስረከቡኝ፤ ስለ እዚህ ትግሌን ሰላማዊ በሆነ መንገድ እቀጥላለሁ፡፡

# ከአሜሪካ ፕሬዝዳንት ቀጥሎ ከፍተኛው ደመወዝ ተከፋዩ ኢትዮጵያዊው ተመራማሪ

በዓለም አቀፍ ደረጃ ካንሠርን በተመለከተ በሚካሄዱ ምርምሮች ላይ ከተሰማሩ እውቅ ተመራማሪዎች መሐል አንዱ ትውልደ ኢትዮጵያዊው ዶክተር ኤሌክትሮ ክበበው ይባላል፡፡

ከወር በፊት ከዓለማችን እውቅ ዩኒቨርሲቲ ዎችና የምርምር ማዕከላት በአንዱ ስታንፎርድ ዩኒቨርሲቲ በአጠቃላይ የቀዶ ሕክምና የትምህርት ክፍል ዋና ኃላፊ ሆኖ እንዲሠራ መመረጡ በመላው አሜሪካ አነጋጋሪ ዜና ሆኖ ነበር የሰነበተው፡፡

ትውልደ ኢትዮጵያዊው ዶክተር ኤሌክትሮ ክበበው ላለፉት ሰባት ዓመታት በሀገረ አሜሪካ ከፕሬዝዳንቱ ቀጥሎ ሁለተኛው ከፍተኛው ደመወዝ ተከፋይ በመሆን በሙያቸው እጅግ ከተሳካላቸው አሜሪካውያን ተርታ ለመሰለፍ በቅቷል፡፡

የ41 ዓመቱ ዕውቅ ተመራማሪ ዶክተር ኤሌክትሮ ክበበው የተጣበበ ጊዜው ሳይገድበው በሚገኝባቸው የትውውቅ መድረኮች ሁሉ ለኢትዮጵያውያን ወገኖቹ በርትተው በመማር በፅናት የሚያጋጥማቸውን ፈተና እና መሰናክል በማለፍ ስኬታማ ሆነው ወገናቸውና የተቀረው ዓለም የተሻለ ሕይወት እንዲኖር እንዲጣጣሩ ጥሪውን ከማስተላለፍ ተቆጥቦ አያውቅም፡፡

አዲስ አበባ ውስጥ ተወልዶ እስከ ዐሥር ዓመቱ ድርስ ከእኩዮቹ ጋር የማይረሳ የልጅነት ጊዜ እንዳሳለፈ ይናገራል፡፡ ብዙዎችን ባስገረመ መልኩ የኤሌክትሪካል ምሁር የሆኑት አባቱ ኢንጂነር ክበበው በድህነት፣ በኋላቀርነትና በፖለቲካ ቀውስ የምትታመሰውን ሀገራቸው በእያንዳንዱ የገጠር መንደር የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ እንዲሆን የሰነቁትን ምኞት በልጆቻቸው ላይ ለማስረፅ በማሰብ ስማቸውን ኤሌክትሮን፣ ንስትሮን እና ኢዮትሮን ክበበው የሚል ስም ነበር ያወጡላቸው፡፡

ይሁንና አባት ልጆቻቸው በተመኙት መልኩ እንዲሰማሩ ቢያስቡም ሕይወት ግን ሌላ መንገድ ነበር የቀየሰችው፡፡ የ1966ቱን አብዮት ተከትሎ በሀገሪቱ በተፈጠረው የፖለቲካ ቀውስ ሳቢያ ኢንጅነር ክበበው ቤተሰቦቻቸውን ይዘው ወደ አሜሪካ ሄዱ፡፡ ይሔን ጊዜ ነበር የዐሥር ዓመቱ ታዳጊ ኤሌክትሮን ከማያውቀው ማኅበረሰብ ጋር የመኖር ዕጣ ፈንታ የገጠመው፡፡ በሎሳንጀለስ ካሊፎርኒያ መኖር የጀመሩት እነ ኤሌክትሮን በምድረ አሜሪካ ገና ከቀለምና ከዘር ልዩነት አስተሳሰብ ያልፀዳ ማኅበረሰብ የነበረ ቢሆንም፣ በእናታቸው ፅናትና ጠንካራ አስተዳደግ ታግዘው የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በዚያው በማጠናቀቅ ውጤታማ ልጆች ለመሆን በቅተዋል፡፡

ዶክተር ኤሌክትሮ አባቱ ያወጡለት ስም በወቅቱ ባልተዋሐደው የአሜሪካ ማኅበረሰብ ውስጥ እንዴት እንደተቀበሉት ተጠይቆ ሲናገር "ሰዎች እንደኔ ዓይነት ከሳይንስ ጋር የተያያዘ ስም ሲኖራቸው በሌሎች ዘንድ ለየት ያለ ትኩረት ይሰጣቸዋል፡፡ ብዙዎች ባግራሞት ተሞልተው ስሜ ትክክል መሆኑን ይጠይቁኝ ነበር፡፡ ዛሬ ለደረስኩበት ስኬት ስሜ በራሱ ተፅዕኖ ያለው ይመስለኛል " ብሏል፡፡



ዶክተር ኤሌክትሮ

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ በሎሳንጀለስ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በኬሚካል ኢንጂነሪንግ የትምህርት ዘርፍ የመጀመሪያ ዲግሪውን ቢያገኝም ወደ ሥራ አልተሰማራም፡፡ የመጀመሪያ ዲግሪውን የተቀበለበትን ኬሚካል ኢንጅነሪንግን ትቶ የሕክምናውን ዓለም ለምን እንደተቀላቀለ ሲጠየቅ "የኬሚካል ኢንጂነሪንግ ዘርፍን ትቼ ወደ ሕክምናው ዘርፍ ማተኮር የፈለኩት ተመርምሮ በማያልቅ በእግዚአብሔር እጅ ሥራ የታነፀው የሰው ልጅ ተፈጥሮ ሁልጊዜ ስለሚያስገርመኝ ነው" በማለት መልሷል፡፡

ፊቱን ወደ ሕክምና የትምህርት ዘርፍ በማዞር በዩኒቨርሲቲ ኦፍ ሎስአንጀለስ የቀዶ ጥገና ትምሕርት ክፍል በመግባት የሁለተኛ ዲግሪውን አገኘ፡፡ በድጋሚ በዩኒቨርሲቲው አናኮሎጂ ዲፓርትመንት ውስጥ ሦስተኛ ዲግሪውን በማግኘት በዩኒቨርሲቲው ስመጥር ምሁራን ተርታ ያሰለፈውን እውቅና የተጎናፀፈበትን ውጤት አስመዘገበ፡፡

የዶክትሬት ዲግሪውን እንደያዘ ከባለቤቱ ቫዮላንታ ጋር ትዳር በመመሥረት ሕይወቱን ሙሉ አድርጎታል፡፡ "ዛሬ ለደረስኩበት ስኬት የባለቤቴ አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው፤ ላለሁበት ከፍታ የእናቴና የእርሷ ድጋፍ እንዲሁም እገዛ ባይኖር የዛሬው እኔነቴ ሌላ ነበር ይላል" ዶክተር ኤሌክትሮ ክበበው፡፡

በሎሳንጀለስ ዩኒቨርሲቲ አናኮሎጂ ዲፓርትመንት ካንሠርን በተመለከተ በሚደረግ የጥናትና ምርምር ሥራ ውጤታማ ግኝት ላይ በመድረሱ ዝናው ከፍ እያለ ሄዷል፡፡

በዓለም አደገኛና ገዳይ ከሚባሉ በሽታዎች ውስጥ ዋነኛው በሆነው ካንሠር ዙሪያ የዶክተር ኤሌክትሮ አስደናቂ ግኝቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ በዓለም ላይ ከፍተኛ ተቀባይነት ያገኙ ምርምሮች መሆናቸውን የተረዳው የናሽናል ካንሰር ኢንስቲቲዩት ቦርድ ወዲያው ነበር የቦርዱ ሰብሳቢ እንዲሆን የመረጠው፡፡

በካንሰር ህመም በሚሰቃዩ ህሙማን ላይ ለዓመታት በተካሄደ ጥናትና ምርምር በተለይም ኬሞትራፒ ህክምና የሚከታተሉ ህሙማን የታይሮድ ዕጢያቸው አዮዲን እንዳይቀበል ስለሚያደርግ አብዛኞዎቹ ህክምናውን የሚወስዱ ሕሙማን ለስኳር ሕመም ይጋለጣሉ፣ ይህ ደግሞ "ላይቶቶክሲል" የተባለውን የካንሰር መድኃኒት ዋጋቢስ ያደርገዋል፡፡

ዶክተር ኤሌክትሮ ክበበው ይህን ችግር እስከ ወዲያኛው ሊቀርፍ የቻለ "ራዲዮ አዮዲን" የተሰኘ አዲስ ግኝት በመፍጠር ዓለምን ከጭንቀት አውጥቶአል፡፡

ትውልደ ኢትዮጵያዊው ዶክተር ኤሌክትሮ ክበበው በቀዶ ጥገናው ሥራ ዘርፍ ከ2000 በላይ የተሳኩ የቀዶ ሕክምናዎችን ከማድረጉ በተጨማሪ ከ300 በላይ የጥናትና ምርምር ሥራዎቹ በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂነት ባተረፉ ሜዲካል ጋዜጦች ላይ ታትመውለታል፡፡

በትዳሩ ደስተኛ እንደሆነ የሚናገረው ዶክተር ኤሌክትሮ ክበበው ከወይዘሮ ታይዳ ቫዮላንታ "ራስ ኤሌክትሮ" እና "ኢዛና ኤሌክትሮ" የተባሉ ሁለት ወንድ ልጆችን አፍርቷል፡፡

ዕውቁ ተማራማሪ ስለ ልጆቹ እናት ሲናገር "ወይዘሮ ታይዳ ቫዮላንታ በዩኒሴፍ የኤች አይ ቪ ኤድስ ዲፓርትመንት ተቀጥራ በኢትዮጵያ ለዓመታት ሠርታለች፡፡ ይሄ ደግሞ ስለ ኢትዮጵያ ታሪክና ባህል አጠቃላይ እውነታ ከእኔ በላይ የምታውቅ ስለሆነች ልጆቼ የኢትዮጵያን ታሪክ ፣ ባህል እንዲያውቁ የማድረጉን ኃላፊነት በመወጣት ረገድ ጉልህ ሚና ተጫውታለች" በማለት ነው፡፡

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ2011 በሀገረ አሜሪካ ከአንድ ሺሕ ከፍተኛ ደመወዝ ከሚከፈላቸው ዜጎች ዝርዝር ውስጥ ከቀድሞ ከፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማ ቀጥሎ ሁለተኛው ከፍተኛ ደምወዝ የሚከፈለው ባለሙያ ትውልደ ኢትዮጵያዊው ተመራማሪ ዶክተር ኤሌክትሮን ክበበው እንደሆነ ይፋ ሆኗል፡፡

"ከደመወዝ ክፍያ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ስሜ መጠቀሱ ብዙም አላስደሰተኝም፣ ከዚህ ይልቅ በካንሰር እየተሰቃዩ ያሉ ሚሊዮኖችን ሕይወት ለመታደግ ከህክምናው ጋር ተያያዥ የሆኑ ችግሮችን ለማስወገድ የሚያስችል የምርምር ግኝት አግኝቼ ስሜ ቢጠቀስ እመርጣለሁ፣ ማን ያውቃል ከሥራ ባልደረቦቼ ጋር እያደረኩ ያለው የምርምር ጥናት ለዚያ ውጤት ያበቃኝ ዘንድ እመኛለሁ" ብሏል፡፡

በየዓመቱ በአሜሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ልጆቻቸው ኢትዮጵዊ ማንነታቸውን ብሎም ባሕልና ታሪካቸውን እንዲያውቁ አርአያ የሆኑ ባለሙያዎችን በሚጋብዙበት "Heritage and culture camp" ላይ በተደጋጋሚ ተጋባዥ በመሆን ልምድና ክህሎቱን ለተተኪዎች አካፍሏል፡፡ በተጋበዘበት ኢትዮጵያዊ መድረክ ላይም "ወገኖቼ በምንም ነገር ተስፋ አትቁረጡ፣ ፅናትና ዓላማ ካላችሁ ያሰባችሁበት ትደርሳላችሁ፡፡ እናም ፈፅሞ ተስፋ አትቁረጡ ተማሩ ሁሌም ለመማር ዝግጁ ሁኑ" የሚለው ዕውቁ ዓለም አቀፍ ኢትዮጵያዊ ተመራማሪ የዶክተር ኤሌክትሮ ክበበው ምክር ማሳረጊያ ይሁነን፡፡

TUBE

**Like & Subscribe**

# የመዝናኛ አምራጭ
# አመረጃ ተመራጭ
# ሳቢና ተጻማጭ

www.Dagutube.com
አድራሻ ፡- ጣይቱ ሆቴል ግቢ ውስጥ ቢሮ ቁጥር 140
ስልክ ፡- 0911668805




ግዮን
መጽሔት

12
9 3
6

ግዮን መጽሔት
በየ15 ቀን ቅዳሜ
ይጠብቁዋት!

ቀጣይ ዕትም
ቅዳሜ
መጋቢት 22
ይጠብቁን!

ድርጅትዎንና
አገልግሎትዎን
ያስተዋውቁ!

በቀጣይ
ዕትማችን
የተመረጡ
አምዶቻችንን
ይዘን እንመጣለን

ፃፉልን፣
አስተያየት
ይስጡ ምልሻችን
ፈጣን ነው




ስልክ : +251 912165606
+251 912165606
ኢ-ሜይል: gihonmeg@gmail.com
Facebook: gihon2010meg@gmail.com